የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ

ትምህርት ሚኒስቴር
ግንቦት 2001 ዓ.ም.

ርዕስ **ገጽ**

1 **መግቢያ** 3
2 **ዓላማ**.....3
3 **የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሥርዓት መዋቅር** 4
3.1 **የመጀመሪያ ሳይክል** /9-10/ 4
3.2 **የሁለተኛ ሳይክል** /11-12/.....4
4 **የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አደረጃጀት** 5
4.1 **የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች** 5
4.2 **የምድረ ግቢው ገፅታ አደረጃጀት** 6
4.3 **የምድረ ግቢው ስፋት** 6
4.4 **የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ህንፃ አደረጃጀት** /9-12/.....7
4.4.1 **የመማሪያ ክፍሎች ስፋት በሜትር ካሬ** 7
4.4.2 **የአስተዳደር ህንፃ** /ብሎክ/ **ስፋት በሜትር ካሬ** 8
4.4.3 **የተማሪዎች መፀዳጃ**.....8
4.4.4 **የቤት መፅሐፍት ህንፃ** /ብሎክ/.....9
4.4.5 **የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተ ሙከራ ክፍል /ህንፃ**.....10
4.4.5.1 **የፊዚክስ፣ ላቦራቶሪ ክፍል** /ብሎክ/**ስፋት በሜትር ካሬ** 10
4.4.5.2 **የኬሚስትሪ ላቦራቶሪ ክፍል** /ብሎክ/.....10
4.4.5.3 **የባዬሎጂ ላቦራቶሪ ክፍል**/ብሎክ/**ስፋት በሜትር ካሬ** 10
4.4.5.4 **የሂሣብ ክፍል ብሎክ ስፋት በካሬ ሜትር** 10
4.4.5.5 **ከሳይንስ ውጪ ለሚሰጡ ትምህርቶች የሚገለግሉ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ክፍሎች** 11
4.4.6 **የመሰብሰቢያ አዳራሽ** /ብሎክ/ 11
4.4.7 **የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል**.....11
4.5 **ለተለያዩ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች** 12

4.5.1 የመማሪያ ክፍል.....12
4.5.2 የላቦራቶሪ ክፍል 12
4.5.3 የሂሳብ ትምህርት ክፍል 13
4.5.4 የቢሮ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች.....13
4.5.5 ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚያስፈልጉ የሰውነት ማጎልመሻና ስፖርት ትምህርት ቁሳቁስ.....14
4.5.6 ለመማር ማስተማር ሂደት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎት መስጪያ ክፍሎች የሚስፈልጉ ቁሳቁሶች.....18
4.5.6.1 ቤተ መፅሐፍት 18
4.5.7 ICT ማዕከል 21
4.5.8 ትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል 21
4.5.8.1 የቢሮ ዕቃዎችና መሳሪዎች 21
4.5.8.2 የእጅ መሳሪያዎች 22
4.5.9 የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ.....23
4.5.10 የመምህራንና ተማሪዎች መዝናኛ ክበብ 24
4.5.10.1 የመምህራንና የሠራተኛና ክበብ.....24
4.5.10.2 የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ.....24
4.5.11 የአዳራሽ አጠቃቀም 25
4.6 ለየትምህርቱ ዓይነቱ የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች 25
4.6.1 ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች 26
4.7 የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ.....27
4.8 የተማሪ ክፍል ጥምርታ 27
4.9 የሰው ኃይል ምደባ 27
4.9.1 የመምህራንና የሠራተኞች ተፈላጊ የትም/ደረጃ.....27
4.9.2 የልዩ ትምህርት መምህራንና የሠራተናች ድልድል.....29
5 የማስተማሪያ ዘዴ.....30
6 የሁለተኛ ደረጃ መምህር ፕሮፋይል.....30
6.1 ከሁለተኛ ደረጃ መምህራን የሚጠበቁ ባህሪይ 31
7 የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ፕሮፋይል 32
8 የማስተማር መማር ሂደት መመሪያዎች 32
8.1 የትምህርት አመራርና አስተዳደር መመሪያዎች 33
9 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት 34
9.1 የትምህርት ዓይነቶች የክፍለ ጊዜ ስርጭት 35
9.1.1 በመጀመሪያ ሳይክል /9-10/ የሚሰጡ የትም/ዓይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት.....35
9.1.2 በሁለተኛ ሳይክል /11-12 /የሚሰጡ የትም/ዓይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት 36
10 የትምህርት ወቅት 38
10.1 የት/ቤት ሰዓት.....38

10.2 የተጓዳኝ ትምህርት 39
11 የመረጃ አያያዝና ፍሰት 40
12 የትምህርት ደረጃ ምዘናና ማጠናቀቂያ መረጃ 41
13 በማረጋገጫ የውስጥ የትም/ማስረጃዎች 42
14 የት/ቤት ፣የአካባቢ ማህበረሰብ /ኮሙኒቲ/ እና የወላጅ ግንኙነት 42

1. መግቢያ

የአንድ አገር ሥልጣኔና ዕድገት ሊገነባ የሚችለው አገሪቱ ባላት የተማረ የሰው ሀይል መሰረት መሆኑ ግልፅ ነው። የመልካም አስተዳደርና ፈጣን የልማት ስትራቴጂን ተግባራዊ የሚያደርግ፣ የህዝብና የሀገር ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀና ሀላፊነት የሚሰማው ከተፈጥሮ ተጽዕኖ በተግባር ለመላቀቅ የተዘጋጀ የማምረትና የመመራመር አቅሙ የዳበረ ዜጋ ለማዘጋጀት የሚያስችል የአጠቃላይ የትምህርትና ሥለጠና ፖሊሲ ተቀርጿል። የትምህርት ፖሊሰውን መሰረት በማድረግ በአገሪቱ ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የትምህርት እንቅስቃሴ እንዴት መካሄድ እንዳለበት፣ ምን ምን ዓላማዎች ሊኖሩት እንደሚገባ በትምህርት ፖሊሲው ተካተዋል...

ይኽ የተቀረጸው የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ውጤታማ እንዲሆን ደግሞ የትምህርቱ እንቅስቃሴ ጥራት በየወቅቱ መለካት መቻል አለበት። ለዚሁም የኢትዩጵያ ፊደራላዊ ዲሞክራሲያዊ መንግሥት የትምህርት ሚኒስቴር ፖሊሲውን መሰረት በማድረግ በ1987ዓ.ም. የትምህርት ስታንዳርድ ለየእርከኑ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረጉ የሚታወስ ነው። በዚህ ስታንዳርድ አማካኝነት ትምህርት ሚኒስቴር በአገሪቱ ውስጥ ያለውን የትምህርት እንቅስቃሴ ጥራት ለማስጠበቅ አስፈላጊ ጥረት አድርጓል። በአሁኑ ወቅትም ይኽንን የትምህርት ስታንዳርድ አገሪቱ ካለችበትና ከደረሰችበት የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታዎች አንፃር ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ ይኽ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ ተሻሽሎ ቀርቧል።

2 ዓላማ

ይኸ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ስታንዳርድ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- በተማሪው ላይ ለማምጣት የተፈለገውን ባህርይ በግልፅ ለማስቀመጥና ለመለካት እንዲቻል፣
- በትምህርት ቤቱ መሟላት የሚገባቸው ቁሳቁሶችንና ፋሲሊቲዎችን ለመወሰን፣
- የትምህርት ቤቱና የአካባቢ ህብረተሰብ ግን ኙነት ይበልጥ ለማጠናከር፣
- በትምህርት ቤቱ ሊኖር የሚገባውን የሰው ኃይል ለመወሰን፣
- የትምህርት ቤቱ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ከትምህርቱ አንቅስቃሴ አመቺነት አንፃር ምን መምሰል እንደሚገባቸው በግልፅ ለማስቀመጥ ነው፡፡

3 የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ሥርዓት መዋቅር

በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሰረት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሁለት ሳይክል ተከፍሎ የሚሰጥ ሲሆን በመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ከ9ኛ– 10ኛ ክፍል በሁለተኛ ሳይክል ደግሞ ከ11ኛ–12ኛ ክፍል የሚሰጥ ነው፡፡

3.1 በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል እድሜያቸው 15 ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆናቸው የአጠቃላይ ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን በሚከተሉትን ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

- በዚህ እርከን የሚሰጥ ትምህርት ተማሪው በአግባቡ ትምህርቱን እንዲረዳው፣ ያለውን የግል ተሰጥኦውን ተረድቶ የወደፊቱን ፍላጎቱን እንዲገነዘብና ለቀጣዩ ትምህርት የሚስማማውን የትምህርት መስክ እንዲመርጥ የሚያዘጋጀው ነው ::
- በዚህ ሳይክል የሚሰጠው የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ ነው፡፡

3.2 በ2ኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት እድሜያቸው 17 ዓመትና ከዚያም በላይ ለሆኑ ከአጠቃላይ ትምህርት ጋር ተዛምዶ የሚሰጥና ተማሪዎች በቂ ችሎታና ክህሎቶች ገብይተው እንዲጨርሱና ለከፍተኛ ትምህርት በብቃት እንዲዘጋጁ የሚያደርግ ነው::

የልዩ ፍላጎት ትምህርትም የመደበኛውን ትምህርት መዋቅር የሚከተል ነው፡፡ ነገር ግን በአካልና በአእምሮ ችሎታ ችግር ምክንያት ለመደበኛ ትምህርት ታስቦ የወጣውን እርከን ከሌሎች ተማሪዎች በእኩል መዝለቅ አይችሉም፡፡ በሌላ በኩል

በጣም የመጠቁ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች ደግሞ የተለየ ችሎታ በሚያሳዩበት ትምህርት ዓይነት እንዲገፉበት ሁኔታዎች ማመቻቸት ያስፈልጋል።

በመሆኑም በእነዚህ ሁለት የተለያዩ ባህሪያት ያላቸው ወጣቶች ችሎታ ያለው መምህር ተመድቦ ተጨማሪ እገዛ እንዲያደርግላቸው ይደረጋል። ስለሆነም በተለያዩ ዘርፎች ላይ የሚገኙት ልዩ ትምህርት ለሚያሰፈልጋቸው ተማሪዎች በአብዛኛው በሚከተሉት የትምህርት እርከኖች ሊሳተፉ ይችላሉ።

	የልዩ ፍላጐት ትምህርት ወጣቶች	የትምህርት እርከን	
		9–10	11–12
1	ማየት የተሳናቸው	ይሳተፋሉ	ይሳተፋሉ
2	የስሜት መረበሽ ያለባቸው	እንደሁኔታው	እንደሁኔታው
3	መናገር የተሳናቸው	ይሳተፋሉ	ይሳተፋሉ
4	የአካል ጉዳት ያለባቸው	ይሳተፋሉ	ይሳተፋሉ
5	ተደራራቢ ጉዳት ያለባቸው	እንደ ሁኔታው	እንደሁኔታው
6	የጎዳና ላይ ተዳዳሪ	ይሳተፋሉ	ይሳተፋሉ
7	ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው	ይሳተፋሉ	ይሳተፋሉ
8	መስማት የተሳናቸው	ይሳተፋሉ	ይሳተፋሉ

4. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አደረጃጀት

4.1 የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች

ጥራት ያለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለማስፋፋት ት/ቤቶቹ ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ መሆን አለባቸው። ከዚህ አንፃር አንድ ት/ቤት የሚከተሉትን መሰፈርቶች ማሟላት አለበት።

- ተማሪዎች ተመላልሰው ሊማሩ የሚችሉበት ሆኖ ከተማሪዎች መኖሪያ ክልል አማካይ ርቀት ከ3–5 ኪሎ ሜትር ያልበለጠ፣ /እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል/
- የመኪና መንገድ፣ መገናኛ ያለው ወይንም ከመገናኛ መንገድ ቅርበት ያለው፣
- የአካባቢውን ጸጥታ ከሚያውኩ ከትራፊክ መጨናነቅ፤ ከመጠጥ ቤቶች፤ ከገበያ ፣ከወንዝ፣ ከጫት መቃሚያ ቤቶች፣ ከሙዚቃ ቤቶች የራቀ፣
- የት/ቤቱ ግቢ ወጣ ገባ ያልበዛበት ወይም ሜዳማ የሆነ ቦታ ያለው፣
- ለትምህርት ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚሆን በቂና ተስማሚ የእስፖርትና የጓሮ አትክልት ቦታ ያለው ፤
- የመሬቱ አቀማመጥ ለጎርፍ ፤ ለፍሳሽ ለከባድ ንፋስና ለአቧራ ያልተጋለጠ፤
- የውኃ የመብራትና ስልክ አገልግሎት ያለው፤

4.2 **የምድረ ግቢው ገጽታ አደረጃጀት**

የሚቋቋሙ ት/ቤቶች በተማሪዎች የመማርና የማስተማር ውጤቶች ላይ ተፅዕኖ ከሚያስከትሉ ነገሮች ነፃ መሆን አለባቸው። አንድ ት/ቤት የሚከተሉት ገጽታና አደረጃጀት ይኖሩታል።

- ለመማሪያና ለተለያዩ አገልግልቶች የሚውሉ ብሎኮችና ክፍሎች እንደ ሥራ ቅርበታቸውና አገልግሎታቸው የተሰሩ፤
- የህንፃዎች አደረጃጀት የምድረ ግቢውን ውበት አጠባበቅ ግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ የመኪና ማቆሚያና የእግር መንገዶች እንደ አስፈላጊነቱ የተሠራለት ፣
- የመዝናኛ መጫዎቻ ቦታዎች / ሜዳዎች/ ያሉት
- በአጥር የተከለለና የተከበረ፤
- ከክፍል ውጭ ሰሚሰጡ ትምህርቶች /እርሻ ፤ እስፖርት . . ./ ተመጣጣኝ ቦታ በግቢው ውስጥ ያሉት ፣
- በአጠቃላይ የህንፃዎች አደረጃጀትና የመንገዶች አቀማመጥ ለትምህርት አሰጣጥ አመቺና መስጎብ ያለው ይሆናሉ።

4.3 **የምድረ ግቢው ስፋት**

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሊኖረው የሚገባው የምድረ ግቢው ስፋትና መጠን አንደተማሪዎች የዕድገት ደረጃና የእንቅስቃሴ ሁኔታ የተለያዩ ትምህርት ኘሮግራሞች ሊያቅፍ ስለሚችል ከ30,000 – 60,000 ሜትር ካሬ ስፋት ያለው ቦታ ይኖረዋል። ሆኖም በከተማና በገጠር እንደየሁኔታው ሊለያይ የሚችል ሲሆን በገጠር የትምህርት ቤቶችን የውስጥ ገቢ ለማጠናከር እንዲቻል የተቀመጠው አሐዝ ባለበት የሚቀጥል ይሆናል። ነገር ግን በከተማ ካለው የቦታ ጥበት አኳያ የት/ቤቶች ህንፃዎች ፎቆች ሊሆኑ እንደሚችሉ እና እንዲሁም የእስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎች ከአንድ አገልግሎት በላይ እንዲሰጡ ተደርገው ይሠራሉ።

4.4 የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሕንፃ አደረጃጀት (ከ9–12 ክፍል)

- የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕንፃ እንደየባህሪያቸው ተለያይተው የተሰሩና ለጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት በዕቅድ፣ በአቅምና ለብዙ አካባቢዎች በማዕከልነት ተሰባስበው የሚገለገሉበት ስለሚሆን ከብሎኬት፣ ከሸክላ ወይም ከድንጋይ እንደ አካባቢው የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት እየታየ ሊሰራ ይችላል።
- የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ህንጻዎች ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ይሆናሉ።
- የሕንፃው አደረጃጀትም በተመለከተ አንድ ወጥ በመሆኑ ከ9–12 ወይም በተናጠል ከ9–10 እና ከ11–12 ተብሎ እንደየእድገት ደረጃው ሊዋቀር ይችላል።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች (9-12) የህንጻዎች አደረጃጀት እንደየፕሮግራሙ ሁኔታ ተፈላጊ የሆኑ የሚከተሉት ህንፃዎች ይኖሩታል።

4.4.1. የመማሪያ ክፍሎች ስፋት በሜትር ካሬ

- እንድ የመማሪያ ክፍል ለ40 ተማሪዎች የሚበቃ ሆኖ መጠኑ 7.20×6.40=46.08 ካ.ሜ ይሆናል።

- በጥቅሉ ባለ አራት የመማሪያ ክፍል የብሎኩ መጠን 7.10×29.80=211.58 ይሆናል።
- የመማሪያ ክፍሎችና ብሎኮች ትምህርት ቤቱ በሚኖረው የተማሪ ብዛት እና በአካባቢው የአየር ፀባይ መሰረት የሚወሰን ሲሆን የትምህርቱን ሥራ በአግባቡ ለመምራትና ውጤታማ የማስተማርና መማር ሂደት ለማካሄድ እንዲቻል የቤቱ ቁመትና የመስኮቶቹ ስፋት ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት። አንድ ትምህርት ቤት ከ3000 ተማሪዎች በላይ ማስተናገድ የለበትም።

4.4.2 የአስተዳደር ሕንፃ /ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

ተ.ቁ	ክፍል/ቢሮ	መጠን/ስፋት	
1	የርዕሰ መምህር ቢሮ	355×3.53=12.53	
2	ም/ ርዕሰ መምህርት ቢሮ	3.55×3.53=12.53	
3	የአስተዳደር ቢሮ	3.55×3.53=12.53	
4	የመዘክር ክፍል .	3.55×3.53 =12.53	
5	የፀሐፊ ቢ፱	3.00×3.53=10.59	
6	የመምህራን ማረፊያ	3.70×7.60=28.12	
7	የመጀመሪያ ህክምና እርዳታ ክፍል	3.53×4.20=14.83	
8	የመቆያ ቦታ	1.80×2.30=4.14	
9	ንብረት ክፍል	555×6.70=37.19	
10	ዕዳት ሠራተኛ ክፍል	14.85×1.2=17.82	
11	መጸዳጃ ቤት	2.15×2.85=6.13	
12	2 የጥበቃ ቤት (እንደየ ት/ቤቱ ሁኔታ ይወሰናል)	2.45×2.45=6.00	

ተ.ቁ	ክፍል/ቢሮ	መጠን/ስፋት	
13	የሚይንዲስሪቢዩሽን / የኤሌክትሪክ ዋና ማከፋፈያ / ያለበት ክፍል	1.00×1.48=1.48	
	ባጠቃላይ የብሎክ መጠን	22.40×7.10=159.04	

4.4.3 **የተማሪዎች.መጸዳጃ**

የወንድና የሴት መፀዳጃ ቤቶች ፊትና ጀርባ ሆነው የሚሠሩ ሲሆን፣

4.4.3.1 **የወንዶች ደረቅ መጸዳጃ ቤት / ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ**

- **ባለ** 8 **ቀዳዳ ደረቅ ሽንት ቤት የአንዱ ሽንት ቤት መጠን** 0.90×1.2 **ሲሆን በጥቅሉ የብሎኩ መጠን** 5.30×4.2=22.26 **መሆን አለበት።**
- **የእጅ መታጠቢያ ቧንቧ ይኖረዋል።**

4.4.3.2 **የሴቶች ደረቅ መጸዳጃ ቤት / ብሎክ/**

- **ከላይ በተራ ቁጥር** 4.4.3.1 **አንደተጠቀሰው መጠኑ እኩል ነው።**
- **የእጅ መታጠቢያ ቧንቧ ይኖረዋል።**

4.4.4_**የቤተ መጻሕፍት ሕንፃ / ብሎክ/**

- **የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የቤተመፃህፍት ህንፃ ስፋት የሚወሰነው በዓመቱ ውስጥ ከሚመዘገቡት የተማሪዎች ቁጥር ከ**5-10 **በመቶ በአንድ ጊዜ ሊያስተናግድ በሚችል ሆኖ።**

  መጻሕፍት በሚመደቡበት ወቅት 10 **በመቶ ልብወለድና** 90 **በመቶ ደግሞ ማጣቀሻ መጻሕፍት ይመደባሉ።**

  በአጠቃላይ ለሁሉም ት/ቤቶች ለአንድ ተማሪ በአማካኝ ከ4 **እስከ** 5 **መፃህፍት እንዲደርሳቸው ታስቦ ቤተ መፅሕፍቱ መደራጀት አለበት።**

  በሁለተኛ ደረጃ የሚቋቋም ቤተመጻሕፍት የሚከተሉትን የሥራ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል።

- **የተማሪዎች የማንበቢያ ክፍል** 10 **ሜትር** x 20 **ሜትር** = 200 **ካሬ ሜትር፣**
- **የመጻሕፍት ማዋሻና መቀበያ ስፍራ** 30 **ካሬ ሜትር፣**
- **የአዳዲስ መጻሕፍትና መፅሔቶች ማስተዋወቂያ ስፍራ** 9 **ካሬ ሜትር**
- **የመምህራና ሠራተኛ ማንበቢያ ክፍል** 20 **ካሬ ሜትር ይኖሩታል፣**

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተመጻሕፍት ህንፃ ፣ የሠራተኞች ክፍሎችን፣ ማንበቢያ፣ መጻሕፍት ማስቀመጫ ክፍሉች እንዲሁም የት/ቤቱ ተማሪዎች በአግባቡ ማስተናገድ የሚችል ሆኖ መደራጀት አለበት።

የተማሪዎች ብዛት	የቤተመፃህፍት ሠራተኞች ብዛት		የቤተመፃህፍቱ ማንበቢያ ክፍል			ቤተመፃህፍቱ ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ የመጻሕፍት ብዛት	
	የሠለጠነ ባለሙያ	ረዳት ሠራተኛ	የወለሉ ስፋት በአንድ አካባቢ	በአነስተኛ ግምት መቀመጫዎች	የንባብ ክፍሎች	ዓይነት	ብዛት
200-400	1	1	1ካሜ	50	1	500	1,000
401-500	1	1	1ካሜ	60	1	1,200	2,500
501-1200	1	1	1ካሜ	75	1	2,500	5,000
1201-2500	1	1	1ካሜ	100	1	5,000	10,000
2501-3000	2	1	1ካሜ	100	2	7,500	15,000
3000 በላይ	3	2	1ካሜ	100	2	10,000	20,000

4.4.5. የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መከራ ክፍል /ህንፃ/

ለፊዚክስ፣ ለኬሚስትሪና ለባዮሎጂ የሳይንስ ትምህርቶች ልዩ ልዩ ኬሚካሎች፣ አፓራተስና ኢኩፕመንት የሚያገለግሉ ዕቃዎች የሚቀመጡበት ስቶርና መምህሩ ትምህርቱን ከማቅረቡ በፊት ልምምድ የሚያደርግበት የዝግጅት ክፍል እንዲሁም ተማሪዎች የሚለማመዱበት የዲሞኔስትሬሽን ክፍል ያስፈልጋል።

4.4.5.1 የፊዚክስ ላብራቶሪ ክፍል/ ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

ተ.ቁ	ክፍል	መጠን	መግለጫ
1	ዴሞንስትሬሽን ክፍል	17.70×5.85=102.55	
2	ዝግጅት ክፍል	2.40×5.80=13.92	
3	ስቶር	3.30×5.80=19.14	
4	በአጠቃላይ የብሎኩ መጠን	24.44×6.25=152.75	

4.4.5.2 የኬሚስትሪ ላብራቶሪ ክፍል/ ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

ተ.ቁ	ክፍል	መጠን	መግለጫ
1	ዴሞንስትሬሽን ክፍል	17.70×5.85=102.55	
2	ዝግጅት ክፍል	2.40×5.80=13.92	
3	ስቶር	3.30×5.80=19.14	
4	በአጠቃላይ የብሎኩ መጠን	24.44×6.25=152.75	

4.4.5.3 የባዮሎጅ ላባራቶሪ ክፍል ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

ተ.ቁ	ክፍል	መጠን በሜትር	መግለጫ
1	ዴሞንስትሬሽን ክፍል	15.×5.55=87.75	
	ዝግጅት ክፍል	2.4×2.86=6.86	
	ስቶር	3.3.30×2.85=9.4	
	አጠቃላይ የብሎክ መጠን	6×18=108	

4.4.5.4 የሂሳብ ክፍል ብሎክ/ ስፋት በሜትር ካሬ

	ሂሳብ ክፍል		
1	ክፍል	6.92×7.26=50.24	

4.4.5.5 ከሳይንስ ውጪ ለሚሰጡ ትምህርቶች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት ክፍሎች

ከሳይንስ ውጪ ለሆኑ የሶሻል ሳይንስ ትምህርቶች እንደ ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ ኢኮኖሚክስ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣የቴክኒካል ድሮዊንግም ትኩረት ስለሚሰጣቸው ለእነዚህ ትምህርቶች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች የሚቀመጡበት የየራሳቸው ክፍል እንዲኖራቸው ይደረጋል።

ተ ቁ	ክፍል	መጠን በሜትር	መግለጫ
1	አይሲቲ	8×7= 56	ከ9ኛ - 12ኛ
2	የሳትላይት	4×4=16	ከ9ኛ - 12ኛ
3	አይቲ	8×7 =56	ለመሰናዶ ብቻ

4	የቴክኒካል ድሮዊንግ	8x7=56	ለመሰናደ ብቻ

ማሳሰቢያ፣

1/ ከላይ ከ1 እስከ 4 የተጠቀሱት ክፍሎች ብዛት እንደ ተማሪዎች ብዛት ይወሰናል።

2/ በአይሲቲ ክፍል ውስጥ መኖር የሚገባው የኮምፒውተር ብዛት እንደ ተማሪው ብዛት የሚወሰን ይሆናል።

4.4.6 የመሰብሰቢያ አዳራሽ /ብሎክ/

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለመምህራንና ለተማሪዎች መሰብሰቢያ የሚያገለግል መጠኑ 16.25×26.20=425.75 ካሬ ሜትር ስፋት የሆነ አዳራሽ ሊኖረው ይገባል። አዳራሹ የተሟላ ፋሲሊቲ ይኖረዋል።

4.4.7 የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ችሎታቸውንና ዝንባሌያቸውን የሚፈትሹበት አንድ ወርክሾፕ 12 ሜ × ሜ 8»=96 ሜ .ካ እና ስቶር 11 ሜ X 9 ሜ»=99».ካ ሜ ያለው የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ሊኖረው ይገባል።

4.5 ለተለያዩ ክፍሎች አስፈላጊ የሆኑ ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመማሪያ ክፍሎች፣ቤተሙከራ፣ቤተመጽህፍት፣ቢሮዎች፣ የሂሳብ ትምህርት ክፍል ፣የትምህርት ማበልጸጊያ፣ የአይሲቲ ማዕከሎች፣ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ፣ የሰውነት ማጎልመሻ፣ ደረጃቸውን በጠበቁ ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘት አለባቸው።

4.5.1 የመማሪያ ክፍል

ተ.e	መጠን በሴንቲ ሜትር					
	የመማሪያው ዓይነት	ብዛት	ርዝመት	ወርድ	ቁመት	ምርመራ
1	/ወንበርና ጠረጴዛ/	20	55	100	74	በ1 ዴስክ 2 ተማሪዎች የሚያስቀምጥ
2	ጠረጴዛ	1	80	120	74	የመምህሩ
3	ወንበር	1	40	56	78	የመምህሩ
4	አርምቼየር	40	35	35	77	የተማሪው
5.	የጠመኔ ሰሌዳ	–	5	1.20		ለአንድ መማሪያ ክፍል
6.	ማስታወቂያ ሰሌዳ	1	–	1.2	2.20	

4.5.2 የላብራቶሪ ክፍል

ተ.ቁ	የእቃው ዓይነት	ብዛት			መጠን በሴንቲ ሜ.		
		ፊዚክስ	ባዮሎጂ	ኬሚስትሪ	ስፋት	ወርድ	ቁመት
1	በርጩማ ስቱል	42	42	42	32	–	54
2	የመምህሩ ወንበር	1	1	1	40	56	78
3	የመምህር ጠረጴዛ	1	1	1	120	60	75
4	የመምህሩ ዲሞንስትሬሽን ጠረጴዛ	1	1	1	80	220	85
5	የተማሪዎች አግዳሚ ጠረጴዛ	20	20	20	55	110	82
6	ቀምሳጥን፡ - ላይ - ታች	 4 4	 4 4	 4 4	 120 120	 40 60	 110.2 82.2
7	ማሳያ ቁምሳጥን - ላይ - ታች	 1 1	 1 1	 1 1	 120 120	 40 50	 67.7 82.6

4.5.3 የሂሳብ ትምህርት ክፍል ፈርኒቸርና ቁሳቁሶች

ተ.ቁ.	የዕቃው ዓይነት	መጠን በሴንቲ ሜትር			
		ብዛት	ርዝመት	ወርድ	ቁመት
1	ካፕ ቦርድ	1	120	50	200.4
2	ጠመኔ ሰሌዳ	1	240	–	120
3	የግራፍ ሰሌዳ	1	120	–	120
4	ማስታወቂያ ሰሌዳ	1	120	–	120
5	የመምህሩ ወንበር	1	40	56	78
6	የመምህሩ ጠረጴዛ	1	60	120	75
7	የተማሪ ዴስክ	20	110	55	75
8	የተማሪ ወንበር	40	40	56	78
9	ፋይሊንግ ካቢኔት	1	45	60	130

4.5.4 የቢሮ ፈርኒቸርችና ቁሳቁሶች

ተ.ቁ	ዓይነት	መጠን			ርዕሰ መምህር ቢሮ	መምህራን	አስተ. ክፍል	ዕቃ ቤት ግምጃ	ምርመራ
		ስፋት	ወርድ	ቁመት					
1	ባለ መደገፊያ ወንበር	40	56	78	1	-	1	1	
2	ወንበር(መደገፊያ የሌለው)	40	56	78	4	5-20	6	3	
3	የቢሮ ዴስክ ባለ ኪስ	80	160	74	1	-	2	1	
4	የመሰብሰቢያ ጠረጴዛ	80	150	74	1	2-6	1	-	
5	ካኘቦርድ	40	120	100	4	-	6	2	ባለ 9 ተካፋች
6	ካኘቦርድ	40	120	200	-	2–6	2	-	ባለ 9 ተካፋች
7	ፋይል ካብኔት	45	62	135	1	2-6	1	1	ባለ አራት ተካፋች
8	ታይፒስት ወንበር	40	40	77	1	-	1	1	
9	ታይፒስት ዴስክ	50	75	65	1	-	1		
10	ሸልፍ	120	40	200	-	–	2	8	
11	የኮት መስቀያ		–	–	1	3	1	-	የግድግዳ
12	ጠመኔ ሰሌዳ	500	120	–	-	1	-		–
13	ማስታወቂያ ሰሌዳ	120	120	–	2	1	1	1	-
14	ቆሻሻ ማጠራቀሚያ	–	–	–	1	1	1	1	-
15	የፋይል ማቅረቢያ ትሪ	–	–	–	2	-	2	-	
16	ኮምፒውተር	–	–	–	1	–	1	1	
17	ፕሪንተር	–	–	–	1		1		
18	ፎቶ ኮፒ ማሽን	–	–	–	1				

4.5.5 ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያስፈልጉ የሰውነት ማጎልመሻ ስፖርት ትምህርት ቁሳቁሶች

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በቀለም ትምህርት ላይ የተመሰረተ ዕውቀት ብቻ ሳይሆን በአካልና በመንፈስ የዳበረ ዜጋ በማፍራት ላይ ትኩረት ይሰጣል። ተማሪዎች በመደበኛ ክፍለ ጊዜ የቀሰሙትን የንድፈ ሀሳብ ትምህርት በተግባር ለማሳየት የሚከተሉትን የትምህርት መሳሪያዎች ት/ቤቱ አሟልቶ መገኘት አለበት።

ተ ቁ	የመማሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን/ ክብደት	ብዛት	ምርመራ
1	ኳሶች				
1.1	እግር ኳስ	9-12	ቁጥር 5	10	1ለ80 ተማሪዎች
1.2	ቅርጫት ኳስ	9-12	ጁኒየር	6	
1.3	ቅርጫት ኳስ	9-12	ሲኒየር	6	
1.4	የእጅ ኳስ	9-12	መደበኛ ሲኒየር	10	
1.5	የመረብ ኳስ	9-12	መደበኛ ሲኒየር	10	
1.6	ከባድ ኳስ	9-12	4 ኪ.ግ	5	
1.7	ከባድ ኳስ	9-12	5 ኪ.ግ	5	
2	የአትሌቲክ መማሪያዎች				ለ80 ተማሪዎች
2.1	– ጦር	9-12	600 ግራም	5	
2.2	– ጦር	9-12	700 ግራም	5	
2.3	– ዲስከስ	9-12	1.50 ኪ.ግ	4	
2.4	– ዲስከስ	9-12	1.75 ኪ.ግ	4	
2.5	– አሎሎ	9-12	5 ኪ.ግ	4	
2.6	-አሎሎ	9–12	5.5 ኪ..ግ	4	
2.7	የከፍታ ዝላይ ቋሚ በጥንድ	9–12	ከብረት የተሰራ	1	በት/ቤት

ተ ቁ	የመሣሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን/ ክብደት	ብዛት	ምርመራ
2.8	የከፍታ ዝላይ አግዳሚ	9–12		4	
2.9	–የሩጫ ሰዓት መቆጣጠሪያ	9–12	ኤሌክትሮኒክስ	6	
2.10	– የሩጫ ማስነሻ ሽጉጥ	9–12		2	
2.11	የሩጫ ማስነሻ ጥይት/በፖኬት/	9–12		4	4
2.12	– የሩጫ ማስነሻ ሳንቃ	9–12		1	
2.13	– የሪሌይ ቅብብል ላዎች	9–12	30ሣ ርዝመት	8	ከ50 ግራም ያላነሰ ክብድት ካለው እንጨት ወይም ስስ ቧንቧ የተሠራ
3	የጂምናስቲክ መሣሪያዎች	9–12			
3.1	– ቢም	9–12		1	
3.2	– ተደራራቢ ሣጥን	9–12	ባለ 5 ክፍል	1	
3.3	– በክ	9–12		1	
3.4	– የጅምናስቲክ ፈረስ ከነኮርቻው	9–12			
3.5	– ፍራሽ	9–12	1×3 ሜትር	3	
3.6	– ፍራሽ	9–12	1×6 ሜትር	2	
3.7.	–አግዳ ወንበሮች /ቤንች/	9–12		4	
3.8	– አግዳሚ ማዕዘን	9–12	ከብረት ኳንኳ የሚሠራ	2	
3.9	– ነጠላ አግዳሚ ዘንግ	9–12	ከእንጨት የሚሠራ	1	የአገር ውስጥ
3.10	– ጥንድ አግዳሚ ዘንድ	9–12		1	〃 〃
1.11	– መንጠሪያ ሣጥን	9–12		1	〃 〃
3.12	ሌሎች				

ተ ቁ	የመሣሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን/ ክብደት	ብዛት	ምርመራ
3.13	ለመውጣትና ለመውረድ የሚያገለግሉ ገመዶች	9–12	8ሜትር ርዝመትና 7 ሣ.ሜ ውፍረት	5	
3.14	– የመዝለያ ገመድ	9–12	1.50 ሣ ሜ ርዝመት	20	
3.15	ለኢላማ መምታትና ለልዩ ልዩ መጫወቻ ማከናወኛ ኳሶች	9–12	ትናንሽ ካሶች	20	ከኘላስቲክ
3.16	– የመምህሩ ቱታ	9–12	የሀገር ውስጥ	1	በዓመት
3.17	የመምህሩ ታኬታ	9–12		2	
3.18	– ፊሽካ	9–12		2	
3.19	– የኳስ መንፊያ ፓምኘ	9–12		2	
3.20	– የመረብ ኳስ መረብ	9–12		4	የአገር ውስጥ
3.21	የባስኬት ቦል ቋሚ ከነሳንቃውና ከነቀለበቱ በጥንድ	9–12		1	
3.22	– መለኪያ ሜትር	9–12	ባለ 25 ሜትር	1	
3.23	– መለኪያ ሜትር	9–12	ባለ 50 ሜትር	1	
3.24	የስፖርት ሹራብ /ማሊያ/ ከነቁምጣው	9–12		16	
4.1	– የእግር ኳስ ሜዳ	9–12	12×100=12,000	ካሬ. ሜ	የሩጫ መስመሮች ያጠቃልላል
4.2	– የቅርጫት ኳስ ሜዳ	9–12	28×16=448 ካ.ሜ		
4.3	– የእጅ ኳስ ሜዳ	9–12	42×22=924 ካ.ሜ		
4.4	– የመረብ ኳስ ሜዳ	9–12	20×11=220 ካ.ሜ		

ተ ቁ	የመሣሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን/ ክብደት	ብዛት	ምርመራ
4.5	– የከፍታና የቢዝመት መዝለያ	9–12	20×15=420 ካ.ሜ		

4.5.6 **ለመማር ማስተማር ሂደት ድጋፍ ሰጪ የሆኑ ልዩ ልዩ አገልግሎት መሰጫ ክፍሎች የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች**

4.5.6.1 **ቤተ መጽሀፍት**

- **በቤተመጽሃፍት የሚገኙ የማዳመጫና የእይታ /የመስሚያና የማያ/መሣሪያዎች፣**
  - **በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጠው ትምህርት በተግባር የተደገፈ እንዲሆን ቤተመጻሕፍቶቹ የሚከተሉትን የማዳመጫና የእይታ መሳሪያዎች አሟልተው መገኘት አለባቸው፡**

ዓይነት	**መግለጫ**
አትላስ	የካርታ መጻሕፈት
ሥዕሎች	ፎቶግራፎች ያጠቃልላል
ቻርቶች	ልዩ ልዩ አሃዛዊ መግለጫዎች የተመለከተ
ግሎቦች	ፊዚካል፤ ፖለቲካል . . . ወዘተ
ካርታዎች	በዓለም ፣በአህጉር፤ በሪጅ፤ በሀገር
ጥቅል የፎቶግራፍ ፊልሞች	ጂኦግራፊ፤ ሣይንስ ትም/ዓይነቶች ቋንቋ. . ወዘተ
ስላይድ የፎቶግራፍ ፊልሞች ባለ ድምጽና ድምጽ የሌላቸው ተንቀሳቃሽ ፊልሞች	የጂኦግራፊ ፤ ሣይንስ ትም/ዓይነቶች

ቴኘ ሪኮርድ	
የባህል መሣሪያዎች	የቴክኖሎጂ የአለባበስና ቅርሳ ቅርስ ስብስብ ያጠቃልላል

በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚቋቋም ቤተ መፅሐፍት የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል።

- ወቅታዊ መጽሃፍት በተለያየ መንገድ በማሰባሰብ ለአከባቢውና ለት/ቤቱ ማህበረሰብ በማቅረብ የንባብ ፍላጐትን ማዳበር፤
- ለትምህርት አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍትን በጥራትና በዓይነት በማቅረብ የተማሪዎችና የመምህራንን ዕውቀት ማበልጸግ፣
- ማንኛውንም የጥናትና ምርመራ ሥራዎችን ለማካሄድ በምንጭነት ማገልገል፤
- የመጻሕፍትና የቤተመጻሕፍት አጠቃቀም ዘዴዎችን ለማስተማር፤
- ትርፍ ጊዜን በንባብ ለማሳለፍ::
- ለተማሪና ለመምህራን ተጨማሪ ዕውቀት የሚሰጡ መፅሐፍት (Supplementary books) በጥራትና በዓይነት ለማቅረብ፣
- ክግል ሀሳብ ይልቅ የጋራ አስተሳሰብን የሚያጐለብቱ ከጥላቻና ከአድሎአዊነት ይልቅ ትክክለኛ ምክንያቶችን የሚያስቀድሙ መፅሐፍት መርጦ በማቅረብ የህብረተሰብን ፍላጎትና አመለካከትን ማዳበር፣

- **በ2ኛ ደረጃ በት/ቤት ውስጥ የሚቋቋም ቤተመጻሕፍት የሚከተሉትን ነጥቦች ማካተት አለበት።**
  - የሚቋቋመው ቤተመጽህፍት በአንድ አማካይና ምቹ ቦታ ማደራጀት፣
  - ፀጥታና በቂ ብርሃን እንዲሁም ሰፊ የማንበቢያ ቦታ ያለው፣
  - የመጻሕፍት ብዛትና ዓይነቶችም እንደ ትምህርት ዓይነቶችና ተማሪዎች ቁጥር ከፍ ያለ መሆን፣
  - ቤተመጻሕፍት ተማሪዎችና መምህራን በሚያመቻቸው ሰዓት ማንበብ እንዲችሉ ክፍት እንዲሆን ማድረግ፣
  - ለዚሁም ሥራውን የሚመራዉ ተማሪውን ከቤተመጻሕፍት ሥርዓት ጋር የሚያስተዋውቅ በሙያው የሰለጠነና ለሥራው ተመጣጣኝ የሰው ኃይል መኖር አለበት::

- **አንድ ስታንዳርዱን የጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ቤተመጽሕፍት የሚከተሉትን ዋና ዋና ፈርኒቸሮችና ቁሳቁሶች ተሟልተው መገኘት አለባቸው።**

ተ.ቁ	ዓይነት	ብዛት	መጠን በሴንቲ.ሜ/	መግለጫ
	ኮምፒዩተር	5		አንድ ኮምፒዩተር ለጽህፈት ቤቱ
1	መቀስ	2		መካከለኛ
2	የቀን መቁጠሪያ ማኅተም	1		
3	የቤተ መፃሕፍት ማኅተም	1		
4	ስቴፕለር	2		
5	የማኅተም መርገጫ	1		
6	ዴት ዱዬ ካርድ	-		
7	ማዋሻ ካርድ	-		
8	መቆጣጠሪያ ካርድ	-		
9	የመፃሕፍት ካርድ	-		
10	የመፃሕፍት መደገፊያዎች	100	13x10	
11	ማንበቢያ ጠረጴዛ	16	80x150x74	
12	ወንበር	80	35x35x77	
13	የካርድ ሣጥን	1	52x44x44	ባለ 12 መሳቢያ
14	የኃላፊው ጠረጴዛ	1	80x162x74	
15	የመጽሐፍት ማጓጓዣ ጋሪ	1	60x100x80	
16	የኃላፊው ወንበር	1	40x56x78	
17	የጋዜጣ መደርደሪያ	1	-	
18	የመጻሕፍት መደርደሪያ	1	95×40×105	
19	የመጻሕፍት ሸልፍ	1	120×40×200	
20	ጠመኔ ሰሌዳ	1	500×120	
21	ማስታወቂያ ሰሌዳ	1	120×120	
22	የግድግዳ ሰዓት	1		
23	ጠረጴዛ	1		

ተ.ቁ	ዓይነት	ብዛት	መጠን በሴንቲ.ሜ/	መግለጫ
24	ፋይል ካቢኔት	1	45×62×35	
25	የጠረጴ ደወል	1		
26	ኮምፒውተር	1	–	–

ማሳሰቢያ፣

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ የተካቱት የቤተመጻሕፍት ግብአቶች በዝቅተኛ መጠን የተቀመጡ ሲሆን በትምህርት ቤት ያሉ ተማሪዎች ቁጥር ሲጨምር ግብአቶቹም በዛው ልክ ይጨምራሉ።

4.5.7 <u>የICT ማዕከል</u>

ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት መማሪያ ክፍል በተጨማሪ ከትምህርታቸው ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ማግኘት የሚያስችላቸው የICT ማዕከል (የኢንተርኔት አገልግሎት ማዕከል) ሊኖራቸው ይገባል።እስከ 1500 ተማሪዎች ላሉት ት/ቤት በአንድ ጊዜ 40 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችል አንድ ማዕከል ሊኖረው ይገባል።ነገር ግን የተማሪዎች ብዛት በጨመረ ቁጥር የICT ማዕከል ብዛትም በዚሁ ስሌት መሰረት ይጨምራል። የኮምፒውተር ብዛትም ለአንድና ተማሪ አንድ መሆን ይኖርበታል።

4.5.8 የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል

በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ደረጃውን ጠብቆ ተጨባጭ የሆነ ትምህርት እንዲሆን በትምህርት መርጃ መሳሪያዎች መደገፍ አለበት።እነዚህን መሳሪያዎች ገዝቶ ለሚሟላት የትምህርት ቤቱ አቅም ስለማይፈቅድ እነዚህ መሳሪያዎች በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች መሰራት ስላለባቸው ይህንኑ ለማሟላት የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ።በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚገባ መደራጀት አለባቸው።

ከዚህ አኳያ የመማር ማስተማሩን ሂደት ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ለተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የሚያስፈልጉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በተፈለገው ዓይነትና

ጥራት እንዲሁም ብዛት ለማዘጋጀትና ለሚሚላት የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት የሚከተሉት ዕቃዎችና መሳሪያዎች ሊሚሉላቸው ይገባል

4.5.8.1 የቢሮ ዕቃዎች

የዕቃው ዓይነት	ብዛት
ወንበር	3
ጠረጴዛ	3
መደርደሪያ ለመሳሪያዎች	1
መደርደሪያ ለዕቃዎች	1
ጠመኔ ሰሌዳ	1
የእንጨት መሥሪያ ቤንች	2
የብረት መሥሪያ ቤንች	2
የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ	1

4.5.8.2 የእጅ መሣሪያዎች

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	መግለጫ
1	ስክሩ ድራቨር	2	
2	አግድም ቆራጨ መጋዝ	2	
3	የብረት መቁረጫ መጋዝ	2	
4	መላጊያ ትልቁ	2	
5	መላጊያ ትንሹ	2	
6	ተጠቅላይ ሜትር	2	ባለ3 ሜትር
7	ቲ–ስኳር	2	
8	ትራይ ስኳር	2	
9	ድሮዊንግ ኢንስትሩመንት	8	
10	ኘሮትራክተር	2	
11	ትራንግል ሄቪ ፕላስቲክ	4	30፣60፣90
12	ትራንግል ሄቪ ፕላስቲክ	4	45፣90
13	የብረት መሰርሰሪያ	2	
14	የእንጨት መሰርሰሪያ	2	
15	የእንጨት ሞረድ	4	
16	የወረቀት መቁረጫ	2	61×51 ሳ.ሜ ተለቀ

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	መግለጫ
17	ትልቁ የብረት መሳሪያ ሞርሣ	2	
18	ትንሽ የእንጨት መሳሪያ ሞርሣ	2	
19	የብረት መሞረጃ ሞረድ	4	
20	ግራይንደር ቤንች ታይኘ	2	
21	የእንጨት መሮ	2	
22	ሲክላምኘ	4	
23	ፒንሣ	2	
24	መዶሻ	2	
25	ጋሪ	2	
26	አካፋ	2	
27	ዶማ	2	
28	ውሃ ማጠጫ	2	

4.5.9 የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ

- ተማሪዎች ካላቸው የአካልና የስሜት ማደግ ባህሪያቸው የተነሣ በተለያዩ መንገዶች ለበሽታና ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ።
- ክእነዚህም፣
  - በጨዋታ ሜዳ ላይ እንዲሁም በሥራ ቦታዎች የወለምታ ፤ የስብራት፤ የመቁሰልና የመድማት ፤ የእባብ የመነደፍና በውሻ የመነከስ፤ በስለት ነገር የመቆረጥና የመወጋት፤
  - በልዩ ልዩ ሕመሞች ምክንያት/ በስኳር በሽታ፣ በሚጥል በሽታ/ አእምሯቸውን የመሳት፤ በውኃ የመስመጥና የመታፈን ሁኔታዎች
  - ቆሻሻ ውኃ በመጠጣት የተቅማጥና የተውከት ችግር በተለያየ ምክንያት የደም መመረዝና ትንፋሽ የማጠር ሁኔታዎች ናቻው ።

ከላይ የተጠቀሱት ችግሮችን ለመቅረፍ የሕክምና እርዳታ የሚሰሩና በአጠቃላይ በጤና አጠባበቅ /sanitation & hygine/ ላይ ትምህርት የሚሰጥ የጤና ባለሙያ በትምህርት ቤቱ ይመደባል። በአቅራቢያው የጤና አገልግሎት ቢኖርም እንኳን እቦታው እስኪደርስ ድረስ በሽተኛው ሊጎዳ ስለሚችል የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል ትምህርት ቤቱ ሊኖረው ይገባል።

በትምህርት ቤቱ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጫ ሣጥን (first Aid kit) **ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው የሕክምና መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው ::**

1 Adhesive plaster 5cm x10mrollS
2 12 vow gauze bandage 8 cm×5m rols
3 dissecting forceps
4 Examination gloves
5 1 bottle of Dettol 250 ml
6 Scissors 14 cm Gc.P
7 Elastic bandage 10 cmx4.5m
8 2 elastic woven bandage 8 cm×5m
9 12 vow gauze bandage 7 5 cm×5m
10 4 triangular bandages
11 Cotton wool 400 gm
12 1 pack hand plaster **ናቸው**
13 **የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ሳጥን**
14 **እስትሬቸር /አንድ እስትሬቸር ለ**100 **ተማሪዎች ስሌት**

4.5.10 *መዝናኛ ክበብ*

4.5.10.1 የመምህራንና ሠራተኞች መዝናኛ ክበብ

መምህራንና ሠራተኞች ጠዋትና ከሠዓት በኋላ ባለው የእረፍት ሠዓት እንዲሁም በምሳ ሰዓትና በቀን ውስጥ ባለው ሌላ የእረፍት ጊዜያቸው ሻይ፣ቡና፣ ለስላሳ፣ ቁርስና ምሳ እንዲሁም ራሳቸውን ዘና የሚያደርጉበት መዝናኛ ክበብ በት/ቤቱ ሊኖር ይገባዋል። ክበቡ በአንድ ጊዜ ሁሉንም መምህራንና ሠራተኞች ሊያስተናግድ የሚችልና ለእንግዶች ሊሆን የሚችል ተጨማሪ ወንበሮችና ጠረጳዛዎችን የያዘና በዋነኛነት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት።

1. 25 **ኢንች ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቴሌቪዥን**
2. **ሲዲ ማጫወቻና ሊያዝናኑ የሚችሉ ሲዲ ወይም የቪዲዮ ካሴቶች፣**
3. *መጠነኛ* **የሆነ የሳተላይት ዲሽ፣**
4. **አንድ ኢንተርኔት ኔትወርክድ የሆነ ኮምፒዩተር፣ /እንደ አስፈላጊነቱ በመምህራንና ሠራተኞች ቁጥር የሚወሰን/**
5. **የቤት ውስጥ** *መጫዎቻዎች*፣

- ዳማ
- ቼዝ
- የጠረጴዛ ቴንስ መጫወቻ እና
- ሌሎች የቤት ውስጥ (Indoor games)

6. ፍሪጅ
7. ለሻይ ለቡና ለምግብ ማዘጋጃ ሊሆኑ የሚችሉ ቁሳቁሶች
8. እንደ አየሩ ጠባይ ታይቶ ኤርኮዲሽነርና ማሞቂያ ማሽን (Heater)

4.5.10.2 የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ

ተማሪዎች እንደ መምህራንና ሠራተኞች ባላቸው ትርፍ ሰዓት የሻይ፣ ቡና፣ለስላሳ ቀለል ያሉ የምግብ ዓይነቶች የሚዘጋጁበትና ራሳቸውን ዘና የሚያደርጉበት ቢያንስ በአንድ ጊዜ አብዛኛውን የተማሪ ቁጥር ሊያስተናግድ የሚችል የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ሊኖር ይገባል። ክበቡ በዋነኛነት የሚከተሉት ሊኖሩት ይገባል።

1. 25 ኢንች ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ቴሌቭዥን
2. መጠነኛ የሆነ ሳተላይት ዲሽ
3. የጠረጴዛ ቴንስ መጫወቻና ሌሎች የቤት ውስጥ መጫዎቻዎች(indoor games)

4. 5 .11 የአዳራሽ አጠቃቀም

- እንደ አስፈላጊነቱ ተማሪዎች፣ መምህራንና የአካባቢው ኅብረተሰብ እየተገናኙ ስለ ትምህርቱ ሂደትና ስለ ት/ቤቱ ዕድገትና መሻሻል የሚወያዩበት መድረክ ፤
- የክፍል ውስጥ ትምህርትን የሚያዳብሩ እንደ፣
  - የጥያቄና መልስ ውድድሮች
  - የተማሪዎች የፈጠራ ሥራዎች ኤግዚቢሽኖች፤
  - የሥነጽሑፍ ፤ ድራማና ሙዚቃ ዝግጅቶች፤
  - ክርክር፤ ውይይት ሲምፖዚየምና የተጋባዥ እንግዶች ንግግር
  - ከአካባቢ እስከ ዓለም አቀፍ ደረጃ በሚታዩ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ፤ ፖለቲካዊ ፤ባህላዊና ተፈጥሮአዊ ክስተቶችና ወቅታዊ ጉዳዩች ላይ ተማሪዎች ግንዛቤ እንዲጨብጡና ለችግሮች መፍትሔ እንዲፈልጉ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች የሚዘጋጁበት መሆን አለበት።
- በአጠቃላይ አዳራሹ በከፍተኛ ወጪ የተሠራ በመሆኑ ለመማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በሚሰጥ መንገድ አገልግሎት ላይ ሊውል ይገባል።

4.6 ለየትምህርት ዓይነቱ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት አሳታፊና ተማሪ ተኮር እንዲሆን የትምህርት መሣሪያዎች በዓይነትም ሆነ በብዛት መገኘት ለትምህርት ጥራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ተማሪዎች በንድፈ ሀሳብ የተማሩትን ትምህርት በተግባር ማለትም የትምህርት መሳሪያዎችን በመዳሰስ፣ በመፈተሽና በመለካት ከተማሩ ትምህርቱን በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። በመሆኑም በፋብሪካ የተመረቱ የትምህርት መሳሪያዎች ተገዝተው ወይም ይህ በማይገኝበት ወቅት መምህራንና ተማሪዎች በትምህርት ማዕከላት ተገኝተው በመስራት ማቅረብ አለባቸው።

በአንዳንድ የትምህርት ዓይነቶች በፋብሪካ ተሠርተው በገበያ ላይ የሚገኙ የትምህርት መሣሪያዎች ዝርዝር በአባሪነት ተያይዟል።

4.6.1 ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች

ማየት ለተሳናቸው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- የብሬል ወረቀት
- ስሌትና ስታይልስ
- በብሬል የተጻፈ የመደበኛ ትምህርት መጽሐፍ ኮፒ
- አባከስ
- ቴሪኮርደርና ካሴት
- የታይኘ መኪናና የቴኘሪኮርደር መለዋወጫ
- ነጭ ብትር/ዘንግ
- ማየት የተሳናቸው ለንባብ የሚረዱበት መሣሪያ /

መጠነኛ የዕይታ ችግር ላለባቸው

- በቅርበት የሚያሳይ ቴሌቪዥን
- አቮርሄድ ኘሮጀክተር
- ትላልቅ ስፒል
- ባለ ትልቅ መስመር ወረቀት
- አጉሊ መነጽር
- ለማንበቢያ የሚረዳ

- የታይኘ መኪናና ቴኘሪከርደር

መስማት ለተሳናቸው

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሣያ መሣሪያ፡
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያለ ነገር እንዲታይ ማድረግ በከፊል ለሚሰሙት ድምጽ አጉሊ መሣሪያ መጠቀም ለምሳሌ ረዳት የመስሚያ መሣሪያ፡
- የታይኘ መኪና፡

መጠነኛ የእይታ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎች

- የዕይታ መሣሪያዎች፤ ብርሃን አስተላለፊ ወረቀት ፊልሞች ካብሽን፤ ስላይድ ፊልሞችና ቻርት ለማሳያ አስፈላጊ ናቸው ::

4.7. የተማሪ መፅሐፍት ጥምርታ

– የተማሪ መጽሃፍት ተሚልቶ መገኘት ለትምህርቱ ጥራት እጅግ ወሳኝ ሚና አለው። በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የተማሪ መፅሃፍ ጥምርታ አንድ ለአንድ መሆን አለበት።

4.8. የተማሪ ክፍል ጥምርታ

– የተማሪ ክፍል ጥምርታ ለትምህርት ጥራት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ከ9ኛ –12ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በአንድ ክፍል 40 /1:40/ ይመደባሉ።

4.9. የሰው ኃይል ምደባ

– የትምህርት ሥራ በጥራትና በተፈለገው መንገድ ሊካሄድ የሚችለው ት/ቤቱ በየትምህርት ዓይነቱ የሚሰጡ ትምህርቶች ለደረጃው የሰለጠኑ መምህራን እንዲሁም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በጥራትና በበቂ ሁኔታ አሚልቶ ሲገኝ ነው። ስለሆነም

– በ2ኛ ደረጃ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ሳይክል የሚመደቡ መምህራን ዲግሪ ያላቸው ሆነው የማስተማር ሥራ ፈቃድ የተሰጣቸው ይሆናሉ።

– አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለሚከተሉት መሰረታዊ የሥራ መደቦች ብቁ መምህራንና ሠራተኞች ሊኖረው ይገባል።

4.9.1 **የመምህራንና ሠራተኞች ተፈላጊ የትምህርት ደረጃ**

ተ.ቁ	የሥራው መስክ	ብዛት	ለሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የትምህርት ደረጃ		
			1ኛ ሳይክል /ከ9ኛ-10ኛ/	2ኛ ሳይክል /11-12/	ምርመራ
1	ርዕሰ መምህር	1	ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ	ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ	ከሰለጠኑበት ትምህርት በአንዱ በትምህርት አስተዳደር ሆኖ የርዕ መም/ |ሥልጠና የወሰደ/ች
2	ምክትል ርዕሰ መምህር	1	ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ	ኤም.ኤ/ኤምኤስሲ	ከሰለጠኑበት ትምህርት በአንዱ በትምህርት አስተዳደር ሆኖ የርዕ መም/ |ሥልጠና የወሰደ/ች
3	መምህር		ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ	ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ	እንደ የክፍሉ ብዛት የሚታይ ሆኖ ከሳይንስና ከሂሳብ ት/ም/ውጪ
4	መምህር		ቢኤ/ቢኤስሲ/	ኤምኤስሲ	ለሳይንስና ለሂሳብ ትምህርት አይነቶች
5	ዩኒት መሪ	2	ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ	ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ	እንደ ተማሪው ብዛት የሚታይ
6	የካውንስሊንግ ባለሙያ	1	ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ	ቢ.ኤ/ቢ.ኤስሲ	በትምህርት ሳይኮሎጂ የተመረቀ/ ች
7	አስተዳዳርና ፋይናንስ	1	ቢኤ	ቢኤ	በትምህርት አስተዳደር ወይም በማኔጅመንት የሰለጠነ/ች
8	ሂሳብ ሠራተኛ;	1	ዲፕሎማ	ዲፕሎማ	በሂሳብ አያያዝ የተመረቀ//ች
9	ገንዘብ ያዝ	1	ዲፕሎማ	ዲፕሎማ	በሂሳብ አያያዝ የሰለጠነ/ች
10	ንብረት ክፍል ኃላፊ	1	ዲፕሎማ	ዲፕሎማ	በንብረት ኣያያዝ የሰለጠነ/ች
11	ፀሐፊ	1	ዲፕሎማ	ዲፕሎማ	በሴክሬታሪያት ሳይንስ

ተ.ቁ	የሥራው መስክ	ብዛት	ለሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የትምህርት ደረጃ		
			1ኛ ሳይክል /ከ9ኛ-10ኛ/	2ኛ ሳይክል /11-12/	ምርመራ
					የሰለጠነ/ች
12	የተማሪዎች መዘከር ኃላፊ	1	ዲፕሎማ	ዲፕሎማ	በመዝገብ አያያዝ የሰለጠነ/ች
13	የቤተ መጻሕፈትኃላፊ	1	ቢኤቢኤስሲ	ቢኤቢኤስሲ	በላይብረሪ ሳይንስ የሰለጠነ/ች
14	የላብራቶሪ ቴክኒሻን	1	ቢኤ/ቢኤስሲ	ቢኤ/ቢኤስሲ	በሳይንስ ትምህርት የሰለጠነ/ች
15	ጽዳት ሠራተኛ	1	8ኛ	8ኛ	የ8ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ/ች
16	የጥበቃ ሠራተኛ	4	8ኛ	8ኛ	የ8ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቀ/ች
17	ተላላኪ	1	8ኛ	8ኛ	እንደ ተማሪውና ክፍሉ ብዛት የሚወሰን
18	አትክልተኛ	1	8ኛ	8ኛ	እንደ ተማሪውና ክፍሉ ብዛት የሚወሰን
19	የጤና ባለሙያ	1		ዲፕሎማ	እንደተማው ብዛት የሚጨመር ይሆናል

4.9.2 የልዩ ትምህርት መምህራንና ሠራተኞች ድልድል

1.መምህር----------በዲግሪ የተመረቀ/ችና የልዩ ትም/ሥልጠና የወሰደ/ች

2. የንግግር ወጌሻ----------ከከፍተኛ ትም/ተቋም በዲፕሎማ የተመረቀ/ችና የልዩ ትም/ሥልጠና የወሰደ/ች

በመደበኛ ት/ቤት የመምህራንና ሠራተኞች ድልድል እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ከ10–20 ለሚሆኑት ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት ለሚከፈት ልዩ ክፍል የሚያስፈልገው ተጨማሪ የሰው ኃይል እንደሚከተለው ይሆናል ::

- ማየት ለተሳናቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ ልዩ መምህር፤
- መስማት ለተሳናቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ መምህር፤

- የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ህጻናት አንድ መምህር፤
- የስሜት መረበሽ ላጋጠማቸው አንድ ልዩ መምህርና የሳይኮሎጂስት ባለሙያ ፤
- የመማር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህር
- የመናገር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህር ወይም የአንደበት ወጌሻ
- የአካል ጉድለት ላለባቸው አንድ ረዳት መምህር
- ተደራራቢ ችግር ላለባቸው ህጻናት እንደ ሁኔታው ታይቶ የሰው ኃይል ይመደባል። ለምሳሌ አንድ ሕፃን የመስማትና የማየት ጥምር ችግር ካለበት የሰው ኃይል ምደባው አንድ ባለሙያ ለአንድ ወይም ለሁለት ሕፃን ይሆናል።
- ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ሕፃናት የሚመደበው ባለሙያ እንደ ሕፃናቱ የአእምሮ ችሎታና ልዩ ተሰጥኦ ሁኔታ ይለያያል። ለምሳሌ አንድ ሕፃን በሂሣብ ትምህርት ወይም በሥዕል ከሌሎች ሕፃናት በጣም የመጠቀ ችሎታ ካለው በዚህ ትምህርት እንዲገፋበት የሚመለከተውና ችሎታ ያለው መምህር ተመድቦለት እንዲከታተለውና እንዲያበረታታው ይደረጋል
- ልዩ ፍላጎቶች ያሏቸው ሕፃናትና ወጣቶች ከሌሎች መደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ በሚደረግበት ጊዜ የተለየ ክህሎት እንዲያገኙ፣ ለማድረግ ከመደበኛ ክፍሎችና የትምህርት ጊዜ ውጪ በልዩ ፕሮግራም / Unit / በልዩ መምህራንና ባለሙያዎች ይረዳሉ።

5. የማስተማሪያ ዘዴ

የማስተማር ዘዴዎች የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት አቀባበልና አፈፃፀም እንዲሁም የመረዳት ግንዛቤ መሠረት ያደረገ መሆን ስለሚገባው መምህሩ የተማሪውን ዕውቀትና የመረዳት ችሎታ መሰረት ያደረገና ተማሪው ነፃ ሆኖ የመጠየቅና የመመለስ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያስችለውን የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም አለበት። ስለሆነም መምህሩ የሚጠቀመው የማስተማሪያ ዘዴ በዋነኛነት ተማሪውን ማዕከል ያደረገ (studnt centered) ሊሆን ስለሚገባው የሚከተሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች መጠቀምና ማጎልበት ይኖርበታል።

1. የጥያቄና መልስ (Question and Answer)
2. ውይይት (Group Discussion)
3. ስዕላዊ ማብራያ (Illustration)
5/ የሚና ጨዋታ (Role playing)
6/ እንግዳ መጋበዝ Guest Invitation
7/ ፕሮጀክት ሥራ Project Work
8/ simulation መስሎ መጫወት

4. የአንድ ጉዳይ ጥናት (Case Study) 9/ ወዘተ

ከላይ የተጠቀሱትንና ተዛማጅ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ውጤታማ ለማድረግ መምህሩ ተማሪዎች በነፃነት በመማር ማስተማር ስራው እንድ አካል እንደሆኑ ለማሳወቅ እንዲሁም ንቁና ብቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የራሱን ተነሳሽነትና ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

6. የሁለተኛ ደረጃ መምህር ፕሮፋይል

- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ስለሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት፣የክፍል ውስጥ አመራርና የመማር ማስተማር ሂደት አያያዝ፣የተከታታይ ምዘናና ግምገማ አፈጻጸም፣በትምህርት ዙሪያ ጥናትና ምርምር በማካሄድና ችግር ለመፍታት አዳዲስ ሀሳቦችን በማፍለቅ፣ ከትምህርት ቤቱና ከአከባቢ ህብረተሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ያደርጋል፣
- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን በተማሪዎቻቸው መካከል ሊኖሩ ስለሚችሉ ልዩነቶች ማለትም የትምህርት አቀባበል ችሎታና ፍላጎት በመገንዘብና ሳይንሳዊ የአቀራረብ ዘዴዎችን በመጠቀም ተማሪዎችን ለጥሩ ውጤት ያበቃል፣
- በፆታ፣በዘር፣በኃይማኖት እንዲሁም በአካል ጉዳት ወይም በችሎታ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ለተማሪዎች ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት፣ የትምህርት ፍትሃዊነት ያረጋግጣል።
- በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ከአካባቢያዊ፣ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበ ትምህርት በመስጠት የሚገኝ ዕውቀትና ችሎታ ኖሮት ተማሪዎችን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በደረጃቸው ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላል።

6.1 ከሁለተኛ ደረጃ መምህር የሚጠበቅ ባህሪ

- የሁለተኛ ደረጃ መምህርነትን ሙያ የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር የመፍጠርና የማዳበር፣ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በጋራ የማቀድ፣የመስራት፣ችግሮችን በጋራ የመፍታት፣ ሙያውን የማሳደግ፣በህብረተሰቡ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግና ኃላፊነትን ይሸከማል፣
- በክፍል ውስጥ ገዋን ሁልጊዜ ለብሶ መገኘት ይኖርበታል።
- ህገመንግሰቱን የማክበር፣ የዲሞክራሲ መርሆዎችን የመተግበር፣ ሴት ተማሪዎችን የመደገፍና የማበረታታት ባህል ማዳበር፣

- በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች የመልካም ሥነ ምግባር ቀዳሚ አርአያ ሆኖ ይገኛል።
- ለት/ቤቱና ለሚኖርበት ማኅበረሰብ መልካም አርአያ ሆኖ ይገኛል።
- በክፍል ውስጥ የመማር ሂደት በሚካሄድበት ወቅት ሞባይልና ሌሎች አዋኪ የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎች ከመጠቀም ይቆጠባል ።

7. **የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ባህሪ**

➢ **የሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ** (9-10)

- በአካልና በአእምሮ ብስለት ለሥራ ብቁ ነው፣
- ራሱንና አከባቢውን ከማህበራዊ ጠንቆችና ጎጂ ባህሎች ለመከላከል የሚያስችል ዝግጅት አለው።
- መብቱን ለመጠበቅና ግዴታውን ለመወጣት ዝግጁ ነው።
- አዳዲስ ማሽኖችና መሣሪያዎችን ለማንቀሰቀስና ለመጠቀም የሚያስችል መሰረታዊ ዕውቀት አለው።
- መደበኛና መደበኛ ባልሆነ ትምህርት አማካይነት የዳበረ የተግባርና የንድፈ ሃሳብ ዕውቀቶች ለማግኘት ዝግጁ ነው።
- በት/ቤቱ ቅጥር ግቢ የት/ቤቱን ዩኒፎርም ለብሶ መገኘት ይገባዋል።

➢ **የሁለተኛ ደረጃ የቀለም ትምህርትን ያጠናቀቀ ተማሪ** (11-12)፣

- ኃላፊነትን በሚጠይቁ ሥራዎች ለመሰማራትና የከፍተኛ ትምህርት ለመከታተል የሚያስችል ዝግጅት አለው።
- አጫጭር ሥልጠናዎች ከተሰጠው በማንኛውም የሥራ መስክ ተሰማርቶ መስራት ይችላል።
- ህጋዊ ለሆኑ ጉዳዮች የውክልና ኃላፊነት የመሸከምና በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በሚደረጉ ሕጋዊ ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ ብቃት አለው።

- በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ የትምህርት ቤቱን ዩኒፎርም ለብሶ መገኘት ይገባዋል።
- በክፍል ውስጥ ሞባይልና ሌሎች የመማር ማስተማሩን ሂደት ሊያውኩ የሚችሉ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን ከመጠቀም ይቆጠባል።

8. **የማስተማር መማር ሂደት መመሪያዎችና ስነዶች**

- የሥ/ትምህርት ማዕቀፍ፣
- ሥርዓተ ትምህርት፣
- የመምህሩ መምሪያዎችና ማስተማሪያ መጻሕፍት በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የክፍለ ጊዜ ስርጭት፣
- የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል መመሪያ፣
- የዘመኑ የትምህርት ካሌንደር፣
- የቤተ ሙከራ አደረጃጀት፣ አያያዝና አጠቃቀም ማኑዋል።

8.1 **የትምህርት አመራርና አስተዳደር መመሪያዎች አጠቃላይ መመሪያዎች**

- ስርአተ ትምህርት ማዕቀፍ፣
- የየትምህርት ዓይነት፣
- የመምህሩ መምሪያዎችና መረጃ መፅሐፍት በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የተማሪው መፅሐፍ በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- በመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም፣
- ት/ቤትን መሠረት ያደረገ አመራር መመሪያ፣

(school Based Management Manual)

- የተማሪዎች ካውንስል አደረጃጀት መመሪያ፣
- የተጓዳኝ ትምህርት አደረጃጀት መመሪያ፣
- በመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁት እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪም
  - የልዩ ፍላጎት ትምህርት መርሀ ግብር እስትራቴጂ።

ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያዎች

- የአጠቃላይ ትምህርት አመራር አደረጃጀትና የህብረተሰብ ተሳትፎ የፋይናንስ መመሪያ(Blue Book)፣
- አጠቃላይ የትምህርትና የስልጠና ፖሊሲ፣

- የአርብቶ አደር አካባቢ ትምህርት እስትራቴጂ፣
- ስለግል የትምህርት ተቃሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብና ማብራሪያ፣
- አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት፣
- የማዕከልና የክልል አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 41/85፣
- የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል መመሪያ(ቀድሞ የተዘጋጀው)፣
- የትምህርት ቤቶች ተጨማሪ በጀት መመሪያ(School Grant Manual)፣
- አገር አቀፍ የሴቶች ትምህርት እስትራቴጂ፣
- የመምህራን ልማት ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የትምህርት ቤት መሻሻል ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣
- የስነዜጋና ስነምግባር ትምህርት ፕሮግራም መመሪያዎች፣
- የትምህርት ህግ።

9. የሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት

ዓላማ፡

- በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል (9-10) የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎች ባላቸው ፍላጎትና ችሎታ መሰረት ዕውቀታቸውና ክህሎታቸው በማዳበር ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ ማዘጋጀት፣
- የሁለተኛ ደረጃ 2ኛ ሳይክል (11-12) የሚሰጠው ትምህርት ተማሪዎች በመረጡት የትምህርት መስክ ለከፍተኛ ትምህርት የሚያበቃቸውን በቂ ችሎታና ክህሎት እንዲጨብጡ ለማስቻል።

በሁለተኛ ደረጃ የሚሰጠው የትምህርት ፕሮግራም የሚከተሉትን ነጥቦች ሊያካትት ይችላል።

1. የትምህርት ኘሮግራም እርዝመት፣
2. የአየር ፀባዩ / ክረምት/፣
3. ብሔራዊ በዓሎች፣
4. የትምህርት ዓይነቶች ብዛት፤
5. የሲለበስ ስፋት፣

6. በቀን ውስጥ የሚመደበው የትምህርት ሰዓት ርዝመት፡፡

በዚህ መሰረት፣

- ትምህርት የሚሰጠው በሙሉ ቀን ፕሮግራም ነው፡፡
- በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት ከ203-206 ባሉት ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ታስቦ የተዘጋጀ ነው የትምህርቱም ወቅት በዓመት ውስጥ በሁለት ሴሚስተር ወይም በሶስት ተርም ተከፍሎ ይሰጣል፡፡
- በሳምንት አምስት የማስተማሪያ ቀናት ይኖራሉ..'.
- በቀን ውስጥ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ሰባት ነው፡፡ የክፍለ ጊዜ ርዝማኔም 45 ደቂቃ ይሆናል፡፡
- በመጀመሪያው ሳይክል አጠቃላይ ትምህርት ይሰጣል
- በሁለተኛው ሳይክል የሚሠጠው ትምህርት በስፔሻላዜሽን ነው

የሙሉ ቀን ኘሮግራም መደራጀት አስፈላጊነት –

- ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት የሚመጣበትን የቦታው ርቀት እየታየ የእለቱን ትምህርት የመጀመሪያውና የመጨረሻ ጊዜ እንደ አመቺነቱ መወሰን ያስችላል፡፡
- በቀን ትምህርት ኘሮግራም እስከ ሰባት ክፍለ ጊዜ መስጠት ያስችላል፡፡
- የያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ ከ40–45 ደቂቃ በማድረግ የተረጋጋ የማስተማር መማር ሂደት መፍጠር ያስችላል፡፡
- በክፍለ ጊዜው የተለያዩ የትምህርት መሳሪያዎችን፤ የማስተማሪያና የመገምገሚያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ በተሻለ ሁኔታ ማስተማር ያስችላል፡፡
- እናሳ ክፍለ ጊዜ ለተሰጣቸው ትምህርቶች ተጨማሪ ክፍለ ጊዜ ማግኘት ያስችላል፡፡
- ለተማሪዎች፤ የክፍል ሥራና የቤት ሥራን በመስጠት ሥራቸውን የመከታተል የማረምና ደከም ላሉ ተማሪዎችም ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል።
- ተማሪዎችና መምህራን ቤተመጻሕፍት፤ ትምህርት ማበልጸጊያ ማእከል፣ ላቦራቶሪ፤ ወርክሾኘ ወዘተ እንዲገቡና እውቀታቸውንና ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ያስችላል፡፡

9.1. የትምህርት ዓይነቶችና የክፍለ ጊዜ ስርጭት

9.1.1. **በመጀመሪያ ሳይክል /9–10/ የሚሰጡ የትምህርት አይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት ፣**

ተ.ቁ	የትምህርት መስክ	የትምህርት ዓይነት	የሳምንት የክፍለ ጊዜ ስርጭት	
			9	10
1	ቋንቋዎች	እንግሊዘኛ	4	4
		አማርኛ	2	2
3	የተፈጥሮ ሳይንስ	ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ	2	2
		ፊዚክስ	3	3
		ኬሚስትሪ	3	3
		ባዮሎጂ	3	3
4	የንብረተሰብ ሣይንስ	ሥነ–ዜጋ	3	3
		ጂኦግራፊ	2	2
		ታሪክ	2	2
5	የሰውነት ማጎልመሻ	የሰውነት ማጎልመሻ	1	1
6		የሳምንቱ ጠቅላላ ፔሬድ ብዛት	30	30

ማሳሰቢያ፣

ከላይ የተገለፀው የፊረቃ ክ/ጊዜ ሥርጭት ሲሆን ትምህርቱ በሙሉ ቀን ሲሰጥ ክፍለ ጊዜው ወደ 35 ከፍ ይላል። አምስቱ ተጨማሪ ክፍለ ጊዜያት አንዱ ለእንግሊዘኛ፣ ሦስቱ ክ/ጊዜያት ለሦስቱ ሳይንሶች እና አንዱ ለሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት ይመደባሉ።

9.1.2. ***በ2ኛ ሳይክል /11–12/ የሚሰጡ የትምህርት አይነቶችና የክፍለ ጊዜ ብዛት ፣***

ተ.ቁ	የትምህርት መስክ	የትምህርት ዓይነት	የሳምንት የክፍለ ጊዜ ስርጭት	
			11ኛ	12ኛ
1	የተፈጥሮ ሳይንስ	**ልዩ ኮርሶች /Specialized/**		
		1. ፊዚክስ	4	4

		2. ኬሚስትሪ	4	4
		3. ባዮሎጂ	4	4
		4. ቴክኒካል ድሮዊንግ	2	2
2		የጋራ ኮርሶች/COMMON CO,/		
		1. እንግሊዘኛ	6	6
		2. ሂሳብ	5	5
		5. ሥነ–ዜጋ	3	3
		6. የሰውነት ማሳልመሻ	1	1
		7. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ	3	3
		ልዩ ኮርሶች /SPECIALIZED/		
3	የነብረተሰብ ሣይንስ	ኢኮኖሚክስ	4	4
		ጂኦግራፊ	4	4
		ታሪክ	4	4
		ቢዝነስ /Generas Business/	2	2
6		አማራጭ ኮርሶች /Elective/		
		አንድ የብሔረስብ ቋንቋ ወይም አማርኛ	3	3
7	የሳምንቱ ጠቅላላ ፔሬድ ብዛት		35	35

በልዩ ትምህርት የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች፤

በእርከኑ በመደበኛ ት/ቤቶች የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች አንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪ የሚሰጡት የተለዩ ትምህርት ይዘቶች የሚከተለት ናቸው::

የመስማት ጉድለት ላለባቸው

የምልክት ቋንቋ መሪ የማስተማሪያ ቋንቋ ይሆናል።

ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚሰጡ

– የነፍስ ወከፍ ንግግር – የቋንቋ ችሎታን ማዳበር

- የቡድን ንግግር
- የምልክት ቋንቋ
- የማዳመጥ ሥልጠና

10. የትምህርት ወቅት

- አንድ የትምህርት ዓመት ከ203–206 የትምህርት ቀናት ይኖሩታል::
- አንድ የትምህርት ዓመት በሁለት ሴሚስተሮች ይከፈላል::
- በአንድ ሳምንት ውስጥ አምስት የትምህርት ቀናት ይኖራሉ ::
- በየሴሚስተሩ መጨረሻ የሚሰጡ ፈተናዎች በ10 ቀናት ውስጥ እንዲያጠናቅቁ ይደረጋል።
- በየሴሚስተር መጨረሻ ከፈተና በኋላ የአንድ ሳምንት የፈተና ማረሚያና ውጤት የማጠናቀቂ ጊዜ ይኖራል::

10.1 የትምህርት ቤት ሰዓት

መደበኛ ትምህርት በተመለከተ

- ትምህርት ቤቶች ሙሉ ቀን የሚያስተምሩ ሆኖ በቀን ሰባት ክፍለ ጊዜ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ 45 ደቂቃ የሚወስድ ይሆናል። ሆኖም በፈረቃ ለሚሰሩ ትምህርት ቤቶች በቀን 6 ክፍለ ጊዜ እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ 40 ደቂቃ ይኖረዋል፡

የመምህራን የሥራ ሰዓትና አጠቃቀም

- የአንድ መምህር የሳምንት መደበኛ የሥራ ሰዓት 40 ሰዓት ይሆናል::
  - **አንድ መምህር የሳምንቱን የሥራ ሰዓት በሚከተለው መልክ ሊደለድል ይገባዋል፣**
- በክፍል ማስተማር ሥራ ላይ እስከ ሃያ ሁለት ተኩል ሰዓት፣
- በክፍል ትምህርቶች ዝግጅትና የተማሪዎችን ሥራ ለማረምና ለመከታተል እስከ አስራ አንድ ሰዓት ተኩል፣
- ለተጓዳኝ ትምህርት እስከ ሦስት ሰዓት እና
- ለልዩ ልዩ ሥራዎች እስከ ሦስት ሰዓት መጠቀም ይችላል።

10.2 የተጓዳኝ ትምህርት ፤

- ፕሮግራሙ በትምህርት ቤቱ ዕቅድና አቅም መሰረት በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርቶች በሚያግዝ መልኩ ከክፍል ውጪ የሚሰጥ ሲሆን ልዩ ልዩ ክበባት እና ሌሎች ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች በማቋቋም ተማሪዎች ባላቸው ዝንባሌ፣ፍላጎትና ችሎታ እንዲደራጁ ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው በተለያዩ ክበባት እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ ከተደረገ ትርፍ ጊዜያቸውን ጠቃሚ በሆነ ሥራ እንዲያውሉ በማድረግና እንደፍላጎታቸው በማራዘም ሆነ በማሳጠር የመስራት ዕድል ስለሚያገኙ በክፍል ውስጥ ያገኙትን ዕውቀትና ክህሎት ያዳብራሉ።በሌላ በኩል በትምህርት ቤት ቆይታቸው ከጓደኞቸቸው ሆነ ከመምህራኖቻቸው በሚያገኙት ልምድ፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደር ከሚሰጥ መመሪያና በትም/ቤቱ በሚደረጉ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች የወደፊት ዝንባሌያቸውን ሊያዳብሩላቸው የሚችሉ ክህሎቶችን ማግኘት ይችላሉ::
- ስለሆነም ለመማር ማስተማር ሂደት የሚሰጠው ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት የተማሪዎች እድገትና ጥንካሬ እየታየ በሳምንት ከ4 ሰዓት በማይበልጥ ውስጥ ፕሮግራሙ መካሄድ አለበት።

የፕሮግራሙ ዓላማ :–

- ተማሪው የበለጠ ዕውቀት እንዲገበይ መርዳት፣
- ለሙያ ሥራ አክብሮትና መልካም አርአያነትን ለመፍጠር፣
- ተማሪዎች በፍላጎታቸው በችሎታቸውና በሀገሪቱ የት/ዓላማ መሠረት የወደፊቱን የሙያ መስክ ለመምረጥ እንዲችሉ ለመርዳት፣
- በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ችሎታቸውን ለማዳበር፣
- የሥራ መውደድ ባህርይ ለመፍጠርና ለማዳበር፣
- የተማሪዎች ዝንባሌ ወደ ጥናትና ምርምር እንዲያመሩ ለመርዳት፣
- ተማሪዎች ማኅበራዊ ግልጋሎቶችን እንዲሰጡ ለማበረታታት
- በክፍል ውስጥ ትምህርት ብቻ ሊገኙ የማይችሉ ለምሳሌ የማቀድ፣ የመምራት የማስተባበር፣ የመገምገም፣ ኃላፊነትን የመቀበል ፣ ውሣኔ የመስጠትን ፣ ችግሮችን በራስ አነሳሽነትና በፈጠራ የመፍታትን ተግባራትና ክህሎቶችንና ልምዶችን ለማዳበር፤
- ትርፍ ጊዜያቸውን ትምህርት በሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲያሳልፉ በማድረግ፣ እያንዳንዱ ተማሪ በቡድንና በግል የፈጠራ ሥራዎችን እንዲሠራ ለማበረታታት ፤

- ተጨማሪ ደስታና ልዩ ስሜትን በመፍጠር በት/ቤቶቻቸው ላይ ፍቅር እንዲያድርባቸውና የባለቤትነት መንፈስን እንዲገነቡና በዲሲፕሊን እንዲታነፁ ማድረግ፤
- በጥልቀትና በስፋት እንዲሰጡ የሚደረጉ የት/ዓይነቶች አማካይነት ለሚደክሙ ተማሪዎች ልዩ እርዳታ ለመስጠት፤
- በአካባቢያዊ / ክልላዊ አገራዊ፤ ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዩችን አዳዲስ ክስተቶችንና ችግሮችን፤ እንዲሁም ግኝቶችን ለተማሪዎች ለማስተዋወቅና . . በመፍትሔ ሰጪነት ለማሳተፍ ነው
- ተማሪዎች የዲሞክራሲ ባህል እንዲያዳብሩ፣ መብታቸውንና ግዴታቸውን አውቀው ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ለማደረግ፣

11. **የመረጃ አያያዝና ፍሰት**

አንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመረጃ አያያዝና ፍሰት በተመለከተ የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅበታል።፣

- የትምህርቱ እንቅስቃሴ ምን ሁኔታ ላይ እንዳለ የሚጠቁም ሪፖርት ለትምህርቱ ስርዓት ባለድርሻዎች (ለተማሪዎች፣ ለት/ቤቱ ማህበረሰብ፣ ለወላጆች ለሕብረተሰቡ፣ ለወረዳ ት/ጽ/ቤት. . .) ቢያንስ በየሩብ አመት የማሳወቅ ግዴታ አለበት::
- የተማሪዎች፣የመምህራን እና የንብረት ጉዳዮችን የተመለከቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የመስጠት ኃላፊነት አለበት።
- ቀበሌ፣ወረዳ ወይም ዞን እና የክልል ትምህርት መዋቅሮች እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ትምህርት ሚኒስቴር ከትምህርት ቤቱ የሚፈልገውን መረጃ የማግኘት መብት አለው።።።
- የተማሪዎችን፣ የመምህራንንና የንብረት መግለጫዎችን በመዝገብ አደራጅቶ የመያዝ ኃላፊነት አለበት።
- የትምህርት ሥራ ሂደት ለመገምገምና ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ከክልል፣ ከወረዳ ወይም ከዞን እንዲሁም ከማዕከል ወደየተቋማቱ ለሚመጡ የትምህርት ባለሙያዎች ትምህርት ቤቱ የተፈለገውን መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

12. **የትምህርት ደረጃ ምዘናና ማጠናቀቂያ መረጃ**

ማንኛውም ት/ቤት በአግባቡ የእያንዳንዱን ተማሪ የመማርና በትምህርቱም ለውጥ/እድገት/ ማምጣቱን የሚያመለክቱ መረጃዎችን በመሰብሰብና በመተንተን መለካት አለበት። ተማሪው ትምህርት ለመማሩ የሚቀርበው መረጃ የሥርዓተ ትምህርቱን ብቃት፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችን፣ ሙያዊ እድገትንና ደጋፊ አገልግሎቶችን ለመገምገምና ለማሻሻል ይረዳል። ተማሪው በትምህርቱ የሚያሳየው መሻሻልና አፈፃፀም በዋነኛነት በተማሪው ወላጆችና በት/ቤቱ ማህበረሰብ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ በአካባቢው ማህበረሰብ መታወቅ ስላለበት በትክክለኛው መንገድ፣ ግልፅና በአግባቡ ተጠናቅሮ መገለፅ አለበት።
ምዘናን በተመለከተ ለሁሉም ት/ቤቶች የስታንዳርድ አመላካቾች የሚከተሉት ናቸው።

- የት/ቤቱ አመራርና ሠራተኛ ለተማሪዎች ትምህርት ቁርጠኛ መሆን፣ ተሳታፊ መሆንና ተጠያቂነት ሊኖረው ይገባል።
- የተማሪው ትምህርት አቀባበል በአገሪቱ ባለው ሥርዓተ ትምህርትና የማስተማር እንቅስቃሴ ላይ መሠረት ያደረገ መሆን ይገባዋል።
- የተማሪው ውጤት ለት/ቤቶች በሚመደብ ሃብት ላይ ውሳኔ ለመስጠት የሚጠቅሙ መሆን አለበት።
- የምዘና ዘዴዎችና ይዘቶች የተማሪዎቹን ህብረተሰባዊ፣ ስሜታዊ፣ አካላዊና የግንዛቤ/ቋንቋ ግቦችን ማካተት ይኖርባቸዋል።
- ምዘናዎች የእያንዳንዱን ተማሪ ልዩ ፍላጎቶችና ልምዶችን ማንፀባረቅ አለባቸው።
- የተማሪው ቤተሰቦች የተማሪውን ውጤት በተመለከተ ጠቃሚ የመረጃ ምንጮች ተደርገው መወሰድ አለባቸው፡.
- የተማሪዎችን የትምህርት እንቅስቃሴና አፈፃፀምን በተመለከተ ከተማሪው ወላጅ ጋር የሚደረገው የመረጃ ልውውጥና ግንኙነት መደበኛ፣ ጠቃሚና ትርጉም ያለው መሆን አለበት።
- የምዘና ውጤቶች የተማሪው ቤተሰብ ለተማሪው ለሚሰጠው ማንኛውም አስተዋፅኦ መሠረት በመሆናቸው እነዚህ መዛግብቶች በአግባቡ መጠበቅ አለባቸው።
- ተማሪዎች ለየክፍል ደረጃው የተዘጋጀውን ትምህርት በተወሰነው የክፍል ጊዜና የትምህርት ወቅት ተገኝተው መማራቸውን ትምህርት ቤቱ ማረጋገጥ አለበት።

- ት/ቤቱ ተማሪዎች ተከታታይ ምዘናና የማጠቃለያ ፈተና መውሰዳቸውንና በወቅቱ ባለው መመሪያ መሠረት ወደሚቀጥለው ክፍል ለመግባት የሚያስችልና የነበሩበትን ክፍል አጠናቀዋል የሚል አጥጋቢ ውጤት ማምጣታቸውን ማረጋገጥ አለበት።
- ለደረጃውና ለእርከኑ የተመደበውን ትምህርት በትክክል ማጠናቀቃቸውን ፤ በት/ቤቱ መረጃ ወይም በብሔራዊ ፈተና ውጤት መሠረት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

13. **በማረጋገጫ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች**

- ለየክፍሉ ትምህርት ማጠናቀቂያ ወይም የሴሚስተር ፈተና ውጤት መግለጫ ወይም የተማሪ ሪፖርት ካርድ በየዓመቱ ለተማሪ ይሰጣል::
- ተማሪው የአንዱን እርከን ትምህርት ሳያጠናቅቅ በየእርከኑ መካከል ትምህርት ቤት ቢቀይር ከሚለቅበት ት/ቤት የሚሰጠው የየክፍሉ የተጠናቀረ ዝርዝር ውጤት /ትራንስክሪኘት/ እና የመልቀቂያ ሕጋዊ ሰርተፊኬት የተወሰኑ የትምህርት ደረጃ ማጠ ናቀቂያ መግለጫ ይሆናሉ::
- በየርከኑ መጨረሻ ክፍል የሚሰጥ የትምህርት ውጤት ሕጋዊ መግለጫ / ትራንስክሪኘት/ እና የብሔራዊ ወይም አገራዊ ፈተና የሚሰጥበት ደረጃም ከሆነ የብሔራዊ ወይም የአገራዊ ፈተና ውጤት ሕጋዊ መግለጫ ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ መብቃታቸውን ማረጋገጫ ይሆናል::
- በየርከኑ መጨረሻ የሚሰጥ የትምህርት ማስረጃዎች ወይም ሰርተፊኬቶች በማስተማሪያ ቋንቋ ወይም በአገር አቀፋዊ የሥራ ቋንቋ ወይም በክልላዊ የሥራ ቋንቋ ተዘጋጅተው ይሰጣሉ ::

14. **የት/ቤት፣የአካባቢው ማኅበረሰብ/ ኮሚኒቲ/ እና የወላጅ ግንኙነት**

- አንድ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሲቋቋም የአካባቢው ህብረተሰብ የሚፈልገውን ጥቅም እንዲሰጥ ሆኖ ይደራጃል:: ማኅበረሰቡም የትምህርት ቤቱን መቋቋም ጥቅም ተገንዝቦ የመማር ማስተማሩን ሥራ በተገቢው መንገድ እንዲተገበር ቀጥታ ግንኙነት ያደርጋል። የመማር ማስተማር ሥራ የትምህርት ቤቱንና የአካባቢውን ህብረተሰብ አባላት በትምህርት ቤቱ የለት ተዕለት ዕንቅስቃሴ ዙሪያ ተሣትፎአቸውን በሚከተሉት መድረኮች ሊገልጹ ይችላሉ።
    - የትምህርትና ሥልጠና አመራር፣

1) በትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ
2) በወላጅ መምህር ህብረት /ወመህ/

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በትምህርትና ሥልጠና አመራር ቦርድ ይመራል። ይህ ቦርድ ከህብረተሰቡ፣ ከት/ቤቱ ማህበረሰብና ከቀበሌ መስተዳድር የተውጣጡ አባላት ሲኖሩት በመልካም ሥነምግባራቸውና በአመራር ችሎታቸው የተመሰገኑ ሆነው የቦርድ ሰብሳቢ ከቀበሌ መስተዳድር የሚወከል ሲሆን የት/ቤቱ ርዕሰ-መምህር የቦርድ ፀሐፊ ይሆናል።

✓ **የትምህርት ቤቱ፣ የአካባቢው ማህበረሰብና የወላጅ ግንኙነት ዓላማ፣**

- ት/ቤቱ በትምህርት ዘመኑ ያከናወናቸው ተግባራትና ያጋጠሙት ችግሮችን ለህብረተሰቡ ለማሳወቅና መፍትሄ ለመሻት፣
- ኅብረተሰቡ የትምህርት ቤቱን ችግርና ዕቅድ ተረድቶ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዲችል።
- ስለተማሪዎች የትምህርት ውጤት ወላጆች አውቀው ተገቢውን ክትትል በማድረግ ድጋፍ እንዲያደርጉ፤
- የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት ለማጠናከርና የትምህርቱ ውጤት ይበልጥ የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል፤
- .ትምህርት ቤቱን ለማጠናከር በሚቀርብ ዕቅድ ላይ ውይይት በማካሄድ ፤ መርምሮና አሻሽሎ በማጽደቅ አፈጻጸሙን ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣
- ሥርዓተ ትምህርቱ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተዛምዶ ለተማሪዎቹ መቅረቡንና ችግር ፈቺ መሆኑን ለመከታተልና ድጋፍ ለመስጠት

✓ **የትምህርት ቤቱ አመራር ድርሻ፣**

- የተማሪዎችን ወላጆች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ በመጥራት በልዩ ልዩ የትምህርት ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረክ ማዘጋጀት።
- በአካባቢው የልማት ሥራ በመሳተፍና የተለያዩ ክበባትን አቋቁሞ ትምህርታዊና አዝናኝ የሆኑ ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ለአካባቢው ህብረተሰብ አስተዋጸ ያደረጋል፣
- በአካባቢው ማህበረሰብ እንቅስቃሴዎች ማለትም የኢኮኖሚ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መሳተፍና አዳዲሰ ሀሳቦችን በማመንጨት የመፍትሄ ሀሳቦች የማቅረብ ኃላፊነት አለበት።

- የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል፣ ውጤትና ሥነምግባር በሚመለከት ጉዳዮችን በየግዜው የማሳወቅ ግዴታ አለበት።
- ተማሪዎች ለመማር ተግባር የሚያስፈልጋቸውን የትምህርት ቁሳቁሶች እንዲያሟሉላቸው በማሳወቅ ተግባራዊነቱም ይከታተላል።

የተማሪ ወላጅ ድርሻ፣

- ት/ቤቶች በሚያዘጋጇቸው የምክክር መድረኮች ላይ በመሳተፍ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ይወጣሉ።
- የልጆቻቸውን የትምህርት አቀባበልና የሥነምግባር ሁኔታ በየጊዜው በመከታተል ለት/ቤቶች ግብረ መልስ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።
- በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እንዲሁም በጉልበት ት/ቤቱን ማገዝ ይጠበቅባችዋል።
- የአካባቢውን ህብረተሰብ ለትምህርት ቤቱ የልማት እንቅስቃሴ የማስተባበር ሃላፊነት አለባቸው::

የአካባቢው ህብረተሰብ ድርሻ፣

- ትምህርት ቤቱ፣ለተማሪዎችና ለት/ቤቱ ሠራተኞች ደህንነት ሲባል የሚያደርጋቸው እንስቃሴዎች ላይ በጋራም ሆነ በተናጠል በመሳተፍ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል።
- ት/ቤቱ የራሱ ህብት እንደሆነ ተገንዝቦ መንከባከብና መጠበቅ አለበት።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የደረጃ መለኪያ /ስታንደርድ/

የመጀመሪያ ረቂቅ

ትምህርት ሚኒስቴር
ግንቦት 2001 **ዓ/ም**

ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ 1

1 የቅድመ - መደበኛ ትም/ፕሮግራም የደረጃ መለኪያ 4

1.1 የቅድመ-መደበኛ ትም/ተቋማት አስፈላጊነት 4

1.2 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም 5

1.3 የፕሮግራሙ አወቃቀር 6

1.4 የፕርግራሙ አደረጃጀት 6

1.4.1 ጨዋታ 6

1.4.2 በክፍልና ከክፍል ውጭ ተቀናጅተው የሚሰጡ ፕሮግራሞች 6

1.4.3 ሥራ 7

1.5 የፕሮግራሙ ወቅት /ካላንደር/ 8

1.6 የክፍለ - ጊዜያት ሥርጭት 9

1.6.1 ሳምንታዊ የክፍለ - ጊዜያት ሥርጭት 9

1.6.2 ዕለታዊ ፕሮግራም መርሀ-ግብር 10

1.7 የመምህራን የሥራ ሰዓት መጠን 11

1.8 የማስተማር ዘዴዎች 12

1.9 ከመምህራን የሚጠበቅ ባህርይ 12

1.10 የቅድመ - መደበኛ መርሀ - ግብር ያጠናቀቁ ህፃናት ባህርይ..... 13

1.11 የቅድመ - መደበኛ ትም/ ተቋማት የሚቋቋሙባቸው አካባቢዎች
የህንፃው ሁኔታ 13

1.11.1 የቦታ አመራረጥ 13

1.11.2 የምድረ-ግቢው ገጽታና አደረጃጀት..... 14

1.11.3 የቅድመ- መደበኛ ትም/ተቋማት መጠን 14

1.11.4 የምድረ -ግቢና የህንፃዎች አደረጃጀት 15

1.12 የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት ሊኖሩት የሚገባ የአገልግሎት
መስጫ ክፍሎች 16

1.13 ለልዩ ልዩ ክፍሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች..... 17

1.13.1 ለአንድ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎች .. 17

1.13.2 መስማት ለተሳናቸው ህፃናት 17
1.13.3 ማየት ለተሳናቸው ህፃናት 17
1.13.4 የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ሕፃናት 18
1.13.5 ለተግባራዊ ትምህርት የሚገለግሉ መሣሪያዎች 18
1.13.6 የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ዕቃዎች..... 18
1.13.7 ለመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል የሚያስፈልጉ
መድኃኒቶች 19
1.13.8 ለማዕድ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች 19
1.13.9 አላቂ የመጫወቻ ዕቃዎች 20
1.13.10 ቋሚ የውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች 21
1.13.11 ለርዕሰ መምህር ቢሮ የሚያስፈለጉ ዕቃዎች 21
1.14 የሰው ሃይል ምደባ 22
1.14.1 የመምህራንና የሠራተኞች ምደባ..... 22
1.14.2 የመምህራንና የሠራተኞች ብዛት 22
1.14.3 የመምህራንና የሠራተኞች የትምህርት ደረጃ 23
1.15 ልዩ ልዩ አስፈላጊ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት መመሪያዎች 23
1.16 የቅድመ - መደበኛ ትም/ተቋም ከወላጆች፣ከህብረተሰቡና ከአመራር
ጋር ሊኖረው የሚገባ ግንኙነት..... 24
1.16.1 የወላጆች ሚና 24
1.16.2 የአመራር ሚና 25
1.16.3 የህብረተሰብ ሚና 25

መግቢያ

የአንድ አገር የትምህርት ሥርዓት አደረጃጀት፣ የትምህርቱ አላማና ይዘት ህብረተሰቡ የደረሰበትንና ወደፊት ሊደርስበት የሚፈልገውን የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት ደረጃ ያንፀባርቃል።

የትምህርት ዓላማ ታዳጊው ትውልድ ሕብረተሰቡ ዘንድ ተፈላጊነት ያላቸውና በሥራ ሊተረጐሙ የሚችሉ ባህሪያትን/ዕውቀትን፣ ልዩ ልዩ ችሎታዎችን፣ ክህሎቶችን፣ ልምዶችን የተስተካከለ አመለካከትንና ወዘተ. እንዲጨብጥና በሕብረተሰቡ ሕይወት ንቁ ተሳታፊና አምራች ዜጋ እንዲሆን ማድረግ ነው። እነዚህ የተነደፉት የትምህርት ዓላማዎች በተግባር ሊተረጐሙ የሚችሉት ደግሞ አስፈላጊው ግብዓቶች በጥራት ተሟልተውና ተደራጅተው ሥራ ላይ ሲውሉ ነው።

በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የትምህርት ፕሮግራሞች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ ያስፈልጋል። የአንድ አገር የትምህርት ጥራት ከሚገለጥባቸው ባህርያት መካከል ዋናዋናዎቹ፣

- የትምህርት ፖሊሲውና የትምህርት ዓላማው ግልጽነት፣
- በተማሪው ላይ ለማምጣት የተፈለገው የባህርይ ለውጥ በደረጃው ዓይነት፣ ግልጽነትና ስኬታማነት መለየት፣
- የሚፈለገውን ባህርይ ለማስገኘት የሚያስችል የትምህርት ይዘት ጥራትና ዓይነት፣
- የትምህርቱ አደረጃጀትና አወቃቀር አመቺነት፣
- የትምህርት መተግበሪያ ዘዴ፤ ስትራቴጂ በአጠቃላይ ሥርዓተ ትምህርቱ ይገኙበታል። ከላይ የተጠቀሱት የባህርያት ጥራት፤ ብቃትና የምቹነት ደረጃዎች በአንፃራዊነት የሚታዩ፣ ደረጃ በደረጃ እያደጉና እየተለወጡ የሚሄዱ መሆናቸው ቢታወቅም፣ በአንድ በተወሰነ ወቅት መነሻቸውና የጥራት ደረጃቸው ተጠብቆ ስለመካሄዳቸው መመዘን መቻል አለባቸው።

አንድ የትምህርት ፕሮግራም ደረጃውን የጠበቀ ነው ለማለት የሚቻለው ዝቅተኛው /አነስተኛ/ መነሻ መለኪያ /እስታንዳርድ/ ተቀምጦለት በዛው መሠረት እየተጓዘ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው።

የአንድ አገር የትምህርት ጥራት ደረጃ ሊመዘን የሚችለው በአገሪቱ ውስጥ በሚኖረው የደረጃ መለኪያ /ስታንዳርድ/ አኳያ ሲገመገም፣ ተመሳሳይ ስታንዳርድ ካላቸው አገሮች አኳያ ተነፃፅሮ ሲታይና የተሻለ ስታንደርድ እየተጠቀሙ ነው ከሚባሉት አገሮች ጋር ሲገናዘብ ነው።

በአገራችን የትምህርት የዕድገት ደረጃ ሲታይ የተዘበራረቀ ከመሆኑም በላይ ፍላጐትንና አቅምን አጣጥሞ የሚራመድ አይደለም። ለምሳሌ ከአቅም በላይ እስከ 10,000 ተማሪዎች ይዘው የሚያስተናግዱ ትምህርት ቤቶች ሲኖሩ በአንፃሩ ደግሞ ከ400 እና ያነሰ ተማሪዎች ይዘው የሚጓዙ ትምህርት ቤቶች አሉ፤ በውስጥ ድርጅትና በበቂ የማስተማሪያ መሣሪያ የተደራጁና ያልተደራጁ አሉ። እንደዚሁም የመምህራን ብዛትና ጥራት፤ የመማሪያ ክፍሎች መጠን በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በአንድ ክፍል ከ40-50 ተማሪዎች የሚማሩበትና በአንፃሩ ደግማ እስከ 90 የሚማሩበትም አሉ።

እነዚህና ሌሎች መሰል ችግሮች የትምህርቱ ዓላማ ግብ እንዳይመታ እንቅፋት ስለሚሆኑ ትምህርት ቤቶች በሥርዓተ ትምህርት፤ በትምህርት መሣሪያዎች፤ በመምህራን ችሎታና ብቃት በሕንፃቸው አደረጃጀትና በትምህርት አመራርና አስተዳደር ወዘተ. አጠቃቀም ተመጣጣኝና አስገዳጅነት ያለው መነሻ/መለኪያ/ስታንዳርድ/ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

ትምህርት ቤቶች በመንግሥትና በሕዝብ የጋራ ጥረት የሚመሩ፤ የሚተዳደሩና የትምህርቱ ዓላማ ግብ እንዲመታ የሚያበቁ ድርጅቶች ናቸው። በመሆኑም በትምህርት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎች፤ በትምህርት ቤቶች ኢንቬስት የሚያደርጉ የግል ባለሀብቶች እንዲሁም በአጠቃላይ ህብረተሰቡ በየትምህርት እርከኑ ሊሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት አጠቃላይ ትምህርት በሚከተሉት እርከኖች ተደራጅቷል።

1/ የቅድመ - መደበኛ ትምህርት /2 ዓመት/

2/ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት /1-8/

ሀ. የመጀመሪያ ሳይክል ከ1-4 መሠረታዊ ትምህርት

ለ. ሁለተኛ ሳይክል ከ5-8 አጠቃላይ ትምህርት

3/ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት

ሀ. የመጀመሪያ ሳይክል /9-10ኛ/ የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠቃለያ

ለ. ሁለተኛ ሳይክል (11 - 12) ተማሪዎች በሕብረተሰብና በሳይንስ የትምህርት ዘርፎች ለከፍተኛ ትምህርት የሚዘጋጁበት የትምህርት እርከን ነው።

በትምህርቱ ዓላማ መሠረት በየእርከኑ የትምህርት ጥራት እንዲጠበቅና ወይም ስታንዳርዱን የተጠበቀ ለማድረግ መታየት የሚገባቸው ዋና ዋና ጉዳዩች፡-

- የትምህርቱ መዋቅር፤ የትምህርት ወቅትና የትምህርት ፕሮግራሞች፣
- የትምህርቱ ሥራ መመሪያዎች፣
- የትም/ቤቱ አደረጃጀት
  - የትምህርት ቤቱ ደረጃ
  - የሕንፃው ሥራ
  - የትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ
  - የተማሪዎች ብዛት በትምህርት ደረጃና በእያንዳንዱ ክፍል
  - ልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎችና መሣሪያዎች
  - የመምህራንና፣ የሠራተኞች ብዛት፤ ዓይነትና የት/ደረጃ
  - መጻህፍት፤ የመምህሩ መምሪያና የተማሪዎች መማሪያ መጻህፍት
  - ለልዩ ትምህርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፤ መጻሕፍት ወዘተ.. ሲሆኑ፤

እነዚህን የያዘ መነሻ የሚሆን የትምህርት ደረጃ መለኪያ/ስታንዳርድ/ ተሻሽሎና ተዘጋጅቶ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ስታንደርዱ የተዘጋጀው የትምህርቱን ሥራ በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው መሠረት ተግባራዊ ለማድረግ ነው። ይሁን እንጂ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን በአንድ ጊዜ ዕውን ለማድረግ ጊዜን የሚጠይቅ ስለሚሆን በተዘጋጀው ስትራቴጅና በወጣለት ዕቅድ መሠረት በአጭርና በረዥም ጊዜ ተግባራዊ ይሆናል። በዚህ መሠረት የአጭር ጊዜው ዕቅድ ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ ሁኔታዎች ማመቻቸት ሲሆን የረዥም ጊዜዕቅድ ደግሞ ስታንዳርዱን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ይሆናል። ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቶችን በግል የሚከፍቱ ባለሀብቶች ስታንዳርዱን ጠብቀው እንዲሰሩ ይጠበቃል።

1) የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የደረጃ መለኪያ

1.1 የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት አስፈላጊነት

ሕፃናቱ ከዕድሜያቸው ለጋነት የተነሳ በማንኛውም ጊዜ ከየትኛውም የሕብረተሰብ ክፍል የበለጠ ለአደጋና ለጉዳት የተጋለጡ በመሆናቸው ልዩ ጥበቃ፣አያያዝና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው። በተለይ በመጀመሪያዎቹ አምስት አመታት የሚደረግ እንክብካቤ ለህፃናት ህልውና ማለትም መኖር አለመኖር እንዲሁም ለወደፊት ዕድገታቸው ወሳኝነት እንዳለው ስለሚታመንበት ልዩ ትኩረት የሚያስፈለገው ጉዳይ ነው።

የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ተቋማት ሕፃናት የወደፊት ህይወታቸው መሠረት የሚጥሉበትና ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ዝግጁ የሚደረጉበት ሥፍራዎች ናቸው። እንደዚሁም ሕፃናት በጋራ ተሰባስበው አንድ ላይ በሚውሉበት ወቅት የጋራ ስሜትን በማዳበር ማህበራዊ ጠቀሜታንም የሚያስገኝ ነው። በተጨማሪም እናቶች በቂ ጊዜ እንዲኖራቸው በማድረግ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ኑሮ መስክ በመሳተፍ የሚፈለግባቸውን የአገር ግንባታ ተግባር የበኩላቸውን እንዲወጡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው። ከዚህ አኳያ ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አስፈላጊውን ግብአት መመደብ በወደፊቱ የአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ አስተዋጽኦ ያለው ከመሆኑም በላይ ማህበራዊ እኩልነትን የሚያጠናክር ነው።

የቅድመ - መደበኛ ትምህርት መርሐ ግብር ዕለታዊ እንቅስቃሴ በ3 ዋና ዋና አቅጣጫዎች ይመራል።

እነዚህም፣

1/ ነፃና የታቀደ ጨዋታ፣

2/ ትምህርት እና

3/ ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው ሥራ ናቸው።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት + የሚካሄደው ፕሮግራም ተግባራዊ የሚሆነው /ማስተላለፊያ ዘዴው/ (method) በጨዋታ ነው። ይህ የማስተማርያ ዘዴ

የተመረጠበት ምክንያት በዚህ ዕድሜ ክልል ያሉ ህፃናት ጨዋታን እንደ ዋና ተግባራቸው አርገው ስለሚወስዱትና ሕፃናት በጨዋታ ሲሳተፉ አካላቸው ይዳብራል፤ አእምሮአቸው ይበለጽጋል፣ ማህበራዊና ስሜታዊ እሴቶቻቸው ይጎለብታል። ስለሆነም ሕፃናት የአካል፣ የመንፈስ፤ የስሜትና የማህበራዊ ኑሮ አስተሳሰብ ብቃታቸው ዳብሮ ለመደበኛው ትምህርት ዝግጁ የሚሆኑት በግልና በጋራ በሚካሄድ ጨዋታ በመሆኑ ለጨዋታው የተለየ ትኩረት ይሰጠዋል።

ሕፃናት ከላይ የተጠቀሱትን ሰብዕናዎች ሊያዳብሩ የሚችሉት በተበታታነ ሁኔታ ሳይሆን በቅድመ - መደበኛ ትም/ተቋማት በመሰባሰብ ነው። በመሆኑ ለዚህ ከፍተኛ ጠቀሜታ ላለው የትምህርት ፕሮግራም በወላጆችና በሕብረተሰቡ ዘንድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

1.2 የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም

ይህ ፕሮግራም ዕድሜያቸው ከ4-5 እና ከ5 – 6 ዓመት የሆናቸው ጤናማና ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት ሁለገብ የሆነና ለዘላቂ ሕይወታቸው መሠረት የሚጥል ዕውቀት፤ ክህሎትና ባህርይ እንዲያገኙ ለማድረግ ሥርዓት ባለው መልኩ ይደራጃል። በዚህ ደረጃ ሕፃናት ከማንኛውም የትምህርት ደረጃ በበለጠ ጥበቃና እንክብካቤ ተደርጎላቸው፤ በአካል፣ በአእምሮ፣ በስሜትና በማኅበራዊ ኑሮ ተገቢውን የዕድገት መሠረት አግኝተው ማደግ እንዲችሉ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ የሚገባው ነው፣ ይህም የወላጆችንና የኅብረተሰቡን የቅርብ ክትትል፤ የመምህራንን ትጋትና ከፍተኛ ጥረት እንዲሁም፤ የመንግሥትን ትኩረት የሚጠይቅ ነው። ለዚህ ፕሮግራም አደረጃጀት፤አመራርና አስተዳደር የሚረዱ ዝርዝር የሥራ መመሪያዎች አሉ። ስለሆነም መመሪያዎቹ በየደረጃው ባሉ ኃላፊዎች፣ ተጠቃሚ ክፍሎችና ሌሎች ባለድርሻዎችን ጨምሮ በሁሉም ዘንድ ታውቀውና እኩል ግንዛቤ አግኝተው ስለአፈጻጸማቸው ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገና አስፈላጊው ሙያዊ ድጋፍ እየተሰጠ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያሰፈልጋል።

ስለዚህ ከተቋሙ አመሠራረት ጀምሮ ፕሮግራሙ በምን መልክ መደራጀት እንዳለበት፣ የፕሮግራሙንም ሂደት በብቃት በመምራት የሚፈለገው ውጤት እንዲገኝ የሚያስችሉ መሠረታዊ የመነሻ ዝግጅቶች እንዲኖሩ ማድረጉም አስፈላጊነቱ የጎላ ነው።

1.3 የፕሮግራሙ አወቃቀር

የቅድመ - መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከ4 – 6 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ህፃናት ደረጃውን ጠብቆ ለሁለት ዓመት የሚካሄድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት

ፕሮግራም ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ከ4-5 እንዲሁም 2ኛው ደረጃ ከ5-6 ዕድሜ ላላቸው ሕፃናት አንድ ዓመት የሚካሄድ ፕሮግራም ነው።

ይህ ፕሮግራም ልዩ ፍላጎት ያላቸዉንም ህፃናት የሚያቅፍ ሲሆን፣

ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት የተባሉትም የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

ዕድሜ ላላቸው ለአንድ ዓመት፣

- ማየት የተሳናቸው፣
- መስማት የተሳናቸው፣
- የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ያለባቸው፣
- የስሜት መረበሽ ያለባቸው፣
- የመማር ችግር ያለባቸው፣
- የመናገር ችግር ያለባቸው፣
- የአካል ጉዳት ያለባቸው፣
- ተደራራቢ ጉዳት ያለባቸው፣
- ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው .. ወ.ዘ.ተ ናቸው

1.4 የፕሮግራሙ አደረጃጀት

በቅድመ መደበኛ ትምህርት የሚካሄዱ የፕሮግራም ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

1.4.1 ጨዋታ

- በሕፃናቱ ምርጫ የሚከናወኑ ጨዋታዎች፤
- በመምህራን መሪነት የሚከናወኑ ጨዋታዎች፤

1.4.2 በክፍልና ከክፍል ውጭ ተቀናጅተው የሚሰጡ ፕሮግራሞች

- ቋንቋ የአፍ መፍቻ ቋንቋ

- የአካባቢ ሣይንስ ትምህርት
- ሂሣብ
- ሥዕል፣ሙዚቃና የሰውነት ማጐልመሻ
- እንግሊዝኛ

1.4.3 ሥራ

- ህፃናት የሚያከናውኑአቸው ሥራዎች በሁለት ይከፈላሉ። እነዚህም፡-
- ግላዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሥራዎች
- ማኅበራዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ሥራዎች ሲሆኑ፣ ልዩ ፍላጎት ላላቸው ሕፃናት በተጨማሪ የሚከተሉት ሥራዎች ይሰጣሉ።

ሀ. ማየት ለተሳናቸው

- የስሜት ሕዋሳትን የማነቃቃትና የማዳበር
- የነፃ እንቅስቃሴ ትውውቅ/ሞብሊቲና ኦረንቴሽን
- የዕለት ተዕለት ክሂልን የማዳበር
- ቅድመ-ብሬል
- ቅድመ-አባከስ
- የእይታ ስሜት ቀስቃሽ ክንውን /በመስማት እንዲያዳብሩ/

ለ. መስማት ለተሳናቸው

- ከናፍረ-ንባብ
- የማዳመጥ ልምድ
- ንግግር
- ቋንቋ
- የምልክት ቋንቋና የጣት ፊደል ቆጠራ
- ረዳትን የመስሚያ መሣሪያዎች የአጠቃቀም ልምምድ

ሐ. የአእምሮ ዕድገት ዝግመት

- **እንቅስቃሴ**
- **እጅን እንደተፈለገ የመጠቀም ልምምድ**
- **ጨዋታ**
- **ቋንቋ**
- **ማኅበራዊ ኑሮ ዕድገት**
- **ራስን የመርዳት ክሂሎች**
- **ሥነጥበብና ሙዚቃ**

1.5 የፕሮግራም፣ ወቅት/ካሌንደር/

- **የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከ**203 – 206 **ቀናት ይኖሩታል።**
- **የአንድ ዓመት የቅድመ መደበኛ ፕሮግራም** 30 **ሳምንታት ሆኖ በሣምንት** 5 **ቀናት /ከሰኞ-ዓርብ/ ይካሄዳል። በሣምንት** 25 **ክፍለ ጊዜያት ሲኖሩት፣ የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ** 30 **ደቂቃ ሆኖ በመካከል የ**5 **ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል፣**
- **የተቀመጠው የክፍለ-ጊዜ ብዛት እንደ ሕፃናቱ ፍላጎትና ከአካባቢውና ከትምህርቱ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ሊሻሻል ይችላል።**

ሀ. **ለደረጃ አንድ ከ/**4-5 **ዓመት ዕድሜ ላላቸው/ የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት** 25 **ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ**5 **ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።**

ለ. **ለደረጃ ሁለት ከ/**5-6 **ዓመት ዕድሜ ላላቸው/ የአንድ ክፍለ - ጊዜ ርዝመት** 30 **ደቂቃ ሆኖ በክፍለ ጊዜያት መካከል የ**5 **ደቂቃ የዝግጅት ጊዜ ይኖረዋል።**

- **የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም በሙሉ ቀን ይካሄዳል።**
- **በመጀመሪያ ሴሚስተር መጨረሻ ላይ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት ለ**15 **ቀናት ዕረፍት ዝግ ይሆናሉ።**

1.6 የክፍለ ጊዜያት ሥርጭት፤

1.6.1 ሣምንታዊ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት፤/ የክፍለ- ጊዜ ስርጭት

ተ/ቁ	የፕሮግራም ዓይነት	ለደረጃ አንድ ከ4-5 ዓመት*	ለደረጃ ሁለት ከ5-6 ዓመት*	ምርመራ
1	ጨዋታ	10	8	
2	ትምህርት			
	– ቋንቋ	3	4	
	– የአካባቢ ትምህርት	2	2	
	– ሂሣብ	2	2	
	– ሙዚቃ	2	2	
	– የሰውነት ማጐልመሻ	2	2	
	– የሥነ ሥዕልና ቅርጻ ቅርጽ	2	3	
3	– ሥራ / ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው/	2	2	
	ድ ም ር	25	25	

*ከ4-5 ዓመት ማለት ዕድሜያቸው 4 ዓመት ያለፋቸውና እስከ 5 ዓመት የደረሰ ማለት ነው።

*ከ5-6 ዓመት ማለት 5 ዓመት ያለፋቸውና እስከ 6 ዓመት የደረሱ ሕፃናት ማለት ነው።

ማሳሰቢያ፣

1 መደበኛውን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም መከታተል የሚችሉ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት በተለየ ክፍል ውስጥ ሆነው ልዩ ክህሎቶችን ከተከታተሉ በኋላ ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው በፕሮግራሙ ላይ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ። ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው ፕሮግራሙን እኩል መከታተል የማይችሉት ግን በተለየ ክፍል ውስጥ በመሆን አግባብ ያለውን ፕሮግራም ይከታተላሉ። ለዝርዝር ማብራሪያ የልዩ ትምህርት መመሪያ ይመለከቷል።

2 ለየቡድኑ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ በዕለታዊ የፕሮግራም መርሃ ግብር ላይ እንደተመለከተው የጨዋታ፣ የትምህርትና የሥራ ጊዜ ርዝመት እንደ አስፈላጊነቱ የተለያየ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

1.6.2 ዕለታዊ ፕሮግራም መርሃ ግብር

ተ ቁ	የፕሮግራሙ ዓይነት	ደረጃ 1	ደረጃ 2
		ከ4-5 ዓመት	ከ5-6 ዓመት
1	የመቀበያ ሰዓት	2፡00 - 3፡00 ሰዓት	2፡00 - 3፡00 ሰዓት
2	ለትምህርት ቅድመ ዝግጅት	3፡00 - 3፡05 "	3፡00 - 3፡05 "
3	ትምህርት	3፡05 - 3፡30 "	3፡05 - 3፡35 "
4	ለትምህርት ቅድመ ዝግጅት	3፡30 - 3፡35 "	3፡35 - 3፡40 "
5	ትምህርት	3፡35 - 4፡00 "	3፡40 - 4፡10 "
6	ለቁርስ ዝግጅትና ቁርስ መመገቢያ	4፡00 - 4፡40 "	4፡10 - 4፡50 "
7	ዕረፍት/ነፃ ጨዋታ/	4፡40 - 5፡40 "	4፡50 - 5፡50 "
8	የክፍል ውስጥ ጨዋታ	5፡40 - 6፡05 "	5፡50 - 6፡20 "
9	የክፍል ዝግጅት	6፡05 - 6፡15 "	6፡20 - 6፡30 "
10	የምሣ ዝግጅትና መመገቢያ	6፡15 - 7፡15 "	7፡30 - 8፡30 "

11	ከመኝታ መነሳትና መፀዳዳት	8፡15 - 8፡30 "	8፡30 - 8፡45 "
12	የትምህርት ቅድመ ዝግጅት	8፡30 - 8፡35 "	8፡45 - 8፡50 "
13	ትምህርት	8፡35 - 9፡00 "	8፡50 - 9፡20 "
14	የውጭ ጨዋታ	9፡00 - 9፡50 "	9፡20 - 9፡50 "
15	ወደ ቤት ሽኝት	9.50 -10.25 "	9፡50 -10፡25 "

16. ሥራ /ግላዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያለው ተግባር/ 2 ክ/ጊዜ ሆኖ በመምህራኑ በሚዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት 50 ደቂቃ የሚሸፈን ይሆናል፣

* ማሳሰቢያ 1 / በሣምንት ሁለት ቀናት ለትምህርት ከተያዘው ጊዜ ውስጥ የቡድን ሥራ የሚሠሩበት ሰዓት ይሆናል።

2/ የመርሐ ግብሩ የመጀመሪያና የመጨረሻ ሰዓት እንደ

የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

1.7 የመምህራን የሥራ ሰዓት መጠን

- ሕፃናትን በአግባቡ ለማሳደግ፤ ለመንከባከብና ለመደበኛ ትምህርት በብቃት ለማዘጋጀት ለአንድ መምህር/ት/ በሳምንት የሚኖሩት/ራት የሥራ ሰዓት መጠን የሕፃናቱ ምሳና መኝታ በየቤታቸው ከሆነ በሳምንት 30 ሰዓት ይሆናል።
- ይህም
  - 5 ሰዓት ጠዋት ሕፃናትን ለመቀበል፣
  - 13 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ለጨዋታ፤ ለትምህርትና ሥራ ነክ ለሆኑ ፕሮግራሞች፣
  - 11 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ለቁርስ፤ለእረፍት፤ ለክፍል ዝግጅትና ለመሸኛ የሚውለውን ጊዜ ያጠቃልላል።
  - ለሕፃናት ምግብና መኝታ በአፀደ ሕፃናቱ ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ በሳምንት 40 ሰዓት ይሆናል።

ይህም በዝርዝር ሲታይ፣

- 5 ሰዓት ጠዋት ሕፃናትን ለመቀበል፣
- 13 ሰዓት ከ20 ደቂቃ ለጨዋታ፤ ለትምህርትና ሥራ ነክ ለሆኑ ፕሮግራሞች፣
- 21 ሰዓት ከ40 ደቂቃ ለቁርስ፣ለምሳ፣ለመፀዳዳት፣ ለመኝታ፣ ለእረፍት፣ ለክፍል ዝግጅትና ለመሸኛ የሚውለውን ጊዜ ያጠቃልላል።

1.8 የማስተማር ዘዴዎች

በቅድመ መደበኛ ፕሮግራም ለሕፃናት በጨዋታ መልክ የሚሰጡአቸው ተግባራት ከሕፃናቱ የአእምሮና የአካል ብቃት ወዘተ ጋር የሚጣጣሙና ለወደፊት ዕድገታቸው የጐላ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው። ስለሆነም በዚህ ደረጃ ለሕፃናት የሚሰጠው መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ሳይሆን ለሕፃናቱ ዕድገት መሠረት የሚሆኑ ክንውኖች (developmental activities) ስለሆኑ የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች በሙሉ የሕፃናትንና የመምህራን የጋራ ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው። ስለሆነም በግልም ሆነ በጋራ እንዲካሄዱ የሚዘጋጁ እንቅስቃሴዎች የሕፃናትን የአካል የአእምሮ የስሜትና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ መሆን አለባቸው።

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ህፃናት የበለጠ ውጤታማ የሚሆኑት ለእነርሱ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በተለያዩ የማስተማር ዘዴዎች ተደግፈው ሲቀርቡ ነው።

በዚህ ደረጃ መምህራን የሚከተሉትን የማስተማር ዘዴዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።

- የቡድን ጫወታ
- የግል ጫወታ
- ሚና ጫወታ
- ሠርቶ ማሳየት
- የመስክ ጉብኝት /በመምህራን የቅርብ ክትትል/ ማወያየት፣
- የቃል ዘገባ

– ገለጻ /ሕፃናትን አሳታፊ የሆነ/ወዘተ ናቸው።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ሕፃናት የሚገመገሙት ፈተና በመስጠት ሣይሆን በተከታታይ የምዘና ዘዴ ነው።

1.9 ከመምህራን የሚጠበቅ ባህሪ

– ርህራሄ
– ትዕግስት
– ለህፃናት ልዩ ፍቅር ያላቸው
– ደባል ፀባይ የሌላቸው
– ጥሩ ስነምግባር
– ለሙያው ያለው ፍቅር
– የአካባቢውን ባህልና ወግ የሚያውቅ

የቅድመ መደበኛ ትምህርት መምህራን የአፍ መፍቻና የእንግሊዝኛ ቋንቋዎችን ጨምሮ ስለሚያስተምሩት ትምህርት ይዘት፣ ስለሚያስተምሩዋቸው ሕፃናትና በመካከላቸው ሊኖሩ ስለሚችሉ የችሎታና የፍላጐት ልዩነቶች እና እንደዚሁም ለልዩነቶቹ አያያዘ አስፈላጊ የሆኑ ሙያዊ እውቀትና ክህሎት መጨበጥ ይጠበቅባቸዋል። እንዲሁም በሙያዊ ተግባር ክንውን ሂደት ይህን እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን ከተገቢው ሙያዊ ሥነ ምግባር ጋር በማቀናጀት በሕፃናት እንቅስቃሴ ፕሮግራም ላይ በተሟላ መልክ መሳተፍ ይገባቸዋል።

- ለቅድመ መደበኛ ፕሮግራሙ የሚሆኑ ክንውኖችን ከሕፃናት የአካል የስሜትና ማህበራዊ ወዘተ ዕድገት ጋር በማገናዘብ ሥራ ላይ ሊውሉ የሚችሉትን በማቀድ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

1.10 የቅድመ መደበኛ መርሐ-ግብርን ያጠናቀቁ ሕፃናት ባህርይ፣

- በአካልና በአእምሮ የበለፀጉ፣ ስሜትን መግለጽና ውበት ማድነቅ የሚችሉ፣
- ለምርምር፣ለፈጠራና ለሥራ ፍቅር ያላቸው፣ በራስ የሚተማመኑና በሥነ ሥርዓት የታነፁ፣
- ሆሂያትንና አሃዞችን በሥርዓት መለየትና መቅረጽ፣ ተራን ጠብቆ ሃሣብን መግለጽና ማዳመጥ የሚችሉ፣

- በአካባቢያቸው ለማህበራዊ ኑሮ የነቁና ለመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁ ናቸው።

1.11 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚቋቋሙባቸው አካባቢዎችና የሕንፃው ሁኔታ

1.11.1 የቦታ አመራረጥ፤

- አካባቢው የፀዳና ለሕፃናት ተስማሚ የሆነ ንጹህ አየር ያለው፣ ከቆሻሻ መጣያ፣ ከፍሳሽ፣ ከወንዞች፣ ከኩሬዎች፣ ከረግረግና ከገደል የራቀና ሕፃናትን የሚተናኮሉ አውሬዎችና ነፍሳት የሌሉበት፤
- ለትራፊክ አደጋ የማያጋልጥ፤
- በቀላሉ ንጹህ የመጠጥ ውሃ የሚገኝበት፤
- ከመንገድ ዳር ገባ ያለ፤
- ከመጠጥ ቤቶች የራቀ፤
- ቢቻል በአቅራቢያው ሆስፒታል፤ ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ያለው ሆኖ ተላላፊ በሽታ ከሚከላከሉ እንደ ሳንባ ነቀርሳ መከላኪያና ከመሳሰሉት የጤና ድርጅቶች አቅራቢያ ባይሆን የተሻለ ነው።
- ፀጥታ የሰፈነበት አካባቢ፤ የእንጨት መሰንጠቂያ፤ ወፍጮ ቤት፣ ሙዚቃ ቤት ... ወዘተ ከመሳሰሉት የራቀ፤
- ሰፊ ቦታና በቂ የመጫወቻ ሥፍራ ያለው፤
- ለሕፃናቱ እንዳይርቅ ከቤታቸው በአማካይ ከአንድ ኪሎ ሜትር ያልራቀ ቦታ ሊመረጥለት ይገባል።
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሕንፃዎች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከስሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬት፣ ከሸክላና ወዘተ ማቴሪያሎች ሊሠሩ ይችላሉ።

1.11.2 የምድረ ግቢ ገጽታና አደረጃጀት

- አጥሩ በአካባቢው ከሚገኙ ጥሬ ዕቃዎች የተሠራ ሆኖ ቁመቱ ከ1.5 ሜትር ያላነሰና በሕፃናት ላይ አደጋን የማያስከትል መሆን አለበት።
- አጥሩ አሾሃማ አጥር መሆን የለበትም፤

- ለጥላና ለመዝናኛ የሚያገለግሉ ዛፎች ሊኖሩት ይገባል፤
- ግቢው ልዩ ልዩ የመጫወቻና የአካል ማጐልመሻ መሣሪያዎች ያሉት ሆኖ የመሬቱ ወለል ለሕፃናቱ ልዩ ልዩ የአካል እንቅስቃሴ የሚያመች የተስተካከለ መሆን አለበት።
- ድብብቆሽ የሚጫወቱበት፣ የአሸዋ ሣጥን፣ የአበባና የአትክልት ቦታዎች ያሉት፣ሆኖ ስለዕፅዋት፣ ስለዘር፣ ስለተክል ወዘተ. ሊማሩበት የሚያስችል መሆን አለበት።

1.11.3 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መጠን

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት በአንድ ክፍል ውስጥ ከ40 ሕፃናት በላይ ማስተናገድ የለበትም። አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እያንዳንዳቸው 7x9=63 ካ.ሜ የሆኑ እስከ 6 ክፍሎች ይችላል። በእነዚህም ክፍሎች ውስጥ 6 x 40=240 ሕፃናት ሊያስተናግድ ይችላል። በአንድ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ሕፃናት አንድ መምህር /ት/እና አንድ ረዳት መምህር/ት/ ያስፈልጋሉ። ይህም ማለት 6 ክፍሎች ላሉት አንድ ቅድመ መደበኛ ተቋም 6 መምህራንና 6 ረዳት መምህራን በድምሩ 12 ያስፈልጋሉ ማለት ነው።

1.11.4 የምድረ ግቢና የሕንፃዎች አደረጃጀት

- የምድረ ግቢና የሕንፃ አደረጃጀት ለልዩ ፍላጐት ተማሪዎች በሚመች መልኩ ይደራጃል ይህም።
  - የምድረ ግቢው ስፋት እንደ መማሪያው ክፍሉ ብዛት ከ500-3000 ሜትር ካሬ ያለው ይሆናል።
  - በግቢው ውስጥ የሕንፃው ወይም የህንፃዎቹ አቀማመጥ ለሕፃናቱ የውጭ መጫወቻዎች ዝግጅት እንዳያውክ ሆኖ ይሠራል።
  - የሕፃናት ክፍሎች ሲሠሩ ለያንዳንዱ ሕፃን ከ1.55 ሜትር ካሬ ያላነሰ ቦታ እንዲኖር ሆኖ ይሠራል።
  - የቤቱ በርና መስኮቶች አቀማመጥ ለከፍተኛ ቅዝቃዜ የማያጋልጡ ይሆናሉ።
  - ደረጃዎች እንዳይኖሩት ወይም እንዳይበዙበት ተደርጐ ይሠራል፤

- ለአካል ጉዳተኛ ህፃናት ታሳቢ ያደረገ ህንፃ መሆን አለበት።
- መስኮቶቹ ሕፃናት ወደ ውጭ በሚገባ ማየት የሚያስችሏቸው በሩም ክብደት የሌለውና ሳይፈለግ እንዳይዘጋ ከግድግዳው ጋር የሚያያዝ ማጠበቂያ ሊኖረው ይገባል።

– የቤቱ የውስጥም ሆነ የውጭ ግድግዳ ከወለሉ ቢያንስ፣ 1 ሜትር ከፍታ ድረስ ሻካራ ያልሆነና በሕፃናቱ /አካላት ላይ / እጅ ጉዳት የማያደርስ መሆን አለበት።

– የመፀዳጃ ቤቱ ጣራና ግድግዳ ያለው፤ በቂ አየርና ብርሃን የሚያስገባ፤ ወለሉ በቀላሉ ለማጽዳት የሚቻል፤ የጉድጓዱ ቀዳዳ በሕፃናቱ መጠን ግምት ውስጥ አስገብቶ የተሠራና መግጠሚያ ያለው፣ የእጅ መታጠቢያም አጠገቡ ያለው መሆን አለበት።

– ክፍሎቹ እንደ አካባቢው ሁኔታ ብርሃንን፤ ሙቀትን፤ ብርድን፤ ዝናብንና ትንኞችን ለመቆጣጠር በሚያስችሉ እንደ መጋረጃ፣ መስተዋትና እንዲሁም በሽቦና ከመሳሰሉት የተሠራ የወንፊት መስኮት ሊኖራቸው ይገባል።

1.12 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ሊኖሩት የሚገባ የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች

ተ/ቁ	የሕንፃው ክፍሎች	ባለ 1 ክፍል	ባለ 2 ክፍል	ባለ 3 ክፍል	ባለ 4 ክፍል	ባለ 5 ክፍል	ባለ 6 ክፍል	የአንድ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር	የመማሪያ ቦታ በህንፃ በካሬ ሜትር
1	የመማሪያ ክፍል	1	2	3	4	5	6	7X9	1.55 ሜካ
2	ጽ/ቤት ቢሮ	1	1	1	1	1	1	4.2 X5	
3	ዕቃ ግ/ቤት	1	1	1	1	1	1	2.8X2.5	
4	የምግብ ማብሰያ	1	1	1	1	1	1	5X5.6	
5	ዕቃ ክፍል	1	1	1	1	1	1	2X2.6	
6	የሕፃናት መፀዳጃና መታጠቢያ	1	1	1	1	1	1	9X5	
7	የመምህራን መፀዳጃ	1	1	1	1	1	1	2X2.4	
8	የሠራተኞች መጸዳጃ	1	1	1	1	1	1	2X4.2	
9	የሕፃናት ማረፊያ ክፍል	1	1	1	1	1	1	4X5	
10	ሁለገብ አዳራሽ	1	1	1	1	1	1	8X14.10	
11	የዘበኛ ቤት	1	1	1	1	1	1	2.45X2.45	
12	የገ/ያዥ ቢሮና	1	1	1	1	1	1	3.50 X 7	

ተ/ቁ	የሕንፃው ክፍሎች	ባለ 1 ክፍል	ባለ 2 ክፍል	ባለ 3 ክፍል	ባለ 4 ክፍል	ባለ 5 ክፍል	ባለ 6 ክፍል	የአንድ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር	የመማሪያ ቦታ በህንፃ በካሬ ሜትር
	የትም/ዕቃ ግ/ቤት								
13	የመምህራን ማረፊያ	1	1	1	1	1	1	3.50X7	
14	የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫና የጽዳት ዕቃ ማስቀመጫ	1	1	1	1	1	1	3.50X5.70	
15	የምግብ ዕቃ ግ/ቤት	1	1	1	1	1	1	3.40X3.70	
16	ልዩ ልዩ ኮርነሮች /ማዕዘን/ ልዩ የመማር ፍላጐት ላላቸው ሕፃናት የንግግር ወጌሻ መስጫ ክፍል	1	1	1	1	1	1	4X3.5	

1.13 ለልዩ ልዩ ክፍሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች

1.13.1 ለአንድ መማሪያ ክፍል የሚያስፈልጉ ቋሚ መሣሪያዎች፣

ተ ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	መጠን በሳ/ሜ	ምርመራ
1	ጠመኔና ጥቁር ሠሌዳ	1	50 X 100	
2	የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ	1	50 X 100	
3	የመምህሩ ወንበር	1	40 X 56 X 78	
4	የመምህሩ ጠረጴዛ	1	80 X 100 X 74	
5	የሕፃናት ወንበሮች	40	34 X 24 X 27	
6	የሕፃናት ጠረጴዛዎች	10	68 X 98 X 75	
7	ዕቃ መደርደሪያዎች	3	10 X 200 X 40	
8	የቆሻሻ ማጠራቀሚያ	1		ከሳጠራ/ከፕላስቲክ የተሠራ

ከዚህ ሌላ ልዩ የመማር ፍላጐት ላላቸው ሕፃናት የሚከተሉት መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ። በዚህም መሠረት፤-

1.13.2 መስማት ለተሳናቸው ሕፃናት

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሳያት፤
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያሉ ነገሮች እንዲታይ ማድረጊያ፤
- በከፊል ለሚሰሙት ድምፅ አጉሊ መሣሪያ መጠቀም ለምሳሌ፡-ረዳት የመስሚያ መሣሪያ
- ድምፅ - አልባ የታይፕ መኪና መጠቀም
  ሌሎች መሣሪያዎች
- የዕይታ መሣሪያዎች ብርሃን አስተላላፊ ወረቀት፤ ፊልም፤ ካብሽን፤
  ስላይድ፤ፊልም፣ ቻርት መሳሪያ

1.13.3 ማየት ለተሳናቸው ህፃናት

- አባከሰ
- ብሬል
- ስሌት
- ስታይለስ
- ዘንግ
- ቴፕሪከርደር

1.13.4 የእእምሮ ዕድገት ዝግመት ላለባቸው ህፃናት

- ቴሌቪዥን
- DVD
- የፊዚዩቴራፕ ኳሶች

1.13.5 ለተግባራዊ ትምህርት የሚያገለግሉ መሣሪያዎች

ለቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም የተዘጋጁት መሣሪያዎች ልዩ ፍላጐት ላላቸው ሕፃናትም ጭምር ያገለግላሉ።

1.13.6 የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ዕቃዎች

ተራ ቁጥር	የዕቃው ዓይነት	ብዛት
1	የጥጥ ዕቃ	እንደተገኘ
2	ሶስት መዓዘን ፋሻዎች	
3	ጥቅል ፋሻዎች	
4	የተቀቀሉ የጨርቅ ፖዶች	

ተራ ቁጥር	የዕቃው ዓይነት	ብዛት
5	የተቆራረጡ በራዚዎች	
6	ከፋሻ ጋር የተያያዙ ፓዶች	
7	የላስቲክ ፋሻ	
8	የእጅ ፎጣ	
9	መጠነኛ የእንጨት /ስፕሊንት/	
10	የሕፃናት መመርመሪያ አልጋ	1
11	ፍራሽ	1
12	ብርድ ልብስ	2
13	አንሶላ	4
14	የመድኃኒት ስኒ	2
15	መቀስ	2
16	ወረንጦ	2
17	መርፌ ቁልፎች	እንደተገኘ
18	የቁስል መለጠፊያ ፕላስተር	"
19	የማስታወሻ ደብተር	"
20	ሳሙና ከነመቀመጫው	"
21	የመጠጫ ኩባያ	2
22	ሣህን ትንሽ /ኪድኒ ድሽ/	2
23	ተርንኪ/ለስቲክ/	2
24	የሕክምና ኩራዝ	2

ማሳሰቢያ፣

ከላይ ከተዘረዘሩት መካከል በቁጥር ላልተገለጹ ህክምና ዕርዳታ መስጫ/ዕቃዎችን ብዛት እንደ ሕፃናቱ ብዛት ግምት ውስጥ ያስገባ መጠን መሆን አለበት።

1.13.7 ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል የሚያሰፈልጉ መድኃኒቶች

ተ.ቁ	የመድኃኒቱ ዓይነት	ብዛት
1	የሕፃናት አስፒሪን	እንደተገኘ
2	ቴምፕራ ሲረፕ/ፈሳሽ/	"
3	የሳል ማስወገጃ መድኃኒት	"
4	የተቅማጥ መቆጣጠሪያ መድኃኒት	"
5	ቴትራሳይክሊን የዓይን ቅባት	"
6	ፕላሲል ፈሳሽ	"
7	አዩዲን	"
8	ጀንቪያን ባዩዋሌት	"
9	አልኮል	"
10	ሳልፋ ዱቄር ወይም ቅባት	"
11	ቤንዚን ኮኒየም (የቁስል ማጠቢያ)	"

12	ባለመድኅኒት ፕላስተር	"

ማሳሰቢያ፣

ከላይ የተዘረዘሩ ለመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ መስጫ የሚያስፈልጉ መድኃኒቶች ብዛት በተቋሙ በሚማሩ ሕፃናት ቁጥር ተመጣጣኝ መሆን አለበት።

1.13.8 ለማዕድ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች

ተ ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት
1	ማንቆርቆሪያ	1
2	ብረት ድስት	1
3	የሽክላ ድስት	2
4	ቡሃቃ (ማቡኪያ)	4
5	ባልዲዎች	4
6	የዕቃ መደርደሪያ	1
7	ማብሰያ ምድጃ	1
8	ትናንሽ ማንኪያዎች	40
9	ትናንሽ ማብሰያ ሣህኖች	40
10	የሻይ፣የውሃና የወተት ኩባያ	40
11	የዳቦ ማቅረቢያ ትሪ	5
12	ሜልፋዎች	3
13	ማቡኪያ ሣህን ወይም ገበቴ	1
14	ወንፊትና ሰፌድ	2
15	ቢላዎች	5
16	መጥበሻዎች	2
17	የዕቃ መወልወያ ንጹህ ጨርቆች ባለ 1 ሜትር	5

1.13.9 አላቂ የመጫወቻ ዕቃዎች

ተ ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	የተሠራበት ማቴሪያል
1	የመገንቢያ ብሎኮች	4 ሴት	ከሸክላ፣ፕላስቲክ፣እንጨት
2	አሻንጉሊቶች	እንደተገኘ	ከጨርቅ፣ፕላስቲክ
3	ለቤተሰብ ኮርነር የሚያስፈልጉ ሲኒዎች	"	ከሸክላ፣ከቆርቆሮ
	ጀበናዎች	"	ከሸክላ፣ከቆርቆሮ
	ማንኪያዎች	"	ከሸክላ፣ከቆርቆሮ
	ሣህኖች	"	ከሸክላ፣ከፕላስቲክ፣ከቆርቆሮ
	ትናንሽ የአሻንጉሊት አልጋዎች	"	ከእንጨት፣ከፕላስቲክ
4	ለሕክምና ኮርነር የሚያስፈለጉ		

ተቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	የተሠራበት ማቴሪያል
	▪ ሽርጦች	4	ከጨርቅ
	▪ ስሪንጆች	እንደተገኘ	ከጎማ፣ፕላስቲክ
	▪ ማዳመጫዎች	"	ከዕንጨት
	▪ ፋሻዎች	4	ከጨርቅ
	▪ የመድኃኒት ብልቃጦች	እንደተገኘ	ከፕላስቲክ፣ከጠርሙስ
	▪ እንደ ስትሬቸር የሚያገለግሉ አልጋዎች	"	ከሣጠራ፣ከእንጨት
5	ለሱቅ ኮርነር የሚያስፈልጉ ሚዛኖች	"	ከፕላስቲክና ከብረት
	▪ ሚዛን	"	ከፕላስቱክ፣ከብረት
	▪ ባዶ የእስክሪቢቶ ቀፎዎች	እንደተገኘ	ከፕላስቲክ
	▪ ባዶ የክብሪት ቤቶች	"	ከእንጨት
	▪ የተለያዩ የሕፃናት ልብሶች	"	ከጨርቅ
	▪ ቆርኪዎች	"	ከቆርቆሮ
	▪ ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶች	"	ከአፈር፣ከሲሚንቶ
	▪ የገንዘብ ኖቶችና ሳንቲሞች	"	ከወረቀት፣ከፕላስቱክ
6	ለሳይንስ ኮርነር ▪ ልዩ ልዩ የሳይንስ ኪቶች	"	ከወረቀት፣ ከፕላስቱክ ከወረቀት፣ከዕንጨት፣ከቆርቆሮ፣ ከጭቃ፣ወዘተ
7	ለንብረተሰብ ኮርነር ▪ ልዩ ልዩ ሥዕሎችና የአካባቢ አልባሳት	"	ከጨርቅ፣ ወረቀት፣ጭቃ
8	ለቋንቋና የንባብ ኮርነር ▪ ሥዕሎች፣ጋዜጦችና የሕፃናት መፃሕፍት	እንደተገኘ	
9	ለሂሣብ ኮርነር ▪ ልዩ ልዩ ቁጥሮች መቁጠሪያ መማሪያዎችና ምልክቶች		ከፕላስቱክና ከእንጨት፣ከወረቀት ከጭቃ
10	ለሙዚቃ ኮርነር ▪ ልዩ ልዩ የአካባቢና ባህላዊ መሣሪያዎች	"	ከዕንጨት፣ከቆዳ፣ከጅማት ክር
11	ለሥነ ሥዕል ኮርነር		ከጨርቅ፣ከእንጨትና ከሸክላ

1.13.10 ቋሚ የውጭ መጫወቻ መሣሪያዎች

ተ/		ብዛት	መጠን	ዓይነት	ምርመራ

ቁ	የዕቃው ዓይነት				
1	ኳሶች	10 /ለአርባ ሕፃናት/			1 ኳስ ለአራት ሕፃናት
2	ጐማዎች	10			
3	ዥዋዥዌ	2			
4	ሚዛን	2			
5	ሸርተቴ	2			
6	ሜራጎራውንድ	2			
7	መሰላል	2			
8	የመሸለኪያ ቱቦዎች	2			
9	የአሸዋ ሣጥን	2			

ማሳሰቢያ፣

ከላይ የተገለፀው እያንዳንዱ የዕቃ ዓይነት ብዛት ለ40 ሕፃናት ሲሆን የሕፃናቱ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የዕቃዎቹም ብዛት እንደሚጨምር ይጠበቃል።

1.13.11 ለርዕሰ መምህር ቢሮ የሚያስፈልጉ ዕቃዎች

ተ				
ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት	መጠን	ዓይነት
1	ወንበር	4	40x56x68	
2	ባለኪስ ጠረጴዛ	1	80x50x74	
3	የመፀሐፍ መደርደሪያ	1	10x200x40	
4	የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ	1		ከሳጠራ/ከፕላስቲክ የተሠራ
5	የቆሻሻ ማጠራቀሚያ	1		
6	የእርሳስ መቅረጫ	1		
7	ስቴፕለር	1		
8	ማስመሪያ	1		
9	መዛግብት	እንደአስፈላጊነት		
10	የፋይል አቃፊዎች	"		
11	ወረቀት	"		
12	ክላስር	"		
13	የወረቀት መርፌ	"		
	ካርቦን			

1.14 የሰው ኃይል ምደባ

1.14.1 የመምህራንና ሠራተኞች ምደባ፤

- የቅድመ መደበኛ ተቋም ርዕሳነ መምህራን፤ መምህራንና ሞግዚቶች ሴቶች ቢሆኑ ይመረጣል፣
- አንድ መምህር / ት 40 ሕፃናትን ያስተናግዳል/ታስተናግዳለች፣
- 40 ሕፃናት ለምታስተምር መምህርት አንድ ረዳት መምህርት ትመደባለች፣

  አንድ ሞግዚት ለ40 ሕፃናት ትመደባለች፣
- ለአንድ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም እንደ ክፍሎችና ሕፃናቱ ብዛት የሰው ኃይል ይመደባል።

1.14.2 የመምህራንና ሠራተኞች ብዛት፣

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም መጠን	የሕፃናት	የር/መምህር	የመምህራን	የረዳት መምህራን	የሞግዚት	የጥበቃ ሠራተኞች	ተላላኪ	የጽዳት ሠራተኞች	የጤና ባለሙያ
የመማሪያ ክፍል	ብዛት	ብዛት	ብዛት	ብዛት	ብዛት		ብዛት	ብዛት	
ባለ 1 መማሪያ ክፍል	40	1	1	1	1	2	1	1	1
ባለ 2 መማሪያ ክፍል	80	1	2	2	2	2	1	1	1
ባለ 3 መማሪያ ክፍል	120	1	3	3	3	2	1	2	1
ባለ 4 መማሪያ ክፍል	160	1	4	4	4	2	1	2	1
ባለ 5 መማሪያ ክፍል	200	1	5	5	5	2	1	2	1
ባለ 6 መማሪያ ክፍል	240	1	6	6	6	2	1	2	1

ማሳሰቢያ፣

የህፃናቱ ቁጥር በጨመረ ቁጥር የሰው ኃይል ምደባው በተገለጸው ሥሌት መሠረት የሚጨምር ይሆናል።

* ከአንድ እስከ ሁለት መማሪያ ክፍሎች ላላቸው ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት በሥራ ልምድና በአገልግሎት ዘመን ብልጫና በሥራ ትጋት የተሻለ/ች አንድ/ዲት መምህር/ት ከማስተማር ሥራው/ዋ በተጨማሪ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኃላፊ መምህር በመሆን ያገለግላል/ ታገለግላለች። ነገር ግን ከሁለት የመማሪያ ክፍል በላይ ላላቸው ትምህርት ተቋማት ራሱን የቻለ ኃላፊ ይመደብለታል።

" በአንድ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ከሚገኙት ሕፃናት ውስጥ ልዩ ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት ብዛት ከ5%-10% ቢሆን ይመረጣል።

1.14.3 የመምህራንና የሠራተኞች የትምህርት ደረጃ፣

- የመምህራን የትምህርት ደረጃ በቅድመ መደበኛ ትምህርት ዘርፍ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች፣
- የረዳት መምህር/ት/የት/ደረጃ 10ኛ ክፍል አጠናቆ/ቃ በአፀደ ሕፃናት ትምህርት በሰርተፊኬት የተመረቀ/ች፣
- ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸውን ሕፃናት ለማስተማር ከላይ ከተገለጸው መመዘኛ በተጨማሪ በልዩ ትምህርት አጫጭር ሥልጠናዎች የወሰዱ መምህራን ሊሆኑ ይገባል።
- የንግግር ወጌሻ የ10ኛ ክፍልን አጠናቅቆ/ቃ/በአፀደ ሕፃናት መምህርነት የሰለጠነ/ች/ የምሰክር ወረቀት ያለው /ያላት/እንዲሁም በልዩ ትምህርት የሰለጠነ/ች/፣
- የሞግዚት የት/ደረጃ 10ኛ ክፍልን ያጠናቀቀች ሆኖ ቢቻል በሥርዓተ ምግብ ሥልጠናና በምግብ ዝግጅት ልምድ ያላት፣
- የጥበቃ ሠራተኞች የት/ደረጃ ቢያንስ 8ኛ ክፍል ያጠናቀቁ ይሆናሉ፣
- ማሳሰቢያ፣ በልዩ ትምህርት የሰለጠኑ መምህራን የሚያስፈልጉት ልዩ የመማር ፍላጐት ያላቸው ሕፃናት ባሉበት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ነው።

1.15 ልዩ ልዩ አስፈላጊ የቅድመ መደበኛ የትምህርት መመሪያዎች

- የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣
- መርሀ ትምህርት፣
- የመምህሩ መምሪያ፣
- የተማሪው የንባብ፤ የተረትና ሥዕላዊ መጻሕፍት፣
- ልዩ ልዩ የት/መርጃ መሣሪያዎች፣
- የቅድመ መደበኛ ትምህርት መመሪያ፣
- ማየት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
- መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
- የአእምሮ ዕድገት ዝግመት ያለባቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣

ሕግ ነክ ሰነዶች

- ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቪንሽን፣
- የትምህርት ሕግ፣
- የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣
- ስለግል የት/ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ፤
- የማዕከልና/የክልል አሰፈጻሚ አካላትን ሥልጠን ለመወሰን የወጣ አዋጅ 4/71/98
- የተሻሻለው አዲሱ የሠራተኞች ህግ አዋጅ ቁጥር 377/1996

1.16 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ከወላጆች፣ ከህብረተሰቡና ከአመራር ጋር ሊኖረው የሚገባ ግንኙነት

1.16.1 የወላጆች ሚና

የወላጆች ተሳትፎ በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጆች ስኬታማነት አስተዋጽየ ከሚያበረክቱት በጣም ጉልህ ነገሮች መካከል አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ያመለክታሉ። ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ መሉ ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ የተማሪዎች የውጤት ደረጃ ያድጋል የልጆቻቸው ከትምህርት ገበታ ላይ የመቅረት ሁኔታ ይሻሻላል። እንደዚሁም የቤት ሥራዎቻቸውን በወቅቱ እንዲሠሩ ከመርዳቱ ሌላ ለባህርያቸው መሻሻልም ትርጉም ያለው አስተዋፃኦ ይኖረዋል።

ስለትምህርት ያላቸው ዝንባሌም የበለጠ አዎንታዊ ይሆናል። ይህም በበኩሉ ተማሪዎች ሳያቋርጡ ትምህርታቸውን በማጠናቀቅ ለከፍተኛ ውጤት እንዲበቁ ያስችላል።

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙ ህፃናት በአካል፣ በአእምሮ፣በማኅበራዊና በስሜት ገና ያልዳበሩ በመሆናቸው ኃላፊነቱን ሙሉ ለሙሉ ለተቋማቱ ከመተው ይልቅ ወላጆች በተቋማቱ በመገኘት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል።

ሕፃናት በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት መሳተፍ ለወደፊት ሕይታቸው መሠረት የሚጣልበት ሲሆን፣ ፕሮግራሙን ለማካሂድ የሚያስፈልገውን ወጪ መንግሥት ብቻውን ስለማይችል ወላጆች እነዚህን ተቋማት በገንዘብና በማቴሪያል በመደገፍ የሕፃናቱ የተሟላ አገልግሎት እንዲያገኙ ወላጆች የበኩላቸውን ድርሻ መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

1.16.2 የአመራር ሚና

የትምህርት አመራርና አስተዳደር ባልተማከለ መንገድ የሚካሄድና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው።

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋማት አመራርና አስተዳደር የተቋማቱን፣ የወላጆችንና የአካባቢውን ማኅበረሰብ አባላት እና ባለድርሻዎች ያቀፈና ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎን ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን ተሳትፏቸውን በሚከተሉት መድረኮች ሊገልጹ ይችላሉ።

- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኮሚቴ ወይም ቦርድ ውስጥ ኅብረተሰቡን በመወከል
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም የወላጅ ኮሚቴ ውስጥ ወላጆችን በመወከል

1.16.3 የኅብረተሰብ ሚና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋሙና የአካባቢው ማህበረሰብ ግንኙነት የተጠናከረ መሆን ይገባዋል።

የዚህም ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

- የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ምን እየሠራ እንዳለና የፕሮግራሙን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ሃላፊነት ለማካፈል፣ ለምሳሌ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋሙ ኃላፊነቱን በብቃት እየተወጣ መሆኑንና ስለ ዓላማውና የዓላማውን ተግባራዊነት ለኅብረተሰቡ ማሳወቅ ከኅብረተሰቡ የሚሰጡ አስተያየቶችን መሠረት በማድረግ የተቋሙን የሥራ አመራር ሥራውን እንዲያሻሽል ለማድረግ፣
- ሕፃናቱ በፕሮግራሙ ስላላቸው ተሳትፎና ውጤት ወላጆች አውቀው ተገቢውን ክትትል ለማድረግ፣
- የወላጆችንና የመምህራንን ግንኙነት ለማጠናከርና የፕሮግራሙ ውጤት ይበልጥ የተሻለ እንዲሆን ለማስቻል
- በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ኮሚቴ ወይም ቦርድ ውስጥ በመሳተፍ፣

  ተቋሙን ለማጠናከር በሚቀርብ ዕቅድ ላይ ውይይት በማካሄድ መርምሮና አሻሽሎ ለማጽደቅ እና አፈጻጸሙንም ለመከታተልና ለመቆጣጠር፣

  ሥርዓተ ትምህርቱ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ተጣጥሞና ተዘምዶ ለሕፃናቱ መቅረቡን ለመከታተልና ሃላፊነት ለመስጠት... ወዘተ ይሆናል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መለኪያ

(Standard)

የመጀመሪያ ረቂቅ

ግንቦት ወር 2001 ዓ.ም

ማ ው ጫ

ገጽ

መግቢያ

1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረጃ መለኪያ (Standard) 1
   1.1 የትምህርት ሥርዓት መዋቅር 1
   1.2 የት/ቤት ህንፃ አደረጃጀትና የአካባቢ ሁኔታዎች 2
      1.2.1. የት/ቤት ህንፃ አሠራር 2
      1.2.2. የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች 2
      1.2.3. የምድረ ግቢ ገጽታ 2

   1.3 የት/ቤት መጠን 3
      1.3.1. የክፍል መጠን አደረጃጀት 3
      1.3.2. የምድረግቢ ሥፋት 3
      1.3.3. የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መጠን 4
         1.3.3.1. የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ላላቸው ት/ቤቶች 4
         1.3.3.2. ሁለቱም ሳይክል ለያዙ /1-8/ ት/ቤቶች 4

   1.4 አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶች 5
      1.4.1. አንድ መማሪያ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ ቁሳቁሶችና መጠናቸው.... 5
      1.4.2. 1-8 ክፍል ለቤተመጽሐፍት የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎችና መጠናቸው 5
      1.4.3. ከ1-8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለር/መምህራን፣ ለቢሮና ለመምህራን ማረፊያ ክፍል የሚያስፈለጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት 6

      1.4.4. ከ1-8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለዕቃ ግምጃ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት 6
      1.4.5. በመጀመሪያ ደረጃ የሳይንስ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ እቃዎችና ብዛታቸው..... 6
      1.4.6. ለትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የሚያስፈልጉ መማሪያዎች. 7

   1.5 የሰው ኃይል ምደባ 7
      1.5.1. በየሳይክሉ ሊኖሩ የሚገቡ የተማሪዎች ብዛት..... 7
      1.5.2. የተማሪ መጽሓፍት ጥምርታ 8
      1.5.3. የመምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ ... 8
         1.5.3.1. ለመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ 8
         1.5.3.2. ለሁለተኛ ሳይክል /5-8/ 8
         1.5.3.3. የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም 9

   1.6 የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት 9
      1.6.1. የትምህርት ጊዜ አደረጃጀት 10
      1.6.2. ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች 10
      1.6.3. የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በትምህርት ዓይነት..... 13
      1.6.4. የትምህርት ቤት አመራር ሚና 14
      1.6.5. የት/ቤት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም 16
         1.6.5.1. የመምህራን የሥራ ሰዓት አጠቃቀም 17

1.6.5.2. ከመምህራን የሚጠበቅ ባህሪ 18
1.6.6. የልዩ ፍላጐት ትምህርትን ፕሮግራም 19
1.6.6.1. የአእምሮ ውሱንነት ላላቸው /1-4/ 19
1.6.6.2. ማየት ለተሳናቸው /1-4/ 19
1.6.6.3. መስማት ለተሳናቸው /1-4/ 20
1.6.6.4. የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራንና ሠራተኞች ድልድል 20

1.6.7. የሙሉ ቀን ትምህርት ፕሮግራም 21
1.6.8. የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም 21
1.6.9. የመማር ማስተማር መመሪያዎች 22
1.6.9.1. አጠቃላይ መመሪያዎች 22
1.6.9.2. የልዩ ፍላጐት ትምህርት መመሪያዎች 22
1.6.9.3. ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያዎች 23

1.7. የማስተማር ዘዴ (Teaching Methodology) 23
1.8. የትምህርት ምዘናና የማለፊያ ነጥብ 24
1.9. የተማሪዎች ሚና (students' role)..... 25
1.10. የወላጆች ሚና (parents role 26
1.11. ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ማሳወቅ የሚገባው 27
1.12. በትምህርት ሥራ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ 28
1.13. ልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች 28
1.13.1. የሬድዮ ትምህርት 28
1.13.2. ቤተሙከራ 32
1.13.3. ቤተመጻሕፍት 32
1.13.4. የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከላት አደረጃጀት 34
1.13.4.1. በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ የትምህርት ማበልፀጊያ የትም/መርጃ መሣሪያዎች ከማዘጋጀት አኳያ ለኖር የሚባው ስታንዳርድ 35
1.13.4.2. በት/ቤት ማበልፀጊያ ማዕከል ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ የእጅ ሥራ መሥሪያ መሣሪያዎች 35
1.13.4.3. ለየትም/ዓይነቱ ሊኖሩ የሚገባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች 35

1.13.5. የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍል 40

1.13.6. ለአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሚያስፈለጉ የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት መሣሪያዎች 42

1.14. የትምህርት ደረጃ ማጠናቀቂያ ስታንዳርድ 43
1.14.1. በየክፍል ደረጃውና በእየርከኑ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች 43

1.15. በየእርከኑ መጨረሻ የሚጠበቁ የተማሪዎች ፕሮፋይሎች /ባህሪያት/. 44
1.15.1. የመጀመሪያ ደረጃ የ4 ዓመት ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች ባህሪ 44
1.15.2. የመጀመሪያ ደረጃ የ8 ዓመት ትምህርት ያጠናቀቀ ተማሪ ባህሪ 45

መግቢያ

ትምህርት የዕድገት መሠረት ነው። ሰዎች የጠራ ራዕይ እንዲኖራቸውና ራዕያቸውንም ወደተግባር ለመለወጥ የሚያስችላቸውን አቅም የሚያጐለብት በመሆኑ ቀጣይነት ወዳለው የልማት ዕድገት የሚያሸጋግር ዋነኛ መሣሪያ ነው።

የትምህርት ዓላማ የተቀመጠለትን ግብ ሊመታ የሚችለው በአንድ አገር የሚሰጠው ትምህርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ ሲገኝ ነው።

የትምህርት ጥራት እንደየአገሮቹ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት የተለያየ ቢሆንም እያንዳንዱ አገር ሊደርስበት የሚገባ የእድገት ደረጃ መሠረት ያደረገ የጥራት መለኪያ (Standard) ሊኖረው ይገባል።

በአንድ አገር የትምህርት ሥርዓት ውስጥ የትምህርት መለኪያ መኖር አስፈላጊነት የትምህርቱን ጥራት በተለያዩ መንገዶች ለማረጋገጥ ስለሚረዳ ነው። ይህም የትምህርቱን አጠቃላይ ፕሮግራም በመፈተሽ ሥ/ትምህርቱን፣ የመምህሩን የማስተማር ዘዴንና የግምገማ ሂደትን፣ የመምህራን ሥልጠናንን እና የባለድርሻ አካላትን ሚና በመከለስ የትምህርቱን የጥራት ደረጃ ከፍ እንዲል በማድረግ ረገድ ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆኑ ነው።

መንግሥታችንም ይህን እውነታ በውል በመገንዘብ ለትምህርቱ ዘርፍ የተለየ ትኩረት በመስጠት ትምህርትን ከማስፋፋትና ለሁሉም ዜጎች በእኩል ደረጃ ከማዳረስ በተጨማሪ የትምህርት ጥራት ጉዳይ የተሻለ ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል። ለዚህም በትምህርት ዙሪያ የሚታዩትን የጥራት ችግሮች ለማስወገድና ጥራቱን ለማስጠበቅ የጥራት ማስጠበቂያ ፓኬጅ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል።

የትምህርቱ ዘርፍ ከተያዘለት ግብና ዓላማ አኳያ እየተካሄደ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚያስችል የጥራት መለኪያ (Standard) በ1987 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ የዋለ ቢሆንም ባለፉት 16 ዓመታት ውስጥ በትምህርቱ ዘርፍ ላይ በርካታ ለውጦች የተካሄዱ በመሆናቸው እነዚህን ለውጦች ማዕከል ያደረገ መለኪያ (Standard) ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ስለሆነም ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መለኪያ (Standard) እንደሚከተለው ተሻሽሎ ቀርቧል።

1. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረጃ መለኪያ (Standard)

ዓላማ፡-

- የትምህርቱ ዘርፍ መንግሥት ከቀየሰው የትምህርት ፖሊሲና የልማት ጐዳና ጋር አብሮ መጓዙን ለማረጋገጥ፣
- በየደረጃው የተማሪዎችን ብቃት ክህሎትና አመለካከት ለማወቅ፣
- በመንግሥት ለትምህርቱ ዘርፍ የሚመደበው የሰው ኃይልና በጀት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለመገንዘብ፣
- በመንግሥትና በሌሎች ት/ቤቶች መካከል በትምህርቱ ዘርፍ ወጥ የሆነ የትምህርት ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ፣
- የአገራችን የትምህርት ጥራትና ደረጃ ከዓለም አቀፍ የትምህርት ጥራትና ደረጃ ጋር ያለው ትስስር ለመረዳት፣

1.1 የትምህርት ሥርዓት መዋቅር

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የቅድመ መደበኛ ትምህርት የተከታተሉም ሆኑ ያልተከታተሉ ከ7 እስከ 14 ዓመት እድሜ ላላቸው ህፃናት በሁለት ሳይክሎች ማለትም 1ኛ ሳይክል ከ1ኛ-4ኛ ክፍሎች፣ 2ኛ ሳይክል ከ5ኛ - 8ኛ ክፍሎች ተከፍሎ የሚሰጥ ሆኖ በ8 ዓመታት ውስጥ የሚጠናቀቅ መሠረታዊ ትምህርት የሚሠጥበትና ለሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ የሚያዘጋጅ ነው። የልዩ ፍላጐት ትምህርትም ይህንኑ መሠረት ያደረገ አደረጃጀት ይኖረዋል።

የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አሰፈላጊነት፡-

- ለተማሪዎች መሠረታዊ ትምህርትን በመስጠት አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማህበራዊ እድገትን ለማዳበር፣
- ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ተግባራትና ምርትን ለማስተዋወቅ፣
- ተማሪዎችን ለቀጣይ ትምህርት፣ ስልጠናና ለሥራ ዓለም የሚያዘጋጃቸው እውቀትን፣ ክህሎትንና አመለካከትን እንዲጨብጡ በማድረግ በደረጃው የምናፈራቸው ተማሪዎች ምርታማ፣ሥራ ፈጣሪና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ግንባታ የበኩላቸውን የሚወጡ እንዲሆኑ ማስቻል።

1.2 የት/ቤት ህንፃ አደረጃጀትና የአካባቢ ሁኔታዎች

1.2.1. የት/ቤት ህንፃ አሠራር

በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ህፃናት በአካልም ሆነ በአእምሮ ያልዳበሩ በመሆናቸው ምቹ የመማሪያ አካባቢ ሊኖራቸው ይገባል።

ተማሪዎችን በብቃት ለማስተማር የት/ቤት ህንፃ ሁኔታና ት/ቤቱ የሚገኝበት አካባቢ አመቺነት፣ የተማሪዎችንና የመምህራን ብዛት መሠረት ያደረጉ የትምህርት ቁሳቁሶችን ማሟላትና የትምህርቱን ፕሮግራም አደረጃጀትንም አመቺ በሆነ መልክ ማደራጀት በተማሪዎች ተፈላጊ ባህሪያት ግንባታ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ስላላቸው በሥራ ላይ የሚገኙም ሆነ ወደፊት የሚከፈቱ ት/ቤቶች በብቃት መደራጀት ይኖርባቸዋል።

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ህንፃ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ የአየር ንብረትና የማቴሪያል አቅርቦት ከሲሚንቶ፣ ከአሸዋ፣ ከብሎኬትና ከሸክላ ወዘተ... ማቴሪያሎች ይሠራል።

1.2.2. የቦታ አመራረጥ መመዘኛዎች

ተማሪዎች ከመኖሪያ ክልላቸው ከ 2 ኪሎ ሜትር በማይበልጥ ርቀት ተመላልሰው መማር የሚችሉበት ሆኖ ት/ቤቱ የመማር ማስተማር ተግባር ከሚያደናቅፉ ሁኔታዎች ማለትም ከዋና መንገድ፣ ከአዋኪ ድምፅና ጫጫታ፣ ከመጥፎ ጠረን፣ ከመጠጥ ቤት፣ ከከፍተኛ ትራፊክ ፍሰት፣ ከወንዞችና ገደላማ ቦታዎች፣ ከገበያና ከፋብሪካ እንዲሁም የተማሪውን ስነምግባር ከሚያበላሹ ከቪዲዮ ቤቶችና ተለጣፊ ሱቆች ከመሳሰሉት የራቀ መሆን ይኖርበታል።

1.2.3. የምድረ ግቢ ገጽታ

- እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ምድረግቢው በድንጋይ፣ በብሎኬት፣ በእሾህ አልባ ሽቦና በእንጨት አጥር ሙሉ በሙሉ የታጠረና የተከበረ፣
- የመማሪያ ክፍሎች፣ የአስተዳደር ቢሮዎችና ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ክፍሎች እንደየሥራ ባህሪያቸውና እንደየአገልግሎታቸው አመቺነት የተሠሩ፣
- ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ምቹ የእግር መንገድ የተሠሩላቸው፣
- በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታ /ሥፍራ/ ያለው፣

- ንፁሕ የመጠጥ ውሃ አገለግሎት ያለው፣
- የመዝናኛና መጫዎቻ ሜዳዎች ያሉት ሆኖ ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ ትምህርቶችም ተመጣጣኝ ቦታ ያለው፣
- እንደአጠቃላይ የህንፃው አቀማመጥም ሆነ የግቢው ሁኔታ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ፣ ሳቢና ማራኪ የሆነ፣

1.3 የት/ቤት መጠን

የአንድ ት/ቤት መጠን በመማሪያ ክፍሎችና በሚኖሩት የተማሪዎች ብዛት የሚወሰን ሲሆን የመማሪያ ክፍሎች ብዛት ደግሞ በተማሪ ቁጥር ይወሰናል።

የልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ከሌሎች በተለየ ክህሎትንና ትምህርትን ለመስጠት የሚያስችሉ ሌሎች ተጨማሪ መማሪያ ክፍሎችና ተስማሚ የሆኑ የትምህርት መሣሪያዎች ማሟላት ይገባል።

1.3.1. የክፍል መጠን አደረጃጀት

አንድ ት/ቤት ለመጀመሪያ ደረጃ ለመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ቢያንስ <u>አራት</u> የመማሪያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል። እንዲሁም ለሁለቱም ሣይክሎች /1-8/ ቢያንስ <u>ስምንት</u> የመማሪያ ክፍሎች ሊኖሩት ይገባል።

1.3.2. የምድረግቢ ሥፋት

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ መማሪያ ክፍሎች ብዛት ከ15,000 እስከ 25,000 ካሬ ሜትር የሚሆን የቦታ ስፋት ይኖረዋል።
- ነገር ግን ይህ ቦታ መጠን በከተማና በገጠር እንደ ሁኔታው ሊለያይ ይችላል በትልልቅ ከተሞች ከሚታየው የቦታ ጥበት የተነሣ የት/ቤቶች ሕንፃዎች በፎቅ ደረጃ ሊሠሩ ይችላሉ። እንዲሁም የእስፖርት መሥሪያ ቦታዎች ከአንድ ዓይነት አገልግሎት /ከአንድ የእስፖርት ዓይነት/ በላይ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገው ይዘጋጃሉ።
- በገጠር ት/ቤቶች ግን ት/ቤቶች ሰፊ ቦታ እንዲኖራቸው ማድረጉ የት/ቤቶች የውስጥ ገቢ ምንጭ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል ከላይ የተጠቀሰው የቦታ መጠን እንዳለ ሥራ ላይ ይውላል።
- ለትምህርቱ ጥራት መጠበቅ ሲባል አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ከ2000 ተማሪዎች በላይ ማስተናገድ የለበትም።
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የመማሪያ ክፍል ስፋት ከ<u>50</u> እስከ <u>56</u> ካሬ

ሜትር ይሆናል።

ይህም ለት/ቤት ህንፃ፣ የስፖርት ሜዳዎች፣ የጓሮ አትክልት ቦታና ለተማሪዎች የእረፍት ሰዓት መዝናኛና መጫወቻ እንደዚሁም ቀደም ሲል በተገለፀው የክፍል መጠን አደረጃጀት መሠረት ት/ቤቱን ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች እንዲኖሩት ያስችላል።

1.3.3. የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች መጠን

1.3.3.1. የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/ ላላቸው ት/ቤቶች

ተራ ቁ.	ክፍሎች	ብዛት	የያንዳንዱ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር	ምርመራ
1	የመማሪያ ክፍል	4	8x7 = 56	ለአንድ ተማሪ 1.12
2	የርዕሰ መምህር ቢሮ	1	4x4 = 16	
3	የመምህራን ክፍል	1	4x4 = 16	
4	የዕቃ ግምጃ ቤት	1	3x3 = 9	
5	የመፀዳጃ ቤት	6	1.50x80 = 1.2	2 የመምህራንና ሠራተኞች 4 የተማሪዎች (የሴትና የወንድ ተማሪዎች) በተለያየ ሕንፃ የተሠራ
6	የትምህርት ማበልፀጊያ ክፍል	1	7x15 = 105	
7	የንባብ ቤት	1	7x8 = 56	
8	ሁለገብ የሣይንስ ክፍል	1	7x15 = 105	
9	የዘበኛ ቤት	1	2.45x2.45 = 6.8	
10	ለልዩ ትምህርት የመማሪያ ክፍሎች የመማሪያ ክፍል		4x7 = 28	
11	የንግግር ወጌሻ መስጫ ክፍል		4x3.5 = 14	
12	የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍል	1	4.05x7.26 = 19.6	
13	የፅዳት ሠራተኛ ክፍል	1	1.21x2.7 = 3.27	

1.3.3.2. ሁለቱም ሳይክል ለያዙ /1-8/ ት/ቤቶች

ተራ ቁ.	ክፍሎች	ብዛት	የያንዳንዱ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር	ምርመራ
1	የመማሪያ ክፍል /1ኛ-4ኛ/	4	7x8 = 56	1-4 ክፍል 50 ተማሪዎች በክፍል
2	የመማሪያ ክፍል /5ኛ-8ኛ/	4	6.2x7.26 = 50.24	5ኛ-8ኛ 40 ተማሪዎች በክፍል
3	የርዕሰ መምህር ቢሮ	1	4.8x4.5 = 19.6	
4	የፀሐፊ ቢሮ	1	2.7x4.84 = 13.67	
5	የመምህራን ክፍል /ስታፍሩም/	1	4.05x7= 17.67	/ከ5ኛ-8ኛ ክፍል
6	የመምህራን ክፍል	1	2.4x7.26=17.42	ከ1ኛ-4ኛ ክፍል/
7	የመጀመሪያ እርዳታ መስጫ ክፍል	1	4.05x1.84 = 19.60	
8	ዕቃ ግምጃ ቤት /ስቶር/	1	6.72x6.05 = 40.84	
9	የጽዳት ሠራተኛ ክፍል	1	1.21x2.7 = 3.27	
10	መጸዳጃ ቤት ለመምህራንና ሠራተኞች ▪ የወንዶች ▪ የሴቶች	 1 1	 3.63x4.05 = 14.7 2.7x3.63 = 9.8	
11	የንባብ ክፍል	1	12.1x6.92 = 83.73	

ተራ ቁ.	ክፍሎች	ብዛት	የያንዳንዱ ክፍል መጠን በካሬ ሜትር	ምርመራ
12	የመጻሕፍት ማስቀመጫ /ስቶር/	1	2.42x6.77 = 16.38	
13	ሁለገብ የሣይንስ ክፍል	1	7x15 =105/-/	ከ1ኛ - 4ኛ
14	ሁለገብ የሣይንስ ክፍል		8x15=/ = 120	ከ5ኛ - 8ኛ
15	የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል	1	7x15 =105	የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች
16	የትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል	1	8x10 = 80	ማዘጋጃ፣ ሰርቶ ማሳያና ማዋሻ ክፍል
17	መፀዳጃ ቤት /ለተማሪ/	8	90x1.20 = 1.08	የብሎኩ መጠን 5.30
18	የዘበኛ ቤት	1	2.45x2.45 = 6.8	4.20 = 22.26 የሴትና የወንድ ተማሪዎች በተለያየ ሕንፃ የተሠራ
19	የልዩ ትምህርት መማሪያ ክፍሎች የመማሪያ ክፍል ስፋት	2	4x7 = 28	
20	የንግግር ወጌሻ መስጫ ክፍል	1	4x3.5 = 14	

1.4 አስፈላጊ የትምህርት ቁሳቁሶች

1.4.1. አንድ መማሪያ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ ቁሳቁሶችና መጠናቸው

ተራ ቁ.		መጠኑ በሴንቲ ሜትር				ምርመራ
		ከፍታ	ወርድ	ቁመት	ብዛት	
1	ዴስክ /የመቀመጫው/	45	10	74	25	በ1 ዴስክ 2 ተማሪዎች ይቀመጣሉ
2	ጠረጴዛ	80	74	100	1	ለመምህሩ
3	ወንበር	40	56	78	1	ለመምህሩ
4	ጥቁር ሰሌዳ	=	500	120	1	
5	ማስታወቂያ ሰሌዳ	=	50	100	1	

1.4.2 ከ1ኛ-8ኛ ክፍል ለቤተመጽሐፍት የሚያሰፈልጉ ማቴሪያሎችና መጠናቸው

ተራ ቁ.	ዓይነት	ከፍታ	ወርድ	ቁመት/ ርዝመት	ብዛት	ምርመራ
1	ወንበር	40	56	74	40-80	
2	ጠረጴዛ	80	100	74	7-14	
3	መጽሐፍ መደርደሪያ	200	40	150	5-8	
4	የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት				1	መካከለኛ

1.4.3 ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለርዕሰ መምህራን፣ ለቢሮና ለመምህራን ማረፊያ ክፍል የሚያስፈልጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት፣

ተራ ቁ.	የዕቃው ዓይነት	ከፍታ	ወርድ	ርዝመት	ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል		ከ1ኛ - 8ኛ		ምርመራ
					ለር/መምህር ቢሮ የሚያስፈል ገው ብዛት	ለመምህራን ማረፊያ የሚያ ስፈልግ ክፍል ብዛት	ለር/መምህር ቢሮ የሚያስፈ ልግ ቢሮ ብዛት	ለመምህራን ማረፊያ የሚያ ስፈልግ ክፍል ብዛት	
1	ባለኪስ ጠረጴዛ	80	150	74	1	-	1	-	
2	ጠረጴዛ	80	100	74	1	1	1	3	
3	ወንበር	40	56	78	5	6	7	18	
4	የፋይል ማስቀ መጫ ቁም ሳጥን	200	60	100	1	-	1	-	
5	መጽሐፍ መደርደሪያ	200	40	100	1	-	-	-	
6	ቁልፍ ያለው ቁም ሣጥን	200	40	120	1	-	1	4	
7	የማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ	40	50	100	1	1	1	1	
9	የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት	-	-	-	1	1	1	1	

<u>ማሳሰቢያ</u>

በየሣይክሉ የመማሪያ ክፍል ቁጥር በጨመረ ልክ የዕቃዎቹ ብዛት በዛው ልክ ሊጨምር ይችላል።

1.4.4 ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ለዕቃ ግምጃ ቤት የሚያስፈልጉ ዕቃዎች መጠንና ብዛት፣

ተራ ቁ.	የዕቃው ዓይነት	ከፍታ	ወርድ	ርዝመት	ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ብዛት	ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላለው ት/ቤት ብዛት
1	ጠረጴዛ ባለኪስ	80	150	74	1	1
2	ወንበር	40	56	78	2	2
3	መጽሐፍ መደርደሪያ	200	40	100	4	16
5	ቁምሳጥን	200	40	150	1	4
6	የቆሻሻ ማጠራቀሚያ	-	-	-	1	1

1.4.5. በአንደኛ ደረጃ ሁለገብ የሳይንስ ክፍል ሊኖሩት የሚገቡ የዕቃዎች አይነትና ብዛታቸው፣

<u>ተራ ቁ.</u>	<u>የዕቃው ዓይነት</u>	<u>ብዛት</u>
1.	የመምህሩ /ዲሞንስትሬሽን/ ጠረጴዛ	1
2.	በቀላሉ የሚንቀሳቀሱ የተማሪ ጠረጴዛዎች	10
3.	ኩርሲዎች ወይም ወንበሮች	50
4.	ጥቁር ሰሌዳ	1

5.	ማስታወቂያ ሰሌዳ	2
6.	/ሰፋፊ/ መደርደሪያዎች/ ለሥራዎች ማስቀመጫ	4
7.	ቁምሳጥን	1
8.	የንብረት ማስቀመጫ /ትንሽ ክፍል	1
9.	የሳይንስ ኪቶች	2
10.	የውሃ መያዣ ጀሪካን	1

1.4.6. ለትምህርት ማበልፀጊያ ማዕከል የሚያሰፈልጉ መሣሪያዎች

ተራ ቁ.	ዓይነት	ሳይዝ በሴንቲ ሜትር				ምርመራ
		ከፍታ	ወርድ	ቁመት/ ርዝመት	ብዛት	
1	ወንበር	40	56	78	3	
2	ጠረጴዛ	80	74	100	3	
3	መደርደሪያ	150	40	150	1	
4	የመሥሪያ ቤንች 2 የእንጨት ሥራ መሥሪያ	6	70	100	3	ከሞርስ ጋር
5	ጥቁር ሰሌዳ	=	500	150	1	
6	ማስታወቂያ መለጠፊያ ሰሌዳ	=	100	200	1	
7	የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት	=	=	=	1	መካከለኛ

1.5 የሰው ኃይል ምደባ

1.5.1. በየሳይክሉ ሊኖሩ የሚገቡ የተማሪዎች ብዛት

- ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ባለው ደረጃ በክፍል እስከ 50 ተማሪዎች ይመደባሉ።
- ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ባለው ደረጃ በክፍል እስከ 40 ተማሪዎች ይመደባሉ።
- የልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ህፃናትና ወጣቶች ከሌሎች ጋር ተቀላቅለው የሚማሩ ከሆነ በክፍል ከ5 መብለጥ የለባቸውም።
- በመደበኛ ት/ቤት በሚከፈት ልዩ ክፍል ውስጥ አንድ መምህር ከ10-20 የሚደርሱ ልዩ ትምህርት የሚያስፈልጋቸውን ህፃናት ያስተምራል።
- አሁን ባለንበት የእድገት ደረጃ የተማሪዎች ቁጥር በዚህ መጠን መወሰን አስፈላጊ የሆነው በትምህርት አሰጣጥና አቀባበል ክትትልና ድጋፍ ከማድረግ አኳያ የተሻለ ውጤት ለማምጣትና የትምህርት ፋሲሊቲዎችን በአግባቡ ለመጠቀም ሰለሚያስችል ነው።
- በአንድ ት/ቤት ከሚገኙት ከመደበኛ ተማሪዎች ውስጥ ልዩ ፍላጐት ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ህፃናት ብዛት በአማካኝ ከ5%-10% ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

1.5.2. የተማሪ መጻሕፍት ጥምርታ

- ተማሪዎች በየእለቱ በሚቀስሙት ትምህርት ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት አስፈላጊ የትምህርት ግብአቶች ተሟልተው ሲቀርቡላቸው ነው። ከግብአቶቹ መካከል የማስተማሪያ መጻሕፍት በዋናነት የሚጠቀሱ ሲሆን እያንዳንዱ ተማሪ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚሰጠው ሥራ በአግባቡ ሊወጣ የሚችለው የተማሪ መጻሕፍት ጥመርታ 1፡1 መሆን ሲችል ነው። ስለሆነም እያንዳንዱ ተማሪ <u>ከየትምህርት ዓይነቱ አንዳንድ መጽሐፍ</u> ሊኖሩት ይገባል።

1.5.3. የመምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች የትምህርት ደረጃ

1.5.3.1. የመጀመሪያ ሳይክል /1-4/

ተራ ቁ.	የሠራተኛው ዓይነት	ብዛት	የትምህርት ደረጃ
1	ርዕሰ መምህር	1	- በዲኘሎማ የተመረቀ/ች ሆኖ የርዕሰ መምህርነት ኮርስ የወሰደ/የወሰደች
2	ዩኒት መሪ	1	- በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
3	መምህራን	-	- በዲፕሎማ የተመረቁ ሆነው ለደረጃው የሚሰጠውን የመምህርነት ሥልጠና የወሰዱ
4	ዘበኛ	2	- 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች
5	ተላላኪ	1	- 8 ክፍል ያጠናቀቀ/ች
6	የፅዳት ሠራተኛ	1	- 8ኛ ክፍል ጠናቀቀ/ች
7	ፀሐፊ	1	- በሴክሬታሪያል ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
8	የቤተ መጻሕፍት ባለሙያ	1	- በላይብራሪ ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች

1.5.3.2. የሁለተኛ ሣይክል /5-8/

ተራ ቁ.	የሠራተኛው ዓይነት	ብዛት	የትምህርት ደረጃ
1	ርዕሰ መምህር	1	- በትምህርት አመራርና እቅድ ዝግጅት በዲግሪ የተመረቀ/ች
2	ምክትል ር/መምህር	1	" " " "
3	ዩኒት መሪ	2	- በማንኛውም የትምህርት መስክ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
4	መምህራን	-	- በዲፕሎማ የተመረቁ
5	ፀሐፊ	1	- በሴክሬታሪያል ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
6	የቤተ መጻሕፍት ባለሙያ	1	- በላይብራሪ ሳይንስ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች

ተራ ቁ.	የሠራተኛው ዓይነት	ብዛት	የትምህርት ደረጃ
7	የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊ	1	- በንብረት አያያዝ ሙያ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
8	ዘበኛ	2	- 8ኛክፍል ያጠናቀቀ
9	ተላላኪ	1	- 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች
10	ፅዳት ሠራተኛ	1	- 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀች

ማሳሰቢያ

ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ላሉ ት/ቤቶች የተማሪዎች ቁጥር ከ1000 በላይ ከሆነ ምክትልር/መምህር ይመደባል

1.5.3.3. የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም መምህራንና ሠራተኞችን በተመለከተ፣

ተራ ቁ.	የሠራተኛው ዓይነት	የትምህርት ደረጃ	
		/1-4/	/5-8/
1	መምህር	በልዩ ፍላጐት ትምህርት ሙያ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች	በልዩ ፍላጐት ትምህርት ሙያ በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
2	የንግግር ወጌሻ	በቋንቋ ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች ሆኖ በልዩ ፍላጐት ትምህርት ሥልጠና የወሰደ/ች	በዲፕሎማ በቋንቋ የተመረቀ/ች የልዩ ትምህርት ፍላጐት ሥልጠና የወሰደ/ች
3	ረዳት ወይም ሞግዚት	በልዩ ፍላጐት ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች	በልዩ ፍላጐት ትምህርት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች

1.6. የትምህርት ፕሮግራም አደረጃጀት

ትምህርት ታቅዶና ታልሞ ከህፃናት እድሜ፣ የአካል ብቃት፣ የአእምሮ ብስለትና የመማር ዝግጁነት ጋር እየተገናዘበ በደረጃና በጊዜ ተመጥኖ የሚሰጥ ሲሆን ይህም የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ተቀዳሚ ተግባር ነው።

ሥርዓተ ትምህርት በአንድ አገር የትምህርት ዓላማዎች ላይ ተመሰርቶ የሚዘጋጅ ሲለበስ፣ የተማሪ መጽሐፍ፣ የመምህሩ መምሪያ፣ መርጃ መሣሪያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ ጽሁፎችና የማስተማር ዘዴዎችን ያካትታል።

በመሆኑም በአገራችን አስፈላጊውን ደረጃ የጠበቀና በየትምህርት እርከኑ ተገቢውን የባህሪ ገጽታ ሊቀርጽ የሚችል ሥርዓተ ትምህርት በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በተገለጹት አጠቃላይ የትምህርት ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ ተዘጋጅቷል።

የትምህርት ፕሮግራሙ የሚከተሉት አደረጃጀቶች ይኖሩታል።

- የትምህርት ጊዜ አደረጃጀት፣
- የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በትምህርት አይነት፣
- የትምህርት ቤት አመራር ሚና፣
- የት/ቤት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም፣
- የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም፣
- የሙሉ ቀን ትምህርት ፕሮግራም፣
- የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም፣
- የተለየ ትኩረት የሚሹ የትምህርት አይነቶች፣
- የመማር ማስተማር መመሪያዎች፣

1.6.1. የትምህርት ጊዜ አደረጃጀት

- የተለያዩ አገሮች ጥናት እንደሚያመለክቱት በአንድ የትምህርት ዘመን ውስጥ ከ150-250 የትምህርት ቀናት አሉ። በዚህ መሠረት በኛ ሀገርም በየደረጃው የሚሰጠው ትምህርት የተዘጋጀው ከ203-206 ባሉት ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ታስቦ ነው። ስለዚህ በዓመት ውስጥ ከ203-206 የትምህርት ቀናት ይኖራሉ።
- አንድ የትምህርት ዘመን በሁለት ሴሚስተር ይከፈላል።
- መደበኛ የትምህርት ቀናት ከሰኞ እስከ አርብ ሆኖ 5 ቀናት ይይዛል።
- አጋማሽ የሴሚስቴር ፈተናዎች እና ተከታታይ ግምገማዎች ቴስቶች በትምህርት ክፍለ ጊዜ ውስጥ ይሰጣሉ።
- የየሴሚስተሩ መጨረሻ ፈተናዎች በሴሚስቴሩ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ይጠናቀቃሉ።
- ከ1ኛ ሴሚስቴር ፈተና በኋላ የአንድ ሣምንት የፈተናና የማረሚያ ውጤት ማጠናቀሪያ ጊዜ ይኖራል።
- በብሔራዊ ፈተናዎችና በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች የሚባክኑ የትምህርት ቀናት ቢኖሩ መካካስ ይኖርባቸዋል።

1.6.2. ትኩረት የሚሰጣቸው የትምህርት ዓይነቶች

- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መሠረታዊ ዕውቀቶችን በማስጨበጥ ለሚቀጥሉት ተከታታይ የአጠቃላይ ትምህርትና ሥልጠና እርከኖች ብቁ የሚያደርግና መሠረት የሚጣልበት በመሆኑ፣ ለቋንቋዎች፣ ለሂሣብና ለተፈጥሮ ሣይንስ ትምህርቶች ትኩረት እንዲሰጥ ይደረጋል።
- ለነዚህ የትምህርት ዓይነቶች ትኩረት ይሰጣል ሲባል ከሥርዓተ ትምህርት ከመማሪያ

መጻሕፍት፣ የመምህሩ መመሪያ፣ ከትምህርት መሣሪያዎች አቅርቦትና በክፍል ውስጥ ለተማሪው የሚደረገውን ጨምሮ የተሟላ የትምህርት አቀራረብ ድረስ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል።

- መምህሩ ትምህርቱን በዓመት፣ በሴሚስተር፣ በሣምንት/ በቀንና በክፍለ ጊዜያት ከፋፍሎ፣ የሚጠቀምበትን ተስማሚ የአቀራረብ ዘዴ፣ ትክክለኛ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን፣ ተማሪዎች የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች (Activities) በመምረጥና በማዘጋጀት ከቀረበ በኋላ ትምህርቱ ተፈላጊውን የባህሪ ለውጥ በተማሪው ዘንድ ማምጣቱን የመገምገሙ ሥራ በብቃትና በጥንቃቄ ያካሂዳል።

ከ1ኛ-4ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠናን አስመልክቶ

ለአንደኛ ደረጃ ለመጀመሪያ ሳይክል መምህርነት የሚሰለጥኑ መምህራን አሀዳዊ የክፍል አያያዝና አመራር ዘዴን የሚጠቀሙ ሲሆን አሰለጣጠናቸው የክላስተር ሞዳሊቲ መሠረት ያደረገ ሆኖ ቋንቋን፣ የህብረተሰብ ሣይንስን፣ ሂሣብንና የተፈጥሮ ሣይንስን እንዲሁም ኤስቴቲክስ በአማራጭነት በመያዝ ይሰለጥናሉ።

ከ5ኛ- 8ኛ ክፍል ለሚያስተምሩ መምህራን ሥልጠናን አስመልክቶ

ተራ ቁ.	በትኩረት መስክ የሚሰጡ ትምህርቶች	መግለጫ
1	ቋንቋ ▪ አማርኛ ▪ እንግሊዝኛ ▪ ብሔር/ብሔረሰብ ቋንቋ	ሶስቱንም የተምህርት ዓይነቶች ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ፣
2	ተፈጥሮ ሣይንስ ▪ ባዮሎጂ ▪ ኬሚስትሪ ▪ ፊዚክስ	ሶስቱንም የትምህርት ዓይነቶች በተናጠልና በማቀናጀት በአጠቃላይ ሣይንስ ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ።
3	የህ/ሰብ ትምህርት ▪ ጂኦግራፊ ▪ ታሪክ ▪ ሲቪክስ	ሶስቱንም የትምህርት ዓይነቶች በተናጠልና በማቀናጀት /ኅብረተሰብ ትምህርት/ ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ።
4	ሂሣብ	ከሂሣብ ትምህርት ጋር ቅርበት ያላቸውን ትምህርቶች ለምሳሌ ፊዚክስና ኬሚስትሪ በተጨማሪ ማስተማር እንዲችሉ ሆነው ይሰለጥናሉ።
5	የጤናና የሰውነት ማጐልመሻ	የጤናና የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት እንዲያስተምሩና በተጨማሪም ሌሎች አግባብ ያላቸው ትምህርቶችንም ይወስዳሉ።
6	ሙዚቃና ሥነ ሥዕል	ሁለቱንም የትምህርት ዓይነቶች እንዲያስተምሩ ሆነው ይሠለጥናሉ።

ከላይ የተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች በትኩረት መስክ ይሰጡ እንጂ የሥልጣኞችን አጠቃላይ ዕውቀት ለማሳደግ ያህል በተጨማሪ በጋራ (common) የሚወስዱቸው

የትምህርት ዓይነቶች ይኖራሉ። <u>ለምሳሌ</u>፡- ፔዳጐጂክስ፣ ሣይኮሎጂ፣ እንግሊዝኛ፣ ብሔር /ብሔረሰብ ቋንቋ፣ ሂሣብ፣ የአካባቢ ሳይንስ፣ የጤናና ሰውነት ማጐልመሻ፣ ሲቪክስ ወዘተ...

1.6.2.1. ቋንቋዎች

ቋንቋ ለግንኙነትና ለትምህርት መስጫ ያገለግላል።

- በት/ቤት ተማሪዎች ሊማሩዋቸው የሚገቡ ቋንቋዎች

ሀ/ <u>የአፍ መፍቻ ቋንቋ</u>

- በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ ይሰጣል።
- በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት /1-8/ በማስተማሪያነት ያገለግላል።

ለ/ <u>አገር አቀፍ ቋንቋ</u>

- አገር አቀፍ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን በአገር ውስጥ ሁሉንም ብሔረሰብ የሚያገናኝ ነው።
- አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ለሆኑ፣ አማርኛ 1ኛ - 8ኛ ክፍል የትምህርት መስጫ ቋንቋ ሆኖ ያገለግላል።
- አማርኛ የአፍ ቋንቋ መፍቻቸው ላልሆኑ ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ 8ኛ ክፍል እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ ይሰጣል።

ሐ/ <u>ዓለም አቀፍ ቋንቋ፣</u>

ከዓለም ጋር ለመግባቢያ የሚያገለግል ቋንቋ እንግሊዝኛ ሲሆን፣

- በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ሆኖ ይሰጣል።

1.6.2.2. የሂሣብ ትምህርትና የተቀናጀ ሣይንስ ትምህርት

- ከ1-8 ላሉ ክፍሎች ለተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ከሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ ከፍተኛ ክ/ጊዜያት ተመድቦላቸዋል። በአጠቃላይ ከ1ኛ-8ኛ ክፍሎች ከላይ በ1.6.2.1 እና በ1.6.2.2 ተ.ቁ. በተጠቀሱት የትምህርት ዓይነቶች ከሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች ይልቅ ከፍተኛ ክፍለ ጊዜ መመደቡ ትኩረትን የሚያመለክት ሲሆን በተጨማሪ መምህራን፡-
  - በዕቅድ ላይ ተመስርተው በየጊዜው የተማሪዎችን ሥራ የመገመገም፣
  - ከግምገማው ውጤት በመነሳት የመማር ማስተማሩን ሂደት የማሻሻል፣
  - ደከም ያሉትን እና ልዩ ተሰጥዎ ያላቸውን ተማሪዎች በመለየት አስፈላጊውን

ተጨማሪ ድጋፍ የመስጠት፣

- የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም የማጠናከር ተግባራትን ያከናውናሉ።

1.6.3. የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በትምህርት ዓይነት

- በፈረቃ ለሚያስተምሩ ት/ቤቶች
  - ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል በቀን 6 ክፍለ ጊዜ ይኖሩታል።
  - የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 40 ደቂቃ ሆኖ በሳምንት 30 ክፍለ ጊዜያት ይኖሩታል።
- ሙሉ ቀን ለሚያስተምሩ ት/ቤቶች
  - ከ1ኛ -2ኛ ክፍል በቀን 6 ክፍለ ጊዜት ይኖራሉ።
  - ከ3ኛ ክፍልና ከዚያ በላይ 7 ክፍለ ጊዜያት ይኖራሉ።
  - የአንድ ክፍለ ጊዜ ርዝማኔ 45 ደቂቃ ሆኖ በሳምንት 35 ክፍለ ጊዜያት ይኖሩታል።

<u>የመጀመሪያ ሳይክል በትምህርት አይነትና በክፍል ደረጃ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት</u>፣

ተራ ቁ.	የትምህርት ዓይነት	የሳምንቱ ክፍለ ጊዜ ሥርጭት በክፍል ደረጃ			
		1ኛ	2ኛ	3ኛ	4ኛ
1	አማርኛ	-	-	3	3
2	የሥነ ውበትና የሰውነት ማጐልመሻ	6	6	4	4
3	እንግሊዝኛ	6	6	5	5
4	የአካባቢ ሳይንስ	7	7	7	7
5	ሒሳብ	6	6	6	6
6	የአፍ መፍቻ ቋንቋ	5	5	5	5
ድ ም ር		30	30	30	30

<u>የሁለተኛ ሳይክል /5-8/ በትምህርት አይነትና በክፍል ደረጃ የክፍለ ጊዜ ሥርጭት</u>፣

ተራ ቁ.	የትምህርት ዓይነት	የሳምንቱ ክፍለ ጊዜ ሥርጭት በክፍል ደረጃ			
		5ኛ	6ኛ	7ኛ	8ኛ
1	አማርኛ	3	3	2	2
2	ባዮሎጂ	-	-	2	2
3	ኬሚስትሪ	-	-	2	2
4	የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር	3	3	3	3
5	እንግሊዝኛ	5	5	5	5
6	የተቀናጀ ሳይንስ	4	4	-	-
7	ሂሣብ	5	5	5	5
8	የአፍ መፍቻ ቋንቋ	3	3	3	3
9	ስዕልና ሙዚቃ	2	2	1	1
10	የጤናና የሰውነት ማጐልመሻ	2	2	2	2
11	ፊዚክስ	-	-	3	3

12	የህብረተሰብ ሳይንስ	3	3	3	3
	ድ ም ር	30	30	30	30

ማሳሰቢያ፡-
ከላይ በሰንጠረዡ የተጠቀሰው የክፍለ ጊዜ ሥርጭት በቀጣይ ከ30 ክ/ጊዜ ወደ 35 ከፍ ሊል ይችላል። ይሽውም 5ቱ ክፍለ ጊዜያትና ለ5ኛ እና 6ኛ ክፍል በአማርኛ፣ በእንግሊዝኛ፣ በሒሳብና በጤናና የሰውነት ማጐልመሻና በተቀናጀ ሳይንስ ላይ አንዳንድ ክፍለ ጊዜ ይጨምራል። ለ7ኛና 8ኛ ክፍሎች ለአማርኛ 1 ክ/ጊዜ፣ ለሦስቱ የሣይንስ ትምህርቶች 3 ክ/ጊዜ፣ ለጤናና የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት 1 ክፍለ ጊዜ ይጨምራል።

1.6.4. የትምህርት ቤት አመራር አካላትና ሚናቸው (School management role)

በት/ቤቶች ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል ሚና ከሚጫወቱ አካላት መካከል ተገቢውን የማስተባበር እና የመምራትን ሥራ የሚያከናውን የትምህርት አመራር በዋነኛነት የሚጠቀስ ነው።

የት/ቤት አመራር አካላት ሲባል ር/መምህራን፣ መምህራንና የአካባቢውን ህብረተሰብና ወላጆች እንዲሁም በየደረጃው ያሉ የትምህርት ባለሙያዎችና ኃላፊዎችን ያጠቃልላል።
የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች በትምህርትና ሥልጠና እና አመራር ቦርድ ይመራሉ። ቦርዱ ከህ/ሰቡ፣ ከት/ቤቱ ማኅበረሰብና ከቀበሌ መስተዳድር የተውጣጡ አባላት ሲኖሩት አባላቱ በመልካም ስነ ምግባራቸው የተመሠከረላቸው እና በአመራር ችሎታቸው የተመሰገኑ ሆነው የቦርዱ ሰብሳቢ ከቀበሌ መስተዳድር የሚወከል ሲሆን የት/ቤቱ ር/መምህር የቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል።

እነዚህ አካላት በትምህርት ሥራ ላይ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ በመሆናቸው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

- **ት/ቤቶች ህብረተሰቡን በማስተባበር በመማር ማስተማር ሥራ ላይ በባለቤትነት የሚሳተፉበትን ዕቅድ በማቀድና ለተግባራዊነቱም ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ ተጨባጭ ውጤት ማምጣት፣**
- **የት/ቤቱን ማህበረሰብና የአካባቢው ህብረተሰብ በአጠቃላይ በውሣኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ በማሳተፍ በተማሪዎች ውጤት ላይ ጉልህ የሆነ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ፣**
- **መምህራን በአመራር ሥራዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ንቁ ተሳትፎ**

እንዲያደርጉ ቁልፍ በሆነ የውሣኔ አሰጣጥ ላይ ኃላፊነትን በማካፈል የባለቤትነት ስሜት ኖሮአቸው ሥራቸውን ብቃት እንዲወጡ ማስቻል፣

- መምህራን፣ የወላጅ ኮሚቴዎችና የትምህርት ባለሙያዎች በት/ቤት እቅድ ዝግጅትና አተገባበር ግምገማ ሂደቶች ላይ እንዲሣተፉ በማድረግ የት/ቤቱን ዕቀድ ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣
- መምህራን በሥራቸው የበለጠ እንዲተጉ /እንዲበረቱ/ ባሳዩት ውጤት አርአያ የሆኑትን ለብቻ ስማቸውን በማስታወቂያ ሰሌዳ በይፋ በመለጠፍ እንዲታወቁና የማበረታቻ ሽልማት እንዲያገኙ በማድረግ፣
- ት/ቤቱ የተማሪዎችን ወላጆች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ በመጥራት በልዩ ልዩ የትምህርት ጉዳዮች ላይ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት በት/ቤቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራዋቸው ማድረግ፣
- በት/ቤቱ ያጋጠሙ ችግሮችን በየጊዜው ለይቶ በማውጣት ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አስፈላጊ የመፍትሔ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ ችግሮቹን ማስወገድ፣
- ት/ቤትን ማዕከል ያደረገ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ መምህራን የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት በትምህርቱ ዙርያ የሚታዩትን ችግሮች እንዲቀረፉና መምህራን ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያመጡ፣ በተጓዳኝ ትምህርት ጥሩ ተሳትፎ ያላቸው እና በጥሩ ሥነ-ምግባር ለሌሎች አርአያ የሆኑትን ተማሪዎች በማስታወቂያ ሰሌዳ ስም ዝርዝራቸውን በመለጠፍ እና ሽልማት በመስጠት በት/ቤቱ ማህበረሰብ ዘንድ እንዲታወቁ በማድረግ እና በሌሎች ተማሪዎች ዘንድም የተወዳዳሪነትን መንፈስ በማሳደግ ለበለጠ ውጤት እንዲነሳሱ ማስቻል፣
- በት/ቤት ውስጥ ካሉት ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች መካከል በሥራቸው የላቀ ውጤት ያመጡትን የማበረታቻ ሽልማት በመስጠት ለተሻለ ውጤት እንዲበቁ ማድረግ፣
- ከመምህራንና ተማሪዎች ጋር ሥራንና የትምህርት ውጤትን በማሻሻል ዙሪያ በየጊዜው ግልፅ ውይይት በማካሄድ የተሻለ የሥራ አፈጻጸም እንዲኖርና የተማሪዎች የትምህርት ውጤት እንዲሻሻል ማስቻል፣
- የአጠቃላይ ትምህርት የጥራት ማረጋገጫ ፖኬጅ መርሀ ግብሮችን ጠንቅቆ በማወቅና ሌሎች ባለድርሻ አካላትም እንዲገነዘቡት በማድረግ የትምህርቱ ጥራት እንዲረጋገጥ ማስቻል፣
- የት/ቤቱን የውስጥ ለውስጥና ከሌሎች አቻ ት/ቤቶች ጋር የልምድ ልውውጥ

በማካሄድ የተሻለ አሠራርና ውጤት ማስመዝገብ፣

- የት/ቤቱን መምህራንና ሠራተኞች የሥልጠና ፍላጐት በመለየት ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ ማስቻል፣
- የት/ቤቱን የውስጥ ሱፐርቪዥን በማካሄድና በተገኘው ውጤት መሠረት መምህራን እርስ በእርስ እንዲማማሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተሻለ የሥራ አፈፃፀም እንዲኖር ማድረግ፣

1.6.5. የት/ቤት የሥራ ሰዓት አጠቃቀም

- ትምህርት በሙሉ ቀን ይሰጣል።
- በአሃዳዊ ክፍል /1-4/ በቀን 6 ክ/ጊዜ በሣምንት 30 ጊዜ ይሰጣል።
- በመጀመሪያው ሳይክል /1-4/ ለ4 መማሪያ ክፍሎች አንድ ረዳት መምህር ይመደባል።
- ረዳት መምህሩ በመደበኛነት የተመደቡ መምህራን በልዩ ልዩ ምክንያት ከሥራ ገበታቸው ሲቀሩ እነሱን በመተካት ማስተማርና በሌላም ጊዜ የቤት ሥራ በማረም የትም/ መርጃ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ተማሪዎች ድጋፍ በመሰጠትና በተጓዳኝ ትምህርት በመሣተፍ ተመድቦ ይሰራል።
- አሃዳዊ ትምህርት የሚሰጠው ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ሲሆን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።
    - አንድን ትምህርት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማዛመድ ለማስተማር ይረዳል።
    - የተማሪውን ደካማና ጠንካራ ጐኖችን በመለየት እርዳታ ለመስጠት ያስችላል።
    - የትምህርቱን አሰጣጥ እንደ ተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ለይቶ ለማቅረብ ይረዳል።
    - መምህራን ለተማሪዎች የቅርብ ክትትልና ድጋፍ ለመስጠት ያስችላል።
    - በሣምንቱ ውስጥ ሊሰጥ የሚገባው ክ/ጊዜ ሳይጓደል ፕሮግራሙን እንደአመቺነቱ ተለዋዋጭ ለማድረግ ያስችላል።
- ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች በቀን 6 ክፍለ ጊዜ በሳምንት 30 ክፍለ ጊዜ ይሰጣል።
- ከ5ኛ - 8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን ከክፍል ወደ ክፍል በመዘዋወር

ትምህርቱን ይሰጣሉ። መምህራኑ በሰለጠኑባቸው የትምህርት ዓይነቶች ይመደባሉ።

1.6.5.1. የመምህራን የሥራ ሰዓት አጠቃቀም

የአንድ መምህር የሳምንት መደበኛ የሥራ ሰዓት 40 ሰዓት ሆኖ ይህም ለትምህርት ዝግጅት፣ ክፍል ውስጥ ገብቶ ለማስተማር፣ የተማሪዎችን ሥራ ለማረምና ለመከታተል ይጠቀምበታል።

- ክፍል ውስጥ ገብቶ ለማስተማር 22፡30 ሰዓት
- ለትምህርት ዝግጅትና የተማሪዎች ሥራ ለማረምና ለመከታተል 11፡30 ሰዓት
- ለተጓዳኝ ትምህርት 3 ሰዓት
- ለልዩ ልዩ ሥራዎች እስከ 3 ሰዓት ይሆናል።

- የተጠቀሰው የሥራ ሰዓት እንደወቅቱ የሥራ ሁኔታ አመቺነት ተከፋፍሎ ሊሰጥ ይችላል።
- የአንድ መምህር የክፍለ ጊዜ ብዛት ከሚፈለገው በታች ከሆነ አንደአስፈላጊነቱ በተመሣሣይ የትምህርት ዓይነትም ሆነ በሌላ ሥራ ላይ ተመድቦ/ተመድባ ይሰራል/ትሰራለች።
- ከ1ኛ - 4ኛ ክፍል ባለው ደረጃ የሚየስተምሩ መምህራን በክላስተር ሞዳሊቲ የሰለጠኑ ሆነው በሰለጠኑባቸው የትምህርት ዓይነቶች ያስተምራሉ።
- ከ5ኛ - 8ኛ ባሉ ክፍሎች አንድ መምህር ብዙ ሴክሽኖች ባሉበት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይንም በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ተመድቦ/ተመድባ ያስተምራል/ ታስተምራለች።

1.6.5.2. ከመምህራን የሚጠበቅ ባህሪ

መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ቀዳሚ ሥፍራ ስላላቸው ያለእነሱ ብርቱ ጥረት ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት አይታሰብም።

መምህራን በማስተማር ችሎታቸው የሚተማመኑ ለተማሪዎችና ለሥራቸው ጥንቃቄ የሚያደርጉና እርስ በርሳቸው የሚረዳዱ ሊሆኑ ይገባል። መምህራን በማስተማሩ ረገድ ተጨባጭ እቅድ በማዘጋጀት ከሁሉም አስቀድመው ሙያዊ ግዴታቸውን ለመወጣት እንዲችሉ የሚከተሉት ቁልፍ ሚናዎች ይኖራቸዋል።

- መምህሩ በክፍል ውስጥ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አዋኪ-የሆኑት /ሲጋራ

ማጨስ፣ሞባይል መጠቀም፣ወ.ዘ.ተ ከማድረግ መቆጠብ፣

- የሚያስተምሩትን የትምህርት ይዘትና አቀራረብን ጠንቅቆ በማወቅ፣ተማሪዎች ከነበሩበት ደረጃ ወደ ተሻለ ውጤት ማብቃት፣
- ግልጽ የሆነ ግብ በመንደፍ ለተግባራዊነቱ ያላሰለሰ ጥረት በማካሄድ፣ተጨባጭ ለውጥ ማስመዝገብ፣
- የሚያስተምሩትን ትምህርት ለተማሪው በሚያመች ግልጽ፣ ሳቢ፣ ማራኪ እና አሳታፊ የትምህርት አቀራረብ (Active Learning) በመጠቀም ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ፣
- ለት/ቤቱ ንብረቶች ከፍተኛ እንክብካቤ በማድረግ ተገቢ ግልጋሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣
- ውጤታማ የሆነ የክፍል አያያዝ ሥርዓትን ተግባራዊ በማድረግ፣
- ለተማሪዎች ውጤትና ሥነ-ምግባር መሻሻል በማቀድና በመተግበር ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት /መኮራረጅ፣ መደባደብ፣ የት/ቤት ንብረት ማውደም ወ.ዘ.ተ/
- ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በሚገባ ለመረዳታቸው በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ እንደተማሪው የትምህርት አቀባበል የባህሪ ለውጥ ማምጣት፣
- ተከታታይ ግምገማና ምዘና በማካሄድ በተገኘው ውጤት መሠረት የማስተማር ዘዴዎችን ከተማሪዎች የትምህርት አቀባበል አኳያ በመጠቀም ተማሪዎችን ለጥሩ ውጤት ማብቃት ፣
- በት/ቤቱ ማህበረሰብም ሆነ በሌላ የመልካም ሥነ ምግባር አርአያ ሆኖ መገኘት፣
- በተማሪዎች መካከል የዕድ እኩልነትና የችሎታ ልዩነት መኖሩን በመረዳት እና ተገቢ ድጋፍ በመስጠት ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት፣
- ሙያቸውን ለማሻሻል እርስ በርሳቸው የሚማማሩባቸውና ሙያዊ ድጋፍ የሚሰጣጡባቸውን መድረኮችን በመፍጠር አቅምን - ማዳበር፣
- በት/ቤቱ የሥራ ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ በመሣተፍና ከወላጆችና ከተማሪዎች ጋር በመወያየት በመማር ማስተማር ሥራ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ፣
- የት/ቤቱን የደምብ ልብስ /ጋዋን/ መልበስና ማንነታቸውን የሚገልፅ ባጅ ማድረግ።

1.6.6. የልዩ ፍላጐት ትምህርት ፕሮግራም

- አብዛኛዎቹ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ይዘቶች ከመደበኛ ትምህርት ይዘቶች ጋር ተቀናጅተውና ተዋህደው ስለሚሰጡ የተለየ የክ/ጊዜ ስርጭት አያስፈልጋቸውም።

- የተለየ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መምህሩ አመቺ የሆነ ክፍለ ጊዜ በመስጠት ለእያንዳንዱ ተማሪ ልዩ ድጋፍ ይሰጣል።
- አንድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህር የሥራ ሰዓት ከመደበኛው ት/ቤት መምህር እኩል ነው።

1.6.6.1. የአእምሮ ውስንነት ላላቸው /1-4/

- ለመደበኛው የትምህርት ፕሮግራምና ለእድገት ዘርፎች የሚረዱ ስልጠናዎች ማለትም በቋንቋ፣ በንባብና ቅድመ ንባብ፣ በቁጥር፣ በማህበራዊ እድገት፣ በሥነ ስዕል፣ በእጅሥራና በድራማ ትምህርቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

1.6.6.2. ማየት ለተሳናቸው /1-4/

- የስሜት ህዋሳት ስልጠና፣ ነፃ እንቅስቃሴና ትውውቅ፣ የአባካስ፣ የብሬል ንባብና ጽሕፈት፣ ጽሑፍን በቴፕ አቀራረጽ፣ መተየብ፣ የእጅ ጽሕፈትና የዕለት ተዕለት ክሂል ካዳበሩ በኋላ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመቀላቀል ይማራሉ።

1.6.6.3. መስማት ለተሳናቸው /1-8/

መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች የነፍስ ወከፍና የቡድን ንግግር፣ የማዳመጥ ሥልጠናና የቋንቋ ችሎታን ማዳበር የመሣሉ ክሂሎችን ይማራሉ።

1.6.6.4. የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራንና ሠራተኞች ድልድል

የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራን ድልድል እንደ መደበኛው ት/ቤት የመምህራንና ሠራተኞች ድልድል ሆኖ፣ በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ከ10-20 ለሚሆኑት የልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ሕፃናት ልዩ ክፍልና ተጨማሪ የሰው ኃይል እንደሚከተለው ይሆናል።

- የማየት ጉድለት ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ ልዩ መምህር፣
- የመስማት ጉድለት ላለባቸው ሕፃናትና ወጣቶች አንድ መምህር፣
- የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው አንድ ልዩ መምህርና አንድ ረዳት መምህር ወይም ሞግዚት፣
- የስሜት መረበሽ ላጋጠማቸው አንድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህር፣ አንድ የሳይኮሎጂ ባለሙያ፣
- የመማር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህርና አንድ ረዳት መምህር፣
- የአንድ የልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህር የሥራ ሰዓት ከመደበኛው ትምህርት መምህር እኩል ነው።

- የመናገር ችግር ላለባቸው አንድ ልዩ መምህርና አንድ የአንደበት ወጌሻ፣
- የአካል ጉድለት ላለባቸው አንድ ረዳት መምህር ወይም ሞግዚት፣
- ተደራራቢ ችግር ላለባቸው እንደየሁኔታው ታይቶ የሰው ኃይል ይመደባል። ለምሳሌ አንድ ሕፃን የመስማትና የማየት ጭምር ችግር ካለበት የሰው ኃይል ምደባው አንድ ባለሙያ ለአንድ ወይም ለሁለት ሕፃናት ይሆናል።
- ልዩ ተሰጥኦ ላላቸው ሕፃናት የሚመደበው ባለሙያ እንደየሕፃናቱ አእምሮ ችሎታና ልዩ ተሰጥኦ ሁኔታ ይለያያል። <u>ለምሳሌ</u> አንድ ሕፃን በሂሣብ ትምህርት ወይም በሥዕል ወዘተ. ከሌሎች ሕፃናት በጣም የመጠቀ ችሎታ ካለው በዚህ ትምህርት እንዲገፋበት የሚመለከተውና ችሎታ ያለው መምህር ተመድቦለት እንዲከታተለውና እንዲያበረታታው ይደረጋል።

ልዩ ፍላጐት ትምህርት ለሚያስፈልጋቸው ሕፃናትና ወጣቶች ከሌሎች መደበኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ በሚደረግበት ጊዜ የተለየ ክህሎትና ይዘት እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲቻል ከመደበኛ ክፍሎችና የትምህርት ጊዜ ውጭ በልዩ ክፍሎች (unit) በልዩ ፍላጐት ትምህርት መምህራንና ባለሙያዎች ይስተናገዳሉ።

1.6.7. የሙሉ ቀን ትምህርት

የተማሪዎች ብዛት ከጊዜ ወደጊዜ እያደገ በመምጣቱ ት/ቤቶች እነዚህን ተማሪዎች ተቀብለው ለማስተናገድ ባለመቻላቸው ምክንያት ትምህርት በሁለት ፈረቃዎች እንዲሰጥ ሲደረግ ቆይቷል። ይህ አሠራር ለጊዜው ለችግር ማቃለያነት ተብሎ የተወሰደ ቢሆንም ተማሪው በቀን ውስጥ ማግኘት የሚገባውን ትምህርት በስፋትና በጥልቀት እንዲያገኝ ስለማያስችለው በትምህርቱ ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

በመሆኑም እስከ አሁን ድረስ በሁለት ፈረቃ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ቀስ በቀስ ሁኔታውን በማመቻቸት ሙሉ ቀን እንዲያስተምሩ ይደረጋል። ከአሁን በኋላ የሚከፈቱ ት/ቤቶች ግን ትምህርት የሚሰጡት በሙሉ ቀን ፕሮግራም ይሆናል። የተጓዳኝ ትምህርት ከክፍል ትምህርት ጋር ተቀናጅቶ ከክፍል ውጭ ይሰጣል።

1.6.8. የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም

የተጓዳኝ ትምህርት ከክፍል ትምህርት ውጭ የመማር ማስተማር ሥራ ለማገዝ የሚሰጥ ትምህርት ሆኖ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል። ተማሪው የበለጠ እውቀት እንዲገበይ ለመርዳት፣

- ተማሪው ለሙያ ሥራ አክብሮትና ጥሩ አመለካከት እንዲኖረው ለማድረግ፣

- ተማሪዎች ዕምቅ ችሎታቸውን በማውጣትና በማዳበር በፍላጐታቸውና የሙያ መስክ ለመምረጥ እንዲችሉ ዕድል ለመስጠት፣
- ችሎታቸውን በሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀት እንዲያዳብሩ፣
- የሥራ ፍላጐትና ፍቅር ለመፍጠርና ለማዳበር፣
- ተማሪዎች ማህበራዊ ግልጋሎቶችን እንዲሰጡ ለማበረታታት፣
- በክፍል ውስጥ በሚሰጡ ትምህርቶች ሊገኙ የማይችሉ የማቀድ፣ የመምራት፣ የማስተባበርና የመገምገም፣ ኃላፊነትን የመቀበል ውሳኔ የመስጠትን ችግሮችን በራስ ተነሳሽነትና በፈጠራ የመፍታትን ክህሎቶችንና ልምዶችን ለማዳበር፣
- ትርፍ ጊዜያቸውን ትምህርት በሚሰጡ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዲያሳልፉ ለማድረግ፣ ተጨማሪ ደስታና ልዩ ስሜት ለመፍጠር፣
- በጥልቀትና በስፋት እንዲሰጡ የሚደረጉ የትምህርት ዓይነቶች አማካይነት ለሚደክሙ ተማሪዎች ልዩ እርዳታ ለመስጠት፣
- አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮችን፣ አዳዲስ ክስተቶችንና ግኝቶችን ለተማሪዎች ለማስተዋወቅና ብሎም በመፍትሄ ሰጪነት ለማሳተፍ፣

የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም በትምህርት ቤቱ አቅምና እቅድ መሠረት የተለያዩ ክበባትንና ቡድኖችን በማቋቋም በክፍል ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርቶች በእያንዳንዱ ተማሪ ዝንባሌ፣ ፍላጐትና ችሎታ መሠረት ያደረገ እውቀትንና ክህሎትን ያዳብራል።

የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራም የሚከናወነው መደበኛውን የትምህርት ጊዜ ሳይሻማ አንዳንድ ሥራዎችን ለመስራት ያስችላል። እንዲሁም ተማሪዎች ጊዜያቸውን እንደፍላጐታቸው አራዝመውና አሳጥረው እንዲሰሩ ይረዳቸዋል። ፕሮግራሙ እንደተማሪው ዕድሜና ጥንካሬ በሳምንት ከ4 ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይካሄዳል።

1.6.9. የመማር ማስተማር መመሪያዎች

1.6.9.1. አጠቃላይ መመሪያዎች፣

- ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣
- የየትምህርቱ ዓይነት መርሀ ትምህርቶች፣
- የመምህሩ መምሪያዎችና መርጃ መጻሕፍት በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣
- የተማሪው መጽሐፍ በትምህርት ዓይነትና በክፍል ደረጃ፣

- የትምህርት ካሌንደር።

1.6.9.2. የልዩ ፍላጐት ትምህርት መመሪያዎች

- በመደበኛ ትምህርት የተዘጋጁት እንደተጠበቁ ሆነው በተጨማሪም
  - ማየት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
  - መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
  - የአእምሮ እድገት ዝግመት ያለባቸው ሕፃናት ትምህርት መመሪያ፣
  - የልዩ ፍላጐት ትምህርት መርሃግብር እስትራቴጅ፣

1.6.9.3. ሌሎች ልዩ ልዩ መመሪያዎች

- የአጠቃላይ ትምህርት አመራር አደረጃጀት የህብረተሰብ ተሳትፎ የፋይናንስ መመሪያ (Blue Book)፣
- የትምህርት ቤት አመራርና አስተዳደር መመሪያ፣
- አጠቃላይ የትምህርትና የሥልጠና ፖሊሲ፣
- የአርብቶ አደር እስትራተጂ፣
- ስለግል የትምህርት ተቋሞች ፈቃድ አሰጣጥና ቁጥጥር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብና ማብራሪያ /ለግል ት/ቤቶች/፣
- አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት፣
- የማዕከልና የክልል አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 41/85፣
- የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል መመሪያ /ቀድሞ የተዘጋጀው/፣
- የት/ቤቶች ተጨማሪ በጀት መመሪያ (School grant manual)፣
- አገር አቀፍ የሴቶች ትምህርት እስትራተጂ፣
- የመምህራን ልማት ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የት/ቤት መሻሻል ፕሮግራም ልዩ ልዩ መመሪያዎች፣
- የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጅ፣
- የሥነ-ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት ፕሮግራም መመሪያዎች፣
- የትምህርት ሕግ።

1.7. የማስተማር ዘዴ /Teaching Methodology/

በት/ቤቶች ካሉት ችግሮች መካከል በዋናነት በርካታ ተማሪዎች በትምህርታቸው በሚፈለገው መጠን ውጤታማ ሆነው አለመገኘት ነው። ለዚህ ምክንያት ይሆናሉ

ተብለው ከሚገመቱት ውስጥ፡-

- ተማሪዎች፣ ወላጅና ት/ቤት በሚፈለገው መጠን በትምህርቱ ሥራ በቅንጅት አለመሳተፍና
- የትምህርቱ አሰጣጥ ማራኪና ሳቢ ባለመሆኑ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ አዘወትሮ መቅረትና ማቋረጥ ወ.ዘ.ተ. ናቸው።

ይህን ችግር ለመቅረፍ ት/ቤቶች፣ ወላጅ፣ የአካባቢው ህብረተሰብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በጋራ በመወያየት ተማሪዎችን ሊያበረታታና ሊያሳትፍ የሚችል ትርጉም ያለው የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ሊቀይሱ ይገባል። ስለመምህራን የጊዜ ሰሌዳና የሪሶርስን አጠቃቀም በተመለከተ **ለተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ** ተግባራዊነት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪ ተኮር እና ብቃትን መሠረት ያደረገ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ይከተላሉ። ይህም እው ሊሆን የሚችለው የሚከተሉትን ማድረግ ሲቻል ነው።

- የት/ቤቱ ቀዳሚ ዓላማና ተግባር የተማሪዎችን ፍላጐት ሚሟላት ላይ ማተኮር፣
- ለሁለም ተማሪዎች ስኬታማነት /ውጤታማነት/ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ዲሞክራሲያዊ የሆነ ግንኙነትን በማጠናከር ተማሪዎች ካለምንም ፍርሃትና መሸማቀቅ ትምህርታቸውን እንዲማሩ ማድረግ፣
- የመማር፣ የትምህርት መሻሻል፣ የትምህርት አኩልነት፣ የትምህርት ፍትሃዊነትና መከባበር የት/ቤት ባህል ማድረግ፣

* እንደአጠቃላይ መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ለሚሰጡ ትምህርቶች የተማሪዎችን የግልና፣ የቡድን ችሎታ፣ ፍላጐት፣ ዕድሜ፣ የመማር ዘይቤና ቀዳሚ ተሞክሮ ላይ የተመሠረተ የትምህርት አቀራረብና የምዘና ሥርዓት ሊከተሉ ይገባል።

1.8. የትምህርት ምዘናና የማለፊያ ነጥብ

የአገራችን የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ትኩረት ከሰጣቸው ክፍሎች አንዱ የትምህርት ምዘና ጉዳይ ነው። ተማሪዎች በየክፍል ደረጃው የሚሰጠውን ትምህርት በተሟላ ሁኔታ በመማር የባህሪ ለውጥ ለማሳየታቸው የመማር ማስተማሩን ክንውን ለማሻሻልና የትምህርት ተግባር በጥራት መካሄዱን ለማረጋገጥ የትምህርት ምዘና ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። በአጠቃላይ የትምህርት ምዘና የትምህርት ሂደት አካል

እንደመሆኑ መጠን በጥራት መለኪያነትም የሚያገለግል መሣሪያ ነው።

ተማሪዎች ተገቢውን እውቀትና ክህሎት መጨበጣቸውን እንዲሁም መምህራን በአግባቡ ማስተማራቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ መረጃ ለመሰብሰብ በመምህራን የሚካሄደው ተከታታይ ምዘና (Continuous Assessment) ዋነኛውና እጅግ አሰፈላጊ የትምህርት ምዘና አካል ነው።

ስለሆነም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከ1ኛ-3ኛ ባሉት ክፍሎች የተከታታይ ምዘና ስልት ሆኖ ነፃ የክፍል ክፍል ዝውውር ይደረጋል።

- ከ4ኛ-7ኛ ክፍሎች ከተከታታይ ምዘና በተጨማሪ የማጠቃለያ ግምገማ በማካሄድ ወደሚቀጥለው ክፍል የሚዘዋወሩት በየደረጃው በተቀመጠው የምዘና ሥልት መሠረት ሆኖ መንግሥት ለት/ቤቶች በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይሆናል።
- ከ4ኛ-7ኛ ክፍሎች ወደሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ማለፍ ላልቻሉ ተማሪዎች የክልሉ ትምህርት ቢሮ ክፍል መድገምን በሚመለከት ለትምህርት ተቋማት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል።
- ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል ለመዛወር ፈተናውንም ሆነ የማለፍያ ነጥብ ክልሎች በሚያወጡት መመሪያ መሠረት ይፈፀማል።

1.9. የተማሪዎች ሚና (students' role)

በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ለውጥ ሊመጣ ከሚችልባቸው ዋነኛ ጉዳዮች መካከል የተማሪዎች የራሳቸው ጥረት አንዱ ሲሆን ተማሪዎች በጥሩ ዲስፕሊን ታንፀው የትምህርት ቤትን ደንብና ሥነ-ሥርዓት በማክበር ትምህርታቸውን በንቃት የመከታተልና ለጥሩ ውጤት በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም ከመምህሩ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ እየተደረገላቸው የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

- በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ መምህሩ የሚሰጠውን ትምህርት በጥሞና መከታተል፣ ከት/ቤት ያለበቂ ምክንያት ያለመቅረት፣ መልመጃዎችንና የቤት ሥራዎችን እንዲሁም የችሎታ መመዘኛዎችን ሠርተውና አጠናቀው በጊዜ ማቅረብ፣
- የት/ቤቱ አመራር አካላት የሚሰጡትን ምክር፣ ድጋፍና መመሪያ በአግባቡ በመፈፀም በዲስፕሊን የታነፀ ሆኖ መገኘትና ጤናማ የመማር ማስተማር ሂደት በት/ቤቱ ውስጥ እንዲኖር አስተዋፅኦ ማድረግ፣
- የት/ቤቱን የደምብ ልብስ መልበስና በአጠቃላይ ሥነ-ሥርዓትን የተከተለ

አለባበስ (በአካባቢው ህብረተሰብ ተቀባይነት ያለው አለባበስ) የሚለብሱ፣ አካላዊ ንጽህናቸውን የጠበቁና በሌሎች ጓደኞቻቸው ዘንድም በመልካም አርአያነት የሚጠቀሱ ሆኖ መገኘት፣

- በቡድን በመስራት እርስ በርስ በመረዳዳትና በመማማር በጋራ የመሥራትን፣ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን እና የመቻቻል ባህልን ማዳበር፣
- በተለያዩ ክበባትና ኮሚቴዎች ውስጥ በመሣተፍ እውቀትና ክህሎት የመቅሰም ፍላጐትና ችሎታ የላቸው መሆን፣
- የሀገሪቱን ህገ መንግሥት ጠንቅቆ በማወቅ በት/ቤት ግቢም ሆነ ውጭ መብታቸውን ማስከበርና ግዴታቸውን በአግባቡ መወጣት፣
- ለት/ቤቱ ማህበረሰብ አክብሮት ያላቸውና ት/ቤቱን የሚወዱ በዚህም የተነሣ ትርፍ ጊዜያቸውን በት/ቤቱ ውስጥ የቲቶሪያልና የማካካሻ ፕሮግራሞች ላይ በመሳተፍ የተሻለ ውጤት ማምጣት፣
- በቤተሙከራዎች ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ሆነው በቤተመጽሓፍት አዘወትረው በመጠቀም ተግባራዊና ንድፈ ሀሳባዊ ዕውቀትን ማዳበር፣
- የመጠየቅ፣ የመመራመርና የማወቅ ፍላጐታቸው ከፍተኛ የሆነና በራስ የመተማመን ብቃት ለማዳበር የሚተጉ፣
- የመማር ማስተማሩን ሂደት ከሚያደናቅፉ ነገሮች /ሞባይል መጠቀም፣አልኮል ጠጥቶ ክፍል መግባት ወዘተ/ መቆጠብ።

1.10. የወላጆች ሚና (parents role)

ወላጆች ከት/ቤት ሥራ ጋር የተያያዙ የመማርና የማስተማር ሂደትን የሚያጐልብቱ የተለያዩ ግልጋሎቶችን መስጠት ይጠበቅባቸዋል። ወላጆች የልጆቻቸው የወደፊት ዕጣ ፈንታና የሀገራቸውን እድገት ሊሳካ የሚችለው የችግሮች ሁሉ መፍቻ በሆነው በትምህርት ሥራ በሚያስመዘግቡት ውጤት ላይ መሆኑ ሊገነዘቡ ይገባል። ስለሆነም ተማሪዎች ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት እንዲያገኙ ወላጆች የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን ይጠበቅባቸዋል።

- ለት/ቤቶች አስፈላጊ የገንዘብ ድጋፍና የትምህርት ቁሳቁሶችን በማሟላት ት/ቤቶችን ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- ከት/ቤቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር በት/ቤቶች አመራር ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት፣
- የተማሩ ወላጆች በት/ቤት በመገኘት ቲቶሪያል በመስጠትና በሌሎች ትምህርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ በመሳተፍ ለተማሪዎች ውጤት መሻሻል የበኩላቸውን

አስተዋጽኦ ማድረግ፣

- ለልጆቻቸው ለትምህርት የሚያስፈልጓአቸውን የትምህርት ቁሳቁሶች ማሟላት፣
- በተለያዩ ጊዜያት ት/ቤት ድረስ በመምጣት ስለልጆቻቸው ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ለተሻለ ውጤት እንዲበቁ ማስቻል፣
- ልጆቻቸው የቤት ሥራ ለመሥራትም ሆነ ለጥናት ምቹ አካባቢና የጥናት ጊዜ እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ተማሪዎች በትምህርት ገበታቸው አዘወትረው መገኘታቸውንና የት/ቤቱን ህግና ሥነ- ሥርዓት መጠበቃቸውን ከት/ቤቱ ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ ጥረት ማድረግ፣

1.11. ትምህርት ቤቱ ለህብረተሰቡ ማሳወቅ የሚገባው

በት/ቤቶችና በህብረተሰቡ መካከል ጥብቅ ትሥሥር ሊኖር ይገባል። ት/ቤቶች ራሳቸውን እንደ ደሴት ሳይቆጥሩ ህብረተሰቡን በትምህርቱ ሥራ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህም፡-

- ወላጆች አቅም በፈቀደ መጠን ለልጆቻቸው የተመጣጠነ ምግብ፣ በቂ የጥናት ስፍራና የእረፍት ጊዜ እንዲሰጡአቸው ማበረታታት፣
- ልጆች የቤት ሥራና ሌሎች ከትምህርት ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥራዎች ሲሰጡአቸው ወላጆች እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ግንዛቤ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ለወላጆች በመደበኛነት ስለልጆቻቸው የትምህርት አቀባበልና ክትትል ምክር በመስጠት የልጆቻቸው የትምህርት ውጤት እንዲሻሻል አቅዶ መንቀሳቀስና ተግባራዊ ማድረግ፣
- በተማሪ ውጤትና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ፎርም በማዘጋጀት ለወላጅ በየጊዜው የሚያሳውቁበት መንገድ በማቀድ ሥራ ላይ ማዋል፣
- በት/ቤት በኩል የሚወጡ ማስታወቂያዎች ለወላጆች ግልጽና በቀላሉ ሊረዱዋቸው በሚችል መልኩ አዘጋጅቶ መተግበር፣
- በት/ቤት እቅድ ዝግጅት ወላጆች ከመምህራን ጋር ተሳትፎ እንዲኖራቸው መጋበዝ፣
- የወላጆች ልማን የሆኑ ትምህርታዊ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ለወላጆች እንዲደርሱ ማድረግ፣
- የወላጆችና የት/ቤት ግንኙነት ለማጠናከር ወላጆችን ያሣተፉ ትምህርታዊ መዝናኛ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣

- በወላጆች ቀን ወላጆች ት/ቤት በመገኘት የት/ቤቱን አጠቃላይ እንቅስቃሴና የልጆቻቸውን የትምህርት ውጤት አውቀው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ አቅዶ ተግባራዊ ማድረግ፣

1.12. በትምህርት ሥራ ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎ

ህብረተሰቡ ትምህርት ቤቶችን በማሻሻል፣ በመገንባት፣ የውስጥ ገቢን በማሳደግ፣ በትምህርት አመራርና በሥርዓተ ትምህርት ቀረፃ በባለቤትነት ስሜት በመሳተፍ የትምህርትን ጥራት ለማሻሻል ጉልህ ሚና መጫወት ይኖርበታል። ይህም፡-

- ት/ቤት ሲቋቋም ማህበረሰቡ የሚፈልገውን ጥቅም እንዲሰጥ ሆኖ መደራጀቱን ያረጋግጣል።
- ለት/ቤቶች መሻሻል ባለው አቅም የገንዘብ ድጋፍና የትምህርት ቁሳቁሶች ያሟላል።
- በት/ቤቶች በተለያየ የአመራር ደረጃ በመሳተፍ ላይ ጉልህ ሚና ይጫወታል።
- የተማሩ የህብረተሰብ ክፍሎች በት/ቤቶች በመገኘት በቲቶሪያልና በሌሎች የትምህርት እንቅስቃሴዎች ላይ ድጋፍ በማድረግ የትምህርቱን ጥራት ከፍ እንዲል የራሳቸውን ድርሻ ይወጣሉ።
- ለችግረኞችና ለወላጅ አልባ ህፃናት ድጋፍና እንክብካቤ በማድረግ ከትምህርታቸው እንዳይተጓጎሉ ጥረት ያደርጋል።
- ከት/ቤቱ አስተዳደር ጋር በመተባበር ዕድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ህፃናት ወደ ት/ቤት እንዲመጡና ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።
- በተለያዩ የትምህርት ኮሚቴዎች በመወከል ከእቅድ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ትግበራ ሂደት ላይ በመሳተፍና አፈፃፀሙንም በመከታተልና በመቆጣጠር የትምህርቱ ሥራ በአግባቡ እንዲካሄድ እገዛ ያደርጋል።
- በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ላይ ተሳትፎ በማድረግ ትምህርቱ ተገቢነትና ተጨባጭነት እንዲኖረው በማድረግ በኩል ድርሻውን ይወጣል።

1.13. ልዩ ልዩ ድጋፍ ሰጪ አገልግሎቶች

1.13.1. የሬዲዮ ትምህርት

<u>ሬደዮ ለመደበኛ ትምህርት ሂደት ያለው ጠቀሜታ</u>

የመደበኛ ትምህርት ሲባል ትምህርት የሚሰጥበት ቦታ ተዘጋጅቶ ሕንፃው ተሰርቶ ለትምህርት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ተሟልተው፣ ሥርዓተ ትምህርት ተዋቅሮ፣

የመማሪያ መጻሕፍት ተዘጋጅተው፣ መምህር ተቀጥሮ የጊዜ ሰሌዳው ወጥቶ በሙሉ ጊዜ የሚካሄድ የትምህርት ሂደት ነው።

የአንድን አገር እድገት ለማፋጠን ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንዱና ዋነኛው ትምህርት ነውና ትምህርቱ ውጤታማ የሚሆነው ደግሞ በአቀባዩና በተቀባዩ መካከል ስኬታማ የሆነ ተግባቦት (effective Communication) ሲኖር ነው። ስለሆነም ተግባቦትና ትምህርት በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው። መማር፣ ማወቅና የአስተሳሰብ አድማስን ማስፋት የተግባቦት ውጤት ነው። ስለዚህ ለመደበኛም ሆነ መደበኛ ላልሆነው ትምህርት ፌድዮ አማራጭ ያልተገኘለት መገናኛ መሣሪያ ነው።

የሬዲዮ ትምህርት ከሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች የተመረጠበት ምክንያት፡-

- ወጪው አነስተኛ በመሆኑ፣
- ትምህርትን በስፋት ለማዳረስ አመቺ በመሆኑ በተለይ ለገጠሩ ህብረተሰብ፣
- በአንድ በተወሰነ ሰዓት ብዙ ሰው ማስተማር ማስቻሉ፣
- የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እገዛ ማድረጉ፣
- የባለሙያዎችን እውቀትና ልምድ በቀላሉ ወደ ክፍል ተማሪዎች ማምጣት መቻሉ፣
- የጥቂት ብቁ መምህራንን የማስተማር ዘዴና ልምድ ለሌሎች ለማካፈል ማስቻሉ፣
- በየት/ተቋማት ውስጥ ያለውን የትም/ድጋፍ ሰጪ መሣሪያዎች ችግር ማቃለሉ፣ ወዘተ... ናቸው።

<u>የመደበኛ ትምህርት ሬዲዮና ሥርዓተ ትምህርት ቅንጅት</u>

የመደበኛ ትምህርት ሬዲዮ ፕሮግራም፣

- ከ1ኛ - 8ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ይዘጋጃል፣
- እንደ የሁኔታው በእያንዳንዱ የት/ዓይነት እየተዘጋጀ ይሠራጫል፣
- በአገሪቱ ሥ/ትምህርት መሠረት ይዘጋጃል።

ይህም በመሆኑ በትምህርት ሬዲዮና ሥርዓተ ትምህርት ዓላማዎች፣ ይዘቶች የአቀራረብ ዘዴዎችና ግምገማ መካከል የጠበቀ ግንኙነት ሊኖር ይገባል።

<u>መደበኛ የሬዲዮ ትምህርት ሚና</u>

የመደበኛ ትምህርት ሬዲዮ ፕሮግራም በመደበኛ ትምህርት ሥርዓት ውስጥ ተማሪዎችን ዓላማ ያደረጉ <u>ሦስት</u> ሚናዎች አሉት።

1. በማጠናከሪያነት (enrichment)
2. በመማር መድብልነት (learning resources)

3. በቀጥታ በማስተማሪያነት (Bates, 1984)

<u>የሬዲዮ ትምህርት ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈለጉ ዝግጅቶች</u>

- የሬድዮ ትምህርት መቀበያ ሬድዮኖች፣
- የሬድዮ ማዕከላት ወይም የሬድዮ መማሪያ ክፍሎች፣ የመብራትና የስኬት እንስታሌሽን፣
- የሬድዮ ትምህርት የሥርጭት የጊዜ ሰሌዳ፣
- በእያንዳንዱ የት/ዓይነት የተዘጋጀ የሬድዮ የመምህሩ መምሪያ።

<u>ባለሙያዎችን በተመለከተ</u>

- ባለሙያዎቹ ከመምህራን ይመለመላሉ፣
- በሬድዮ ትምህርት ሥልጠና የወሰዱ መሆን ይኖርባቸዋል።

የ2001 ዓ.ም የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት ፕሮግራም

(ከለገዳዲ ትም/ማሰራጫ ጣቢያ የተወሰደ)

የክፍል ፔሬድ	የክፍል ፔሬድ ሰዓት መለ ቀን	የሬዲዮ ሥርጭት ሰዓት	ሰኞ		ማክሰኞ		ረቡዕ		ሐሙስ		አርብ	
			የት/ዓይነት	ክፍል	የት/ዓይነት	ክፍል	የት/ዓይነት	ክፍል	የት/ዓይነት	ክፍል	የት/ዓይነት	ክፍል
1	2፡15 - 3፡00	2፡20 - 2፡35	እንግሊዝኛ	3	እንግሊዝኛ	3	እንግሊዝኛ	3	እንግሊዝኛ	3	እንግሊዝኛ	
2	3፡05 - 3፡50	3፡10 - 3፡25	እንግሊዝኛ	1	እንግሊዝኛ	1	እንግሊዝኛ	1	እንግሊዝኛ	1	አካባቢ ሳይንስ	
		3፡55 - 3፡50	ሕብረት	5	ሣይንሰ	5	እንግሊዝኛ	8	አማርኛ	6	እንግሊዝኛ	
3	3፡55 - 4፡40	4፡00 - 4፡15	አማርኛ	4	አካባቢ ሳይንስ	2	አማርኛ	1	አካባቢ ሣይንስ	3	አማርኛ	
	4፡40 - 4፡55	እረፍት	እረፍት		እረፍት		እረፍት		እረፍት		እረፍት	
4	5፡00 - 5፡45	5፡30 - 5፡45	አማርኛ	8	አካባቢ ሳይንስ	4	አማርኛ	8	አማርኛ	7	ሳይንስ	
5	5፡50 - 6፡35	6፡15 - 6፡30	ሳይንሰ	6	ሕብረተሰብ	5	እንግሊዝኛ	5	አካባቢ ሳይንሰ	1	አካባቢ ሳይንስ	
6	8፡00 - 8፡45	8፡05 - 8፡20	እንግሊዝኛ	4	እንግሊዝኛ	4	እንግሊዝኛ	4	እንግሊዝኛ	4	አካባቢ ሳይንስ	
		8፡25 - 8፡40	አካባቢ ሣይንሰ	3	ሐብረት	6	አማርኛ	7	ሳይንሰ	6	አማርኛ	
7	8፡50 - 9፡35	8፡55 - 9፡10	እንግሊዝኛ	2	እንግሊዝኛ	2	እንግሊኛ	2	እንግሊዝኛ	2	አማርኛ	
	8፡15 - 9፡30	9፡15 - 9፡30	ሕብረተሰብ	6	እንግሊዝኛ	5	እንግሊዝኛ	6	እንግሊዝኛ	7	እንግሊዝኛ	

ማሳሰቢያ፡-

- የእንግሊዝኛ IRI ፕሮግራሞች ከሰኞ - ሐሙስ በየቀኑ አዳዲስ ፕሮግራሞች ስለሚሰራጩ ለእያንዳንዱ ክፍል ሁሉንም IRI ስርጭት ማስደመጥ ይገባል።
  - የ1ኛ መንፈቀ ዓመት የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት መስከረም 26/2001 ተጀምሮ በየሳምንቱ እየተካሄደ ጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም ይጠናቀቃል።
  - የ2ኛ መንፈቀ ዓመት የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት የካቲት 16/2001 ተጀምሮ በየሳምንቱ እየተካሄደ ግንቦት 21/2001 ዓ.ም ያበቃል።
  - የ0ውደ ዓመት /የሕዝብ/ ዕለቶች የሬዲዮ ትምህርት ሥርጭት አይኖርም።

ከላይ በተገለፀው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ክልሎች እንደየአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቀቀማቸውና የጊዜ ሰሌዳቸው መሠረት በማጣጣም መጠቀም ይችላሉ።

1.13.2. ቤተ ሙከራ

የመማር ማስተማር ሥራ ውጤታማ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ትምህርቱ በንድፈ ሀሳብ ላይ ብቻ ተወስኖ ከሚሰጥ ይልቅ በተግባር ተደግፎ ሲሰጥ እንደሆነ የትምህርት ባለሙያዎች አበክረው ያስረዳሉ። በተለይ እድሜአቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ይህ ጉዳይ የበለጠ ይመለከታቸዋል። ተማሪዎች ፈጣሪዎችና ተመራማሪዎች የሚሆኑት ዕለት በዕለት የሚሰጠውን ትምህርት ራሳቸው በተግባር ሲሞክሩትና ከውጤቱም መማር ሲችሉ ነው። በቤተ ሙከራ የሳይንስ መርጃ መሣሪያዎች መኖር ዓላማ የምልከታ፣ የመለካት፣ የመመራመር፣ የዲዛይን፣ ግንባታና አካባቢን የማጥናት ክሂሎችን ተማሪው እንዲያጐለብት ለማድረግ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ሊኖሩ የሚገቡ የሣይንስ መርጃ መሣሪያዎችም የሚከተሉት ናቸው።

- ቻርቶች /ሥዕሎች ፎቶግራፎች፣
- ሞዴሎች፣
- ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች/ቢከር፣ ፔትሪ ስሃን፣ ፍላስክ... አካላት፣
- የተሟሉ የሣይንስ ኪቶች፣
- ተፈጥሮአዊና ማኅበራዊ ቅርሶች፣
- መገልገያ መሣሪያዎች፣
- መለኪያ መሣሪያዎች /ርዝመት፣ ግዝፈት፣ አንግል፣ ይዘት፣ ጊዜ/፣
- የእጅ መሣሪያዎች /መዶሻ፣ መጋዝ/፣
- የነበሩ ናሙናዎች (Preserved specimen)፣
- በአካባቢው የሚገኙ /ህይወት ያላቸውና የሌላቸው/ ነገሮች፣

1.13.3. የቤተመጻሕፍት አገልግሎት

ሀ/ <u>የቤተ መፃህፍት አደረጃጀት</u>

የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መፃሕፍት የሚደራጀው በት/ቤቱ ግቢ ውስጥ ሆኖ ከተለያዩ አዋኪ ድምፆች የራቀና ለት/ቤቱ ህብረተሰብ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት በሚችል መልኩ መሆን አለበት።

የቤተ መጻሕፍት በአንድ ት/ቤት መኖር ፋይዳው፡-

- ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና እንዲሁም ለአካባቢው ህብረተሰብ አገልግሎት የሚሰጡ መጻሕፍትን በማቅረብ የንባብ ፍላጎትን ለማዳበር፣
- በተለያዩ የትምህርት ርዕሶች ዙሪያ ለሚካሄዱ ጥናቶች በምንጭነት ለማገልገል፣
- ተማሪዎች ትርፍ ጊዜአቸውን በቤተመፃሕፍት መጻሕፍት በማንበብና እንዲያሳልፉ ለማድረግ ነው።

ለ/ <u>የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት የተለያዩ የመሥሪያ ክፍሎች</u>

የአንድ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት ስፋትና ይዘት እንደየት/ቤቱ ተማሪዎች ብዛትና የሚያስተግናደው የክፍል ደረጃ የሚለያይ ሲሆን፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት የሚከተሉት የመገልገያ ክፍሎች ይኖሩታል።

- የመጻሕፍትንና የመጽሔቶችን መደርደሪያዎች ጭምር የሚይዝ ስፋቱ 10 ሜ X 20 ሜ = 200 ካሬ ሜትር የሆነ የማንበብያ ክፍል፣
- ለመጽሐፍ መዋሻና መቀበያ ስፍራ 30 ካሬ ሜትር፣
- ስፋቱ 5 ሜ X 8 ሜ. = 40 ካሬ ሜትር ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የቤተ መጻሕፍት ሥራ ማከናወኛ ክፍል፣
- አዳዲስ መጻሕፍትና መጽሔቶች ማስታወቂያ ስፍራ 9 ካሬ ሜትር፣
- ለት/ቤቱ ስታፍ (staff) አባላት ማንበቢያ ስፍራ 20 ካሬ ሜትር።

ሐ/ <u>ቤተ መጻሕፍት መያዝ ያለበት ክምችት</u>

ለሰው ልጅ የመረጃና የዕውቀት ምንጭ ከሆኑት ነገሮች መካከል በዋናነት መጻሕፍት ናቸው። ሰዎች መፃሕፍትን በማንበብ ስለዓለምና ስለራሳቸው የሚኖራቸው የግንዛቤ አድማስ ያሰፋሉ።

ስለሆነም አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ቤተ መጻሕፍት ለመማር ማሰተማሩ ተግባር ድጋፍ የሚሰጡ በተለያዩ ርዕሶች ላይ የተጻፉ መፃሕፍት፣ ሞኖግራፎች (monograph)፣ በተከታታይ የሚታተሙ መጽሔቶች፣ ሥዕላዊ መግለጫዎች፣ የኦዲቪዥዋል ማቴሪያሎች፣ ለጥናትና ምርምር የሚያገለግሉ መጻሕፍትና የጥናት ውጤቶች፣ መዝገበ ቃላት፣ መዝገበ ጥበብ አልሚናክ ዓመታዊ ስንክሣር የሕይወት ታሪክ፣ ጋዜጦች፣ በራሪ ጽሑፎችና ካርታዎች ሊኖሩት ይገባል።

<u>በአንድ ት/ቤት ውስጥ የሚቋቋመው ቤተመጽሐፍት</u>

- ከመማሪያ ክፍሎች የራቀ፣ በማጣቀሻና በክፍል ትምህርት መጻሕፍት የተሟላና የሰለጠነ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል።
- የመጻሕፍቱ ብዛትና አይነት ከተማሪ ቁጥር ጋር ተመጣጣኝ መሆን ይኖርባቸዋል።
- ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች በቂ ቅጂ ያላቸውን መጻሕፍት በውሰት እንዲጠቀሙበት ይደረጋል።
- ቤተመጻሕፍቱ መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች እንዲገለገሉበት ቀኑን ሙሉ ክፍት መሆን ይኖርበታል።

1.13.4. የት/ቤት ማበልጸጊያ ማዕከላት አደረጃጀት

የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላት ዋና ዋና ዓላማዎች

- የመማር ማስተማሩን ሂደት በጥናትና በምርምር ለማበልጸግ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- ሥርዓተ ትምህርቱን እንደየ አካባቢው ሁኔታ ማዳበር፣
- የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎችን ማዘጋጀት፣
- አጫጭር የሙያ ማስተዋወቂያ ፕሮግራሞችን ማካሄድ፣
- የመማር ማስተማሩን ሂደት የሚደግፉ የቤተ መጻሕፍት ዶክሜንቴሽንና የኦዶቪዙዋል አገልግሎቶችን ማሳደግና ማስፋፋት፤

በአጠቃላይ የማዕከላት ዋና ዓላማና ተግባር ከላይ የተገለጹትን በማከናወን ትምህርቱን ተጨባጭ የሚያደርጉ አዳዲስ ዘዴዎችንና ስልቶችን በመቀየስና የፈጠራ ሥራዎችን በማካሄድ ለትምህርቱ ጥራትና ጥልቀት ጠቃሚና ከፍተኛ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ነው።

ለዚህም አገልግሎት እንዲያመች በየወረዳው የተጠናከሩና የተደራጁ ማዕከላት እንዲኖሩ የሚደረግ ሲሆን በት/ቤት ደረጃ ደግሞ ከወረዳ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ከላይ የተጠቀሱትን የማዕከላት ዓላማ ተግባራዊ የሚያደርጉ የት/ቤት ቅርንጫፍ ማዕከላት ይቋቋማሉ።

ስለዚህ አንድ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በሰው ኃይልም ሆነ በማቴሪያል የተደራጀ የማበልፀጊያ ማዕከል ሊኖረው ይገባል።

1.13.4.1 በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከማዘጋጀት አኳያ ሊኖር የሚገባው ስታንዳርድ፣

- አንድ ስፋቱ 7 ሜ x 15 ሜ የሆነ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማዘጋጃ ክፍል፣
- አንድ ስፋቱ 7 ሜ x 8 ሜ የሆነ የሠርቶ ማሳያና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ማዋሻ ክፍል ሊኖር ይገባል።

1.13.4.2. በትምህርት ቤት ማበልጸጊያ ማዕከል ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ የእጅ ሥራ መሥሪያ መሣሪያዎች፣

ተ.ቁ	የዕቃው ዓይነት	ብዛት
1.	ስክሩድራይቨር	1
2.	አግድም ቆረጥ መጋዝ	1
3.	የብረት መቁረጫ መጋዝ	1
4.	መላጊያ ትለቁ	1
5.	መላጊያ ትንሹ	1
6.	ተጠቅላይ ሜትር /ባለ 3 ማትር/	1
7.	ቲ-ስኳር	1
8.	ትራይ ስኳር	1
9.	ድሮውንግ ኢንስትሩሜንት	4
10.	ፕሮትራክተር	1
11.	ትራያንግል ሂሺ ፕላስቲክ 30 60 90	2
12.	ትሪያንግል ሂሺ ፕላስቲክ 45 90	2
13.	የእንጨት መሰርሰሪያ	1
14.	የብረት መሰርሰሪያ	1
15.	የእንጨት ሞረድ	2
16.	የወረቀት መቁረጫ 61 x 61 ሳ.ሜ	1
17.	ትልቅ የብረት ማሠሪያ ሞርሣ	1
18.	ትንሽ የእንጨት ማሠሪያ ሞርሣ	1
19.	የብረት መሞረጃ ሞረድ	2
20.	ግራይንደር ቤንች ሃንድ	1
21.	የእንጨት መሮ	1
22.	ሴክላምፕ	2
23.	ፒንሣ	1
24.	ማዶሻ	1

1.13.4.3 በመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች /1-8/ ለየትምህርት ዓይነቱ ሊኖሩ የሚባቸው የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች

1.13.4.3.1. ለቋንቋ ትምህርት

1. የድምፅ መሣሪያዎች (Audio materials)
2. ቪዥዋል (Visual materials)
3. ቻርቶች (Charts)
4. የቃላት ካርድ (Word Card)
5. ፍላሽ ካርድ (Flash card)
6. ሻሽ ቦርድ (Shash board)
7. ሥዕሎች (Picture cards)
8. ክፍል ሊወሰዱ የሚችሉ ዕቃዎች (Realia)
9. ምልክቶች (Signs)
10. ፊልሞች /የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ

1.13.4.3.2. ለሂሣብ ትምህርት

No.	Description of Items
1.	Wooden black-board protractor (with handle)
2.	Set square
3.	Chalk compasses
4.	Black-board ruler
5.	Pegboards (for nail boards or geo-board)
6.	Balance (excluded if available in science laboratory)
7.	Plastic graduated beakers and funnels
8.	Geometrical surfaces and solid samples
9.	Graph-board with horizontal and vertical lines at the with-top comer (graph board)
10.	Set of mathematical instruments (students)
11.	Token money (Ethiopia)
12.	Abacus metal or wooden ten parallel wires each line containts too polished wooden heads.

1.13.4.3.3. ለኅብረተሰብ ትምህርት

1. የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች አትላስ
2. ፖንቶግራፎች
3. ቴርሞሜትሮች
4. የግድግዳ ካርታዎች
   - የዓለም ካርታ
   - የአፍሪካ ካርታ
   - የኢትዮጵያ ካርታ
   - የክልል ካርታ
5. ሌሎች /ግሎቦች/

1.13.4.3.4. ለሥነ ሥዕል ትምህርት

1. ለኮላዥ ሥራ የሚያገለግሉ የተለያዩ ዕቃዎች
2. ለንድፍ ሥራ " " "
3. ለሕትመት ሥራ " " "
4. ለቅርፃ ቅርጽ ሥራ " " "
5. ለቀለም ቅብ ሥራ " " "

1.13.4.3.5. ለሙዚቃ ትምህርት

1. መዝሙሮችና ምቶችን ለማጀብ የሚረዱ የሙዚቃ መሣሪያዎች /ሪትምስቲክ፣ ከበሮ ማራካሻ/ ፀናጽል፣ ትሪያንግል .../
2. የሙዚቃ ኖታዎችን ለማስለየት የሚረዳ የሙዚቃ መሣሪያ

1.13.4.3.6. የልዩ ትምህርት ማካሄጃ ተጨማሪ መሣሪያዎች

ማየት ለተሳናቸው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- የብሬል ወረቀት
- ስሌትና ስታይለስ
- የብሬል መጻሕፍት
- የብሬል ማስመሪያና ፕሮትራክተር
- አባከስ
- ቴፕሪኮርደርና ካሴት
- የታይፕ መኪናና የቴፕሪኮርደር መለዋወጫ
- ነጭ ባትሪ
- ኣፕታኮን /ዓይነ-ሥውራን ለንባብ የሚረዱበት መሣሪያ/ መጠነኛ የዕይታ ችሎታ ላላቸው
- በቅርበት የሚያሳይ ቴለቪዥን
- አቨርሄድ ፕሮጀክተር
- ትልልቅ ስፒል
- ባለትልቅ መስመር ወረቀት
- አጉሊ መነፅር
- ለማንበቢያ የሚረዳ
- የታይፕ መኪናና ቴፕሪከርደር

መስማት ለተሳናቸው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች

- መሣሪያዎች መንቀሳቀሳቸውን የሚያመለክት ብርሃን ማሳየት፣
- የማስጠንቀቂያ ደወል ለመተካት እንደባትሪ ያለ ነገር እንዲታይ ማድረግ፣
- በከፊል ለሚሰሙት ድምፅ አጉሊ መሣሪያ መጠቀም፣ ለምሳሌ፡- ረዳት የመስሚያ መሣሪያ፣
- ድምጽ አልባ የታይፕ መኪና መጠቀም፣

<u>ማቴሪያሎች</u>

- የዕይታ መሣሪያዎች፣ ብርሃን አስተላላፊ ወረቀት ፊልምና ካብሽን፣ ስላይድ ፊልምና ቻርት ለማሳያ አስፈላጊ ናቸው።

1.13.4.3.7. ለተፈጥሮ ሣይንሰ ትምህርት /Science Kit Items For Primary Schools/

No.	Items	Quantity
1.	Peg board stand with base	1
2.	Peg boards strip for moments	1
3.	Peg board strip	1
4.	Pulley-small	5
5.	Pulley-combined	1
6.	Pulley-combined	2
7.	Trolley	-
8.	10 Grm Mass	1
9.	20 Grm Mass	2
10.	50 grm Mass	3
11.	100 Grm Mass	2
12.	Scale Holder	1
13.	Block weight	-
14.	Clip-Large	4
15.	Clip-small	6
16.	Spindle-short 54mm long	5
17.	Spindle-long 90 mm long	2
18.	Spindle-Conical end 69 mm long	1
19.	Bi-convex Lense F 100 mm clear Plastic R 100 mm	2
20.	Semi-circular Block R. 30 mm clear plastic	1
21.	Bi-concave lense F-clear plastic R 100 mm	1
22.	Prism 90 – 45 Clear plastic	1
23.	Bi –convex Lense F 50 mm Clear Plastic R, -30mm k2-100mm	1
24.	Plane parallel Block-Clear plastic	1
25.	Plane Mirror mounted – 60x15 mm	2
26.	Curved Mirror	2
27.	Angle Bracket	2
28.	Iron clip	1
29.	Iamination set-30 pieces, mild steel strips 12x65mm	1
30.	Battery connector	6
31.	Contact Strip-Large	-
32.	Contact Strip-small 90x12mm	4
33.	Vibrator-Mild-Steel, 180x12mm	1
34.	Strip for magnets mild steel, 50X12m	1
35.	Flexible lead 120 mm with wedged ends	5
36.	Flexible lead 300 mm " " "	4
37.	Flexible lead 500 mm " " "	

2

38.	Coil 400 turn with square spia forcone	1
39.	Bush	1
40.	Spring connector	16
41.	Plastic sleeve	1
42.	Resistance wire-Nichrome 500 mm -100 mm per meter	
43.	Copper wire-Tinned 500 mm	1
44.	Copper wire insulated-singlestrand 500 mm	1
45.	Moving Iron with pointer	1
46.	Riged Plastic -50 mm long 32 mm diameter	1
47.	" " 150 mm " "	1
48.	Bulb holder – with long leads for optics	

1

49.	" " " short long for circuit board	3
50.	Inclined plane	1
51.	Hook for single pully	1
52.	" ' double pully	1
53.	Coil 30 turns	1
54.	String with coxs – 500 mm	1
55.	String with Hoozs – 750 mm	1
56.	" " " 1000 mm	1
57.	" " " 1250 mm	1
58.	Joined string with Hooks	1
59.	Knurled nut	25
60.	Rhehostat	1
61.	Plastic Tubing 1/8 100 mm long	1
62.	Test tube holder	1
63.	Test tube holder base	1
64.	Viewer	1
65.	Land lens	1
66.	Forcens	1
67.	Mounted needle	1
68.	Universal clip handle	1
69.	Plastic Tube -100 mm –Long	1
70.	Universal clip	1
71.	Plate with slites	1
72.	Test tube Brush	1
73.	Root marker	1
74.	Wooden Block	1
75.	Scalpel Handel	1
76.	Pointer for expassion experiment	1
77.	Current Blance lever	1
78.	Asbestos hat 150 mm square	1
79.	Copper electrode-cooper tube 80 mm long	2
80.	Carbon electrode-carbonrod in copper tube	2
81.	Spatila-stair less-140 mm long	1
82.	Deflagrating Spoon-stainless 220 mm long	1
83.	Beaker – 400 ml	1
84.	Dropper	1

85.	Themometer	1
86.	Set of slides – 13 slides	1
87.	Test tube – large	1
88.	Test tube disposable	6
89.	Filter punnel-plastic	1
90.	Petri-Dish	2
91.	Syringe 10 ml	2
92.	Cork Stopper-large	4
93.	Blades for Scalper	2
94.	Modeling clay, ½ packet	1
95.	Scissors	1
96.	Funnel	1
97.	Boiling tube	1
98.	Screw-long	2
99.	Screw-short	6
100.	Plastic cap	1
101.	Plastic cap with hole	1
102.	Plastic cap with glass tube	1
103.	Bulb-round	3
104.	Measuing cylinder 50 ml	1
105.	Delivery tube glass 245 mm long	1
106.	" " " 80 mm long	2
107.	Glass rod – 5x140 mm long	1
108.	Combustron tube 300 mm long 10-48 dia.	1
109.	Measurings silinder 10 ml	1
110.	Watch glass -75 mm diameter	1
111.	Rubber Bung large with 1 hole	1
112.	Rubber Bung large with 1 hole	1
113.	" " " " 2 holes	1
114.	" " small for 150x16 mm test tube	1
115.	" " " with 1 hole	2
116.	Cork stopper for 150x16 mm test bue	6
117.	Porcalain boat	1
118.	Plastic tubing with hole intended dia ¾ for Expansion experiment	1
119.	Rubber Bung with glass tube	1
120.	Crystalization Dish-plastic bottle 110 mm 2x85 cm Deep	1
121.	Boiling flask	1
122.	Crocodile clip with 300 mm lead	2
123.	Penlight Bulb	1
124.	Diode 50 V. lamp	1
125.	Dry cell-Di.6V 32mm dia. 55mm long	-
126.	Visking Tubing 15 cm	2
127.	Beader – 50ml heat resistant	2
128.	magnet – round	1
129.	Washer	6
130.	Hammer	1
131.	Halk saw	1

132.	Plier	1
133.	Screw driver	1
134.	Audus Apparatus	1
135.	Kit Box	1

1.13.5. የመጀመሪያ ዕርዳታ መሰጫ ክፍል

3.13.5.1. ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ለመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችና ባለሙያዎች

ተማሪዎች ካላቸው የአካልና የስሜት ዕድገት ባህሪያቸው እና ከትምህርት ቤት ግቢና ከት/ቤት ውጭ በሚፈጠሩ ችግሮች የተነሣ በተለያዩ መንገዶች ለበሽታና ለአደጋ ይጋለጣሉ። <u>ለምሳሌ</u> ያህል በጨዋታ ሜዳ ላይ እንዲሁም በሥራ ቦታዎች የወለምታ፣ የስብራት፣ የመቁሰልና የመድማት፣ በእባብ የመነደፍና በውሻ የመነከስ፣ በስለት ነገር የመቆረጥና የመወጋት፣ በልዩ ልዩ ሕመሞች ምክንያት /በስኳር በሽታ በሚጥል በሽታ/ አእምሯቸውን የመሳት፣ በውኃ የመስመጥ፣ የመታፈንና የእሳት አደጋ ሁኔታዎች ሊያጋጥማቸው ይችላል። በዚህን ጊዜ ጉዳት የደረሰበት ተማሪ ከፍተኛ የሕመም፣ የጭንቀት፣ የሁከት ሁኔታዎች ይታይበታል።

ይህን በመሳሰሉ ችግሮች ፈጥኖ በመድረስ የሕክምና እርዳታ የሚሰጥ የጤና ባለሙያ በቅርቡ ላይኖር ይችላል። በአቅራቢያው የጤና አገልግሎት ቢኖርም እንኳን እቦታው እስኪደርስ ድረስ በሽተኛው ሊጐዳ ይችላል። ሊሞትም ይችላል።

ስለዚህ በት/ቤት ቅጥር ግቢ የሚገኘው የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ ዋና አገልግሎቱ በሽተኛው ሐኪም ቤት ከመድረሱ በፊት ያለውን ችግር ለመቀነስ፣ እንዳይባባስ ለመርዳትና በሕይወት አቆይቶ ለሕክምና ባለሙያ ለማድረስ የሚያግዝ ፈጥኖ ደራሽ የነፍስአድን ሥራ ነው።

በመሆኑም አንድ ት/ቤት ይህን ሥራ ለማከናወን በየት/ቤቱ የሰለጠነ የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ ሰጪ ባለሙያ፣ የህክምና ዕርዳታ መስጫ መሣሪያዎችና የመጀመሪያ ህክምና ዕርዳታ መስጫ ክፍል (1st aid post) ሊኖሩት ይገባል።

በአንድ የመጀመሪያ ሕክምና እርዳታ መስጫ ሳጥን (first Aid Kit) ውስጥ

ሊኖሩ የሚገባቸው የሕክምና መሣሪያዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. Adhesive plaster 5 cm x 10 m rolls
2. 12 vow gauze bandage 8 cm x 5 rolls
3. Dissecting foreceps
4. Examination gloves
5. 1 battle dettol 250 ml.
6. Scissers 14 cm Gc.P
7. Elastic bandage 10 cm x 4.5m.
8. 2 elastic woven bandage 8 cm x 5m.
9. 12 vow gauze bandages 7.5 cm x 5m.
10. 4 triangulaire bandages
11. Cotton Wool 400 gm.
12. I pack handy plast ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ቁሳቁሶች ከነሳጥኑ በቀይ መስቀል ማኅበር በኩል ሊገዙ ይቻላል።

ከዚህም በላይ በውስጡ ያሉት ዕቃዎች ሲያልቁ የተወሰነ ገንዘብ ለቀይ መስቀል ማኅበር በመክፈል ማሟላት ይቻላል። ከ100 በላይ ተማሪዎች ላሉዋቸው ት/ቤቶች ሁለት ወይም ሦስት የመጀመሪያ ሕክምና ዕርዳታ ሳጥን ያስፈልጋል።

ሕክምናው ከት/ቤቱ አቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ በአቅራቢያ ወደሚገኙ የሕዝብ /ኮሚኒት/ ክሊኒኮች ይላካሉ።

1.13.6. ለመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የሰውነት ማጐልመሻ ትምህርት መሣሪያዎች

ተራ ቁ.	የመሣሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን ክብደት	ብዛት	ምርመራ
1	<u>ኳሶች</u>				
	- የእግር ኳስ	1-3	ቀላል የላስቲክ ኳስ	3	1 ለ80 ተማሪዎች
	- " "	4-6	ቁጥር 3	3	1 ለ80 ተማሪዎች
	- " "	7-8	ቁጥር 4	3	1 ለ80 "
	- ቅርጫት ኳስ	1-4	ቀላል የሚነጥር ኳስ	3	1 ለ100 "
	- " "	5-8	ሚኒ ባስኬት ቦል	3	1 ለ80 "
	- የእጅ ኳስ	1-4	ጁኒየር ሳይዝ	3	1 ለ80 "
	- " "	5-8	ሲኒየር ሳይዝ	3	1 ለ80 "
	- መረብ ኳስ	1-4	ጁኒየር ሳይዝ	3	1 ለ80 "
	- " "	5-8	ሲኒየር ሳይዝ	3	1 ለ80 "
	- ከባድ ኳስ	1-4	2 ኪሎ ግራም	2	2 በአንድ ክፍለ
	- " "	5-8	3 ኪሎ ግራም	3	ጊዜ " " "

ተራ ቁ.	የመሣሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን ክብደት	ብዛት	ምርመራ
2	**<u>የአትሌትክሰ መሣሪያዎች</u>**				
	- ጦር	4-6	500 ግራም	3	በአንድ ክፍለ ጊዜ
	- "	5-8	600 ግራም	2	" " "
	- "	5-8	700 "	3	" " "
	- ደስከስ	4-6	0.75 ኪ.ግ	3	" " "
	- "	7-8	1 ኪ.ግ	2	" " "
	- አለሎ	4-6	3 ኪ.ግ	3	" " "
	- "	7-8	4 ኪ.ግ	3	" " "
	- የከፍታ ዝላይ ቋሚ በጥንድ	1-8	ከብረት የተሠራ	1	ለት/ቤቱ
	- የከፍታ ዝላይ አግዳሚ	1-8		1	"
	- የሩጫ ሰዓት	1-8	ኤሌክትሮኒክስ	3	"
	- የሩጫ ማስነሻ ሽጉጥ				
	" " ጥይት/በፓኬት/	1-8		2	"
	- ሳንቃ	1-8		1	"
	- የሪሌይ ቅብብል ዱላዎች	1-8	28 ሳ.ሜ ርዝመት	8	ክብደቱ ከ50 ግራም ካልበለጠ እንጨት ወይም ስስ የብረት ቧንቧ የተሠራ
3	**<u>የጂምናስቲክ መሣሪያዎች</u>**				
	- ፍራሽ	1-8	12 ሳ.ሜ ውፍረት 1x3	3	ለት/ቤቱ
	- ተደራራቢ ሣጥን	1-8	ሜትር	3	"
	- በክ	1-8		1	"
	- አግዳሚ ወንበር /ቤንች/	1-8		2	"
	- ቀለበቶች	1-8	½ ሜትር ራዲየስ	20	"
4	**<u>ሌሎች</u>**				
	- ለመውጣት ለመውረድ የሚያገለግሉ ገመዶች	1-8	8 ሜትር ቁመት 7 ሣ.ሜ. ውፍረት		
	- የመዝለያ ገመድ	1-8	1.50 ሜ ርዝመት		
	- ለኢላማ መምታትና ለልዩ ልዩ ጨዋታዎች ማከናወኛ	1-8	አነስተኛ መጠን ያላቸው ከፕላስቲክ የተሰሩ ኳሶች	20	ለት/ቤቱ
	- ለኢላማ የሚያገለግሉ ሶኬትልስ			20	ከእንጨት ወይም ከፕላስቲክ የተሠራ
	- የካኪ ጨርቅ ከረጢቶች	1-8	20 x10 ሚ.ሜ	10	ሰአሸዋ የተሞሉ
	- የመምህሩ ቱታ	1-8	የሀገር ውስጥ	1	በዓመት
	- ሽራ ጫማ	1-8	" "	2ጥንድ	
	- ፊሽካ	1-8		2	ለት/ቤቱ
	- የኳስ መንፊያ ፓምፕ	1-8		2	"
	- የመረብ ኳስ መረብ	1-8	የሀገር ውስጥ	2	"
	- የባስኬት ቦል ቋሚ ከነሣንቃ ውና ከነቀለበቱ በጥንድ	1-8		1	
	- መለኪያ ሜትር	1-8	ባለ 50 ሜትር	1	"
	- የስፖርት ሹራብ /ማሊያ/ ከነቁምጣው	1-8		16	"

ተራ ቁ.	የመሣሪያ ዓይነት	የክፍል ደረጃ	መጠን ክብደት	ብዛት	ምርመራ
5	**<u>የስፖርት ሜዳዎች</u>** - የእግር ኳስ ሜዳ - የቅርጫት ኳስ ሜዳ - የእጅ ኳስ ሜዳ - የመረብ ኳስ ሜዳ - የከፍታ ርዝመት መዝለያ	 1-8 1-8 1-8 1-8 1-8	 110x90= 9900 ካ.ሜ 20x16 = 448 ካ.ሜ 42 x 22 = 924 ካ.ሜ 20 x 11 = 220 ካ.ሜ 20 x 15 =420 ካ.ሜ		የሩጫ መስመሮችን ያጠቃልላል

1.14. የትምህርት ደረጃ ማጠናቀቂያ መለኪያ /ስታንዳርድ/

ተማሪዎች በተዘጋጀላቸው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት የደረጃውን ትምህርት ማጠናቀቃቸውን ለማረጋገጥ ት/ቤቶች የሚከተሉትን መንገዶች ይከተላሉ።

- ለክፍል ደረጀው የተዘጋጀውን ትምህርት ቀድሞ በተቀመጠው ክ/ጊዜና የትምህርት ወቅት ተገኝተው መማራቸውን ያረጋግጣሉ።
- ተከታታይ ምዘናና የማጠቃለያ ፈተና መውሰዳቸውን እና በዝውውር ፖሊሲው መሠረት ወደ ሚቀጥለው ክፍል ለመግባት የሚያስችልና "የነበሩበትን ክፍል አጠናቋል" የሚል አጥጋቢ ውጤት ማምጣታቸውን ይረጋገጣል።
- ለክፍል ደረጃውና ለእርከኑ የተመደበውን ትምህርት ተማሪዎች በትክክል ማጠናቀቃቸውን በት/ቤቱ ወይም በብሔራዊ ፈተና ውጤት ይረጋገጣል።

1.14.1. በየክፍል ደረጃውና በየእርከኑ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች

- በየዓመቱ የክፍል ትምህርት ማጠናቀቂያ ወይም የሴሚስቴር ፈተና ውጤት መግለጫ ወይም የተጣራ ሪፖርት ካርድ ለተማሪ ይሰጣል።
- የአንድን እርከን ትምህርት ሳያጠናቅቅ በየእርከኑ መካከል ተማሪው ት/ቤት ቢቀይር ከሚለቅበት ት/ቤት የሚሰጠው ዝርዝር ውጤት የየክፍሉ የተጠናቀረ እና የመልቀቂያ /ትራንስክሪብት/ ህጋዊ ሠርቲፊኬት የተወሰነ የትምህርት ደረጃ ማጠናቀቂያ ማረጋገጫ ይሆናል።
- በየእርከኑ መጨረሻ ክፍል የሚሰጥ የትምህርት ውጤት ህጋዊ መግለጫ /ትራንስክሪብት/ እና የብሔሪዊ ወይም ክልላዊ ፈተና የሚሰጥበት ደረጃም ከሆነ የብሐራዊ ወይም የክልላዊ ፈተና ውጤት ህጋዊ መግለጫ ለሚቀጥለው

የትምህርት ደረጃ መብቃታቸውን ማረጋገጫ ይሆናል።

- በየአርከኑ መጨረሻ የሚሰጡ የትምህርት ማስረጃዎች ወይም ሰርቲፊኬቶች በማስተማሪያ ቋንቋ በአገር አቀፋዊ የሥራ ቋንቋ ወይም በክልላዊ የሥራ ቋንቋ ተዘጋጅተው ይሰጣሉ።

1.15. በየእርከኑ መጨረሻ የሚጠበቁ የተማሪዎች ፕሮፋይል /ባህሪያት/

1.15.1 የመጀመሪያ ደረጃ የአራት አመት ትምህርትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ባህሪያት /1-4/

- ደረጃውን የጠበቀ የእጅ ጽሑፍ የማንበብና መሠረታዊ ስሌት ችሎታዎች ይኖራቸዋል።
- ስለራሳቸው ማንነትና ምንነት፣ ስለቤተሰባቸውና ህብረተሰቡ ኃላፊነቶችና ችግሮች መጠነኛ ግንዛቤ አላቸው። የአቅማቸውን ያህል ኃላፊነት ይሰማቸዋል፣ ችግሮችንም ለመፍታት ጥረት ያደርጋሉ።
- ስለ ተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች ምንነት ጠቃሚነትና እንክብካቤ ያውቃሉ፣ በተግባር ይገልፃሉ፣ ያሳያሉ።
- በአካባቢው ያሉትን የሥራና የምርት እንቅስቃሴዎችን ያስተውላሉ፣ ይገነዘባሉ፣ በሚፈልጓቸው የሥራ ዘርፎች ይሳተፋሉ።
- በግለሰብ፣ በቤተሰብና በህብረተሰብ ደረጃ ጐጂና ጠቃሚ የሆኑትን አመለካከቶች፣ እምነቶች አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ይመረምራሉ፣ ያነፃፅራሉ፣ ይመርጣሉ።
- አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሚአቸው ለመጠየቅና ለመረዳት ይፈልጋሉ፣ ባገኙት ምክርም ለመጠቀም ይጣጣራሉ።
- ከችሎታውና ከአቅማቸው ጋር የሚጣጣሙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን የመሞከርና የመለመማድ ከፍተኛ ፍላጐት ያሳያሉ።
- የግልና የአካባቢ ንጽህና ይጠብቃሉ።
- ተግባርን በተናጠል ከመፈፀም ፋንታ እንዲተገቢነቱ በመስተጋብሮታዊ ተሳትፎ በጋራ ክንዋኔ ለጋራ ውጤት የመሰለፍ ስልትን ይለማመዳሉ።

1.15.2. የመጀመሪያ ደረጃ የሰምንት ዓመት ትምህርትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች /ባህሪያት/ /1-8/

- ለቀላል ሥራ ዝግጁ ናቸው።
- በእውቀትና በሙያ ዘርፎች መጠነኛ አጠቃላይ ግንዛቤንና ክሂሎትን የጨበጡ

በመሆናቸው ለብዙ አይነት ስልጠናዎች የተዘጋጁ ይሆናሉ።

- የእደጥበብ ችሎታዎች፣ የእጅ መሣሪያዎችና የቀላል መኪኖች አጠቃቀም ክሂሎት፣ የሥራ ሂደት እውቀት ስላላቸው በሥራ ላይ መመሪያ፣ ሥልጠናና ተከታታይ ድጋፍ እየተሰጣቸው ቁጥጥር እየተደረገ አምራች ሠራተኞች ይሆናሉ።
- በየደረጃው ኃላፊነት የሚሰማቸው ስለሆኑ ንቁ ባህላዊ ተሳትፎ ይኖራቸዋል።
- በተከታታይ ትምህርት አማካኝነት የአውቀት አድማሳቸውን ለማስፋት ክሂሎትን ለማዳበር፣ አስተሳሰብን ለማጐልበት የእደ ጥበብ ችሎታን ለማሻሻል ይችላሉ።
- በጋራ ክንዋኔ ለጋራ ውጤት በመስተጋብሮታዊ ተሳትፎ የመሰለፍ ልምድን ያዳብራሉ።